## የፊቱ ሽፋን መግለጫ

በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ከፊቱ በግራፊክ አርቲስት ምናሴ መላኩ የተሳሉ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሥራዎችና ገጽታዎች በቀይ ባህር ዳርቻ የቸንታውያን ወደብ ከተማ ከግብጽ መርከቦች ጋር ፣ በሲዳሞ የሻቢ ዋሻ ጥንታዊው የእንሰሳት ስዕል ፣ በትግራይ የአማታውያን ሀውልት ፣ በትግራይ የአክሱማውያን ሾጣጣው ሀውልት ፣ በቀይ ባህር ጠረፍ ጥንታዊው የአዱሊስ ከተማና ሰነዳዊ ሀውልት ፣ በሸዋ ጥንታዊው የጥያ የትክል ድንጋይ ሀውልት ፣ በላስታ የላሊበላው የቋጥኝ ድንጋይ ቤተ ክርስቲያን ፣ ጥንታዊው የሐረር መስጊድ ፣ ጥንታዊው የከፋ የወርቅ ዘውድ ፣ ታላቁ የጉንደር ከተማ፣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ህንፃ ናቸው ።

የሥራዎቹ ዝርዝር ታሪክና ትምህርታዊ ፋይዳ ከፎተግራፍ ጋር በመጽሐፉ ውስጥ አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ተብራርቷል ።

# የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ

## አንደኛ መጽሐፍ

ከዶክተር ላጵሶ ጌ. ድሌቦ

To my first and best teacher Bradford Lapsley with my best Wishes
11/4/91

— Ex Libris —
B. N. Lapsley
375 Willow Wood
Murphy, Texas 75094


አዲስ አበባ
1982

የመጀመሪያ ሕትመት መጋቢት 1982

የሁለተኛ ሕትመት ጥቅምት 1983

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ



ደራሲው ላጵሶ ጌ. ድሌቦ

# ማ ው ጫ


ገጽ

መቅድም ........................................ 9

ክፍል አንድ ........................ 17

የጥናቱ ቴዎሪና ስልት ..................... 17

የኢትዮጵያ ምድር፤ ሕዝብና መንግሥት................ 17

1. የታሪክና የቅድመ ታሪክ ትርጉም.......................... 17
2. የታሪክ መረጃና ትምህርት ............................ 20
3. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ አካባቢ............................ 24
4. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ................................ 26
5. ኢትዮጵያና ዓለም ........................................ 33
6. የጂኦፖለቲካ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ ............................ 37

    በጥንት ዘመን ........................................ 37
    በመካከለኛው ዘመን ........................................ 43
    በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ........................................ 51

ክፍል ሁለት ..................... 56

የኢትዮጵያ ታሪክ ዕድገትና ሂደት ..................... 56

1. በጥንት ዘመን ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 1270 ዓመተ ምሕረት ጥንት የሀበሻ ፤ የአማልክትና የቅመማቅመም አገር 56

    በ2800 ዓመተ ዓለም ........................................ 56
    የታሪክ መረጃ ........................................ 56
    የጥንት ምርትና ንግድ ........................................ 56

የደአማታውያን መንግሥት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 100 ዓመተ ምሕረት ........................................ 58

    የታሪክ መረጃ ........................................ 58
    ደአማት የኢትዮጵያ የሥልጣኔ መነሻ ..................... 59

የአክሱማውያን መንግሥት በዘመነ ክርስትና ከ100 እስከ 1100 ...... 62

    የታሪክ መረጃ ........................................ 62
    የግዛት አጼ ግምባታና ስፋት ..................... 63
    የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ሁኔታ ..................... 68
    የተፈጥሮ ሀብት ሚና ........................................ 71
    የንግድ ሚና ........................................ 73
    የድርጅት ሁኔታ ........................................ 77
    ቋንቋና ጽሕፈት ........................................ 79
    የጂኦፖለቲካ ሚና ........................................ 84

የአገው መንግሥት ከ1100 እስከ1270 .......................... 86
የደቡብ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ዕድገት ከጥንት እስከ1270 .......................... 90
የታሪክ መረጃ .......................... 90
የደቡብ ነባር ሕዝቦች .......................... 91
የመንግሥት ምሥረታና ዕድገት .......................... 93

2. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአጼው መንግሥት ዕድገት ከ1270 እስከ 1524 .......................... 98
የታሪክ መረጃ .......................... 98
መንግሥትና ሃይማኖት .......................... 99
የአጼው መንግሥት ዕድገት .......................... 102
ኢትዮጵያና የአረቡ ዓለም .......................... 104
የሱልጣኖችና የአጼዎች የሥልጣን ጦርነት .......................... 107

3. የአህመድ ግራኝ አመፅ ከ1524 እስከ 1543 .......................... 110
የታሪክ መረጃ .......................... 110
የአዳል የእርስ በርስ ጦርነትና የአህመድ ግራኝ አነሳስ .......................... 112
የአህመድ ግራኝ ጉሳና የጦር ድርጅት .......................... 118
የአመጹ አገር አቀፍ ሂደትና ስፋት .......................... 125
የአህመድ ግራኝ ውድቀት .......................... 141
የአህመድ ግራኝ አመጽ ውጤቶች .......................... 145
መደምደሚያ .......................... 155

4. ታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ ከ1520 እስከ 1660 .......................... 159
የታሪክ መረጃ .......................... 159
የፍለሳው ሂደትና ብሔራዊ ስፋት .......................... 162

5. የአጼው መንግሥት የምዕከልና ትግልና የውጭ ኃይሎች ግፊት 1540—1597 .......................... 178

6. የጐንደር መንግሥት ምስረታና የሃይማኖት ጦርነት 1597—1632 .......................... 194

7. የአካባቢ ሥርዓትና የንዑስ መንግሥታት ዕድገት 1632—1855 .......................... 240
የግዛተ አፄ መቀነስ .......................... 241
የሸዋ መንግሥት አነሳስ፣ ዕድገትና ፖሊሲ .......................... 242
የከፋ-ጊቤ መንግሥታት ዕድገትና ሀብታቸው .......................... 249
የጦርነት፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስተጋቢር .......................... 256

8. የውጭ ኃይሎች ግፊትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የአንድነት ትግል 1855—1900 .......................... 261

9. በኢትዮጵያ ታሪክ የመንግሥትና የሕብረተሰብ ግንኙነት .......................... 290

## ፎቶግራፍ

1. ደራሲው .......................... 3
2. ከአራት ሚሊዮን ዓመታት በፊት ሉሲ/ ድንቅነሽ የመጀመሪያው ሰው እጅግ ከሀደር አዋሽ ታሪካዊ ሥፍራ .......................... 26
3. የረጅም ዘመን ዕድሜ ያለው የቅድመ ታሪክ ሀውልት ከጥያ ሸዋ .......................... 27
4. ከ3500 ዓመታት በፊት በቀይ ባህር ዳርቻ የፑንታውያን ወደብ ከግብጻውያን መርከቦች ጋር .......................... 57
5. ከ2500 ዓመታት በፊት የደአማታውያን ሀውልት ከትግራይ .......................... 60
6. የአዱሊስ ከተማና ሰነዳዊ ሀውልት በ525 .......................... 61
7. ከ2000 ዓመታት በፊት የአክሱማውያን ሾጣጣው ሀውልት ከትግራይ .......................... 69
8. ጥንታዊው የላሊበላ የጸጥኝ ድንጋይ ቤተ ክርስቲያን .......................... 90
9. በ3000 ዓመታት የተገመተ የእንስሳት ስዕል በጥንታዊው የሻቢ ዋሻ በሲዳሞ .......................... 96
10. ጥንታዊው የሐረር መስጊድ .......................... 115
11. ጥንታዊው የሐረር ከተማ በ1850ዎቹ በእንግሊዛዊው መንገደኛ ሪቻርድ በርተን እንደታየው .......................... 154
12. በ1500ዎቹ በንግሥት እሌኒ የተሠራና በ1536 በአህመድ ግራኝ በከፊል የተቃጠለው የመርጦለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጐጃም .......................... 157
13 ጥንታዊው ከብረት የተሰራ ሙሉ የጦር መሳሪያ ከነባርኔጣው .......................... 188
14. ጥንታዊው የምጽዋ ከተማ በ1904 .......................... 192
15. ጥንታዊው የጐንደር ከተማ .......................... 211
16. በ1626 ከድንጋይና ኖራ በአጼ ሱስንዮስ በአባይ ወንዝ ላይ የተሠራ ባለገራቱ ታሪክ የመጀመሪያው ድልድይ .......................... 238
17. ጥንታዊው የከፋ የመርቅ ዘውድ .......................... 254
18. የኢትዮጵያ ጥንታዊው የገባር አገልግሎት በሸዋ ፤በ1890 .......................... 297

## ሠንጠረዥ

1. በአራተኛው ምዕተ ዓመት የአክሱማውያን የፊደልና የቁጥር ገበታ .......................... 81
2. በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት የደቡብ ኢትዮጵያ መንግሥታት የመሬት፣ የጦርና የድርጅት ገጽታዎች .......................... 94
3. በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ የሥልጣን ባላንጣ አጼዎችና ሱልጣኖች .......................... 100-101
4. በታላቁ ፍለሳ ሂደት በሀዲድ - ሲዳማ ተዛማጅ ማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረው ሊንጉዊስቲካዊ ግንኙነት .......................... 164
5 በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የኦሮሞ የገዳ ሐረግ ከባህርይ ዘገባ .......................... 170

# ካርታ


1. የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ ክልሎች ፣ በ1987 .................... 18
2. የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦች ስርጭትና ስብጥር .................... 32
3. የኢትዮጵያ የጥንት ዘመን ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 1270 ዓመተ ምሕረት .......... 55
4. የአጼው መንግሥት ዕድገት ከ1270 እስከ 1524 .................... 97
5. የአህመድ ግራኝ አመጽ ከ1524 እስከ 1543 .................... 158
6. ታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ ከ1520 እስከ 1660 .................... 177
7. የአጼው መንግሥት የምዕከልና ትግልና የውጭ ኃይሎች
   ግፊት ከ1540 እስከ 1597 - .................... 193
8. የአካባቢው መንግሥታትና የጦርነት ዘመን ከ1632 እስከ 1855- .................... 239
9. የውጭ ኃይሎች ግፊትና ብሔራዊ የአንድነት ትግል ከ1855 እስከ 1900.- .......... 260
10. ኢትዮጵያና የአካባቢው መንግሥታት ክስተት
    1910 — 1977 - .................... 289

የታሪክ መረጃ ምንጮች .................... 298


# መ ቅ ድ ም

በድህረ አብዮትና በዘመነ ሪፑብሊክ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግ ሥት በፖለቲካ፤ በድርጅት ፤ በትምህርት ፤ በባህል ፤ በኢኮኖሚና በአ ስተዳደር ፈጣን የሆነ የአገር ግምባታ ፖሊሲና ተግባር በማካሄድ ላይ ይገኛል ። በዚህታላቅ ፖሊሲና ፕሮግራም የአገሪቱ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ የአንድነትና የተግባር መሠረት ፤ መሣሪያ ፤ መመሪ ያና ሚዛን እንደሆነ በከፍተኛ ደረጃ በትክክል ታምኖበታል ።

በሌላ በኩል ረጅም የሥልጣኔ ልምድና ታሪክ እንደሚያስተምረን፤ የአንድ ሕዝብ የታሪክ እውቀት ለሕብረተሰቡ የአንድነት ፤ የድርጅት ፤ የተግባር ፤ የፖሊሲና የሕይወት መሠረት ፤ መሣሪያ ፤ መመሪያና ሚዛን ሆኖ የሚያገለግለው ከሁሉ በፊት ከእውነተኛ የታሪክ መረጃ የተገኘ የሰዎች የሥራ ፤ የልምድ ፤ የሕይወት ፤ የቋንቋ ፤ የባህል ፤ የእምነት ምርትና መግለጫ ተግባራዊ እውቀትና እውነት ሲሆን ብቻ ነው ።

በመሆኑም በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የተገኘ የአንድ የተወሰነ ሕዝብ እውነተኛው ታሪካዊ እውቀት ፤ እውነትና ትምህርት ምን እን ደሆነ መሠረታዊ ባህርዩን ተስማሚና ተግባራዊ በሆነ የጥናት ስልትና ሚዛን ማወቅና ለሌሎችም ማሳወቅ የአንድ የታሪክ ባለሙያ ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታ ነው ።

በዚህ ረገድ ይህ የታሪክ መጽሐፍ በአዲስ የጥናት ስልት በስነ ልሳን ፤ በሰነድ ፤ በትውፊት ፤ በአርኪኦሎጂና በፓሌኦንቶሎጂ መረጃ ዎች ላይ የተመሠረተ ረጅም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ታሪክ ነው። መጽሐፉ በአንድ መልኩ የኢትዮጵያ የታሪክ መረጃና ማስረጃ ማለትም ዝክረ ነገር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ባገር ቋንቋ ዘመናዊ የታሪክ ጥናት ስልት ነው ። ነገር ግን መጽሐፉ በታሪክ መረጃነቱም ሆነ በጥናቱ ስል ትነቱ ፍጹማዊነት የለውም ። በምንም ጊዜ በአዲስ የመረጃና የስልት ግኝት እየተሻሻለና እየዳበረ የሚሄድ ሥራ ነው ። ከአስተዋይ የታሪክ ተማሪና አንባቢ በሚፈልቀው ተጨማሪ የትምህርት ሀሳብ ፤ ሂስ ፤ ስልት ፤ ግኝትና አስተያየት በየጊዜው የበለጠ እየዳበረ የሚሄድ የታሪክ ጥናት ነው ።

ስለሆነም ለታሪክ ተማሪና አንባቢ የግንዛቤ ፤ የሂስና የአስተያየት መነሻ የሚሆኑ የጥናቱ የመረጃ ፤ የስልት ፤ የትርጉም ምንጮችና ሀሳ

ቦች በመጽሐፉ አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ ተብራርቷል ። ስለዚህ የጥናቱን መልእክት ለማግኘት የሚፈልግ የታሪክ ተማሪና አንባቢ መጽሐፉን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በትጋት ቢያነብ የበለጠ ጥቅም ያገኝበታል ።

የታሪኩን መነሻ በሚመለከት ደግሞ ፣ በመጽሐፉ የቀረበው የኢትዮጵያ ታሪክ ፈጣሪዎች ፣ ባለቤቶች ፣ ምክንያቶችና ተዋንያን በአገራቱ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር የኢትዮጵያ ነባርና ተዛማጅ የሆኑ ናይሎቲካዊ ፣ ኦሞአዊ ፣ ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ፣ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የጁዳይዝም ፣ የክርስትናና የእስልምና ሞናትስቲካዊ ( Monothesitic ) ማለትም መለኮታዊ እምነቶችና ባህሎች ናቸው ።

በመጽሐፉ ተደጋግሞ " የኢትዮጵያ መንግሥት " ሲባል የምስተዛማጅና የማይነጣጠሉ ነባርና ነዋሪ ሁኔታዎች ማለትም የኢትዮጵያ ምድር ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ታሪካዊ አንድነት ነው ። የሕዝቦች ብዛትና ታሪካዊ መስተጋቢር ፣ ባህላዊ መወራረስ ማለት ነው ። ባጭሩ የኢትዮጵያ አንድ ምድር ፣ የኢትዮጵያ አንድ ሕዝብ ፣ የኢትዮጵያ አንድ መንግሥት ፣ የኢትዮጵያ አንድ ሕብረተሰብ የኢትዮጵያ አንድ ታሪክ የመጽሐፉ መሠረታዊ ትምህርት ነው ።

ለመጽሐፉ ጥናት መነሻ የሆኑት ልዩ ልዩ የታሪክ መረጃዎች በአለፉት አምስት ሺህ ዓመታት ውስጥ በጥንታዊ የግብጽ ሃይሮግላፊክስ ፣ በጥንታዊ የዕብራይስጥ ፣ የደእማት ፣ የሳባ ፣ የግዕዝ ፣ የግሪክ ፣ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎች እንዲሁም በብዙ ዘመናዊ የውጭ አገር ቋንቋዎች ተጽፈው ወይም በትርጉም የተገኙበት የጊዜ ስሌት በአመዛኙ እንደ አውሮፓውያን ዘመን በመሆኑ የጥናቱም የዘመን አቆጣጠር በአውሮፓውያን የጊዜ ስሌዳ ነው ።

በመጨረሻም የመጽሐፉ ካርታዎች ከእኔ ከደራሲው በጽሑፍ በተሰጡ ረቂቅ የታሪክ መረጃ ንድፎችና ቢጋሮች መሠረት የተዘጋጁት በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በካርታ ዝግጅት ክፍል በቴክኒክ ባለሙያዎች በአቶ ዘሩ አብርሃምና በአቶ ዳንኤል ሰይፉ ነው ። በተረፈ የጥናቱ አጠቃላይ ስልትና ትርጉም ሁለንተናው በነ ራት አሥርታት የትምህርት የጥናትና የሥራ ዘመን በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሙያ መሣሪያ የተገኘ የራሴ የግል ሥራ ነው ።

ሆኖም ለዚህ የታሪክ ሥራዬ ምርምርና ምርት በረጅም የትምህርት፣ የጥናትና የሥራ ዘመን በአገር ውስጥና በውጭ አገር አስተዋጽኦ ያደረጉ ሁኔታዎች ፣ ሰዎች ፣ የትምህርትና የባህል ተቋማት ፣ መጻሕፍት ፣ ምሁራንና ፈላስፋዎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ባለሥልጣናት



በጣም ብዙ ናቸው ። ከእነዚህ ጥቂቱን እንኳን ለማስታወስ ያህል የሚከተለውን የሕይወቴንና የሥራዬን አጭር ዘገባ አቀርባለሁ ።

በግንቦት 1930 በደቡብ ሸዋ አስተዳደር አካባቢ በሶር አውራጃ በኩቱና ቀበሌ በትንሹ የጋር መንደር አምስተኛው ልጃቸው በመሆን ከእስላም ወላጆቼ ከአቶ ድሌቦ ሸለሞና ከወይዘር አሹሬ ደጐ ተወለድኩ ። በአባቴ ወገን ሀዲያ በእናቴ ወገን ከምባታ ነኝ ። ከወላጆቼ የተሰጠኝ ስሜ ላጽሶ ነው ። በሀዲይኛ ትርጉሙም አስግግው ፣ ሰላሙ ፣ ታረቀኝ እንደ ማለት ነው ። በ1943 የ13 ዓመት ልጅ ሆኜ አባቴና እናቴ በአንድ ሳምንት ውስጥ በሞት ተለዩኝ ። በመሆኑም ረጅም የችግር ዕድገትና ኑሮ አጋጠመኝ ። በ1946 በ16 ዓመት ዕድሜዬ በአንድ ዘመዴ በአቶ ወልደዮሐንስ ደልክሶ እርዳታ በሆሳዕና ከተማ አጠገብ በሚገኘው በቦቢቾ የሱዳን ኢንተርየር ሚሲዮን ትምህርት ቤት በአንደኛ ክፍል ረጅም የተማሪ ሕይወትና ጉዞ ጀመርኩ ። ሁለተኛው ስሜ " ጌታሁን" የተሰጠኝ በዚሁ ትምህርት ቤት በሰኔ 1946 ነው ። በዘመኑ በአካባቢው አንድ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ወደ ትምህርት ቤት ሲገባ የስምና የሃይማኖት ለውጥ የተለመደ ነገርና አሠራር ነበር ።

በ1950 በቦቢቾ የሚሲዮን ትምህርት ቤት በአስተማሪዎቹ ምክርና እርዳታ የስድስተኛ ክፍል ትምህርት ጨረስኩ ። በክፍል ትምህርት ውጤት በመጀመሪያ ደረጃ ከሚጠሩ ተማሪዎች አንዱ ነበርኩ ። በመጽሐፍ ቅዱስ በታሪክና በንግግር ትምህርት በተለይ ጉበዝ ተማሪ ነበርኩ። ከገጠር የገበሬ ጉልማሳ ተማሪ በመሆኔ ምክንያት ከጥናት በስተቀር ለጨዋታ ጊዜም ፍላጐትም አልነበረኝም ።

ከ1951 እስከ 1952 በሆሳዕና ከተማ በራስ አባተ ኳያለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ተማርኩ ። በአንድ ሺህ ከሚቆጠሩ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል በሳምንታዊ ውይይት (ዲቤት) አንደኛ በመሆን ከአውራጃው ገዥ ሽልማትና የምስክር ወረቀት አገኝቻለሁ ። በሕይወቴ የማይረሳኝ አንድ ታላቅ ነገር ፣ በቦቢቾና በሆሳዕና ተማሪ የነበርኩበት ዘመን በመሬትና በግብር ችግር ምክንያት ከአውራጃው ብዙ ሕዝብ ለኑሮና ለቅጥር ሥራ ወደ አዲስ አበባ ፣ ጂማ ፣ ሻሸመኔ ፣ ወንጂና ድሬዳዋ የሚሰደድበት ጊዜ ነበር ። በዚሁ ወቅት የዘመዶቼና ለእኔም በውርስ የሚደርሰኝ መሬት በኃይለኛ ጉልተኞችና የመንግሥት ባለሥልጣናት ተያዘ ። ይህ በልጅነት ዘመን በትውልድ አገሬ ያየሁት ታላቅ የመሬት ችግር በኋላ እኔን የታሪክ ባለሙያ ከአደረጉኝ ብዙ ሥርዓታዊ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሆነ ።

ከ1953 እስከ 1956 በናዝሬት ከተማ በአጼ ገላውዴዎስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በባይብል አካዳሚ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማርኩ

በቦቢቾ ከአንድ እስከ ስድስተኛ ፤ በባይብል አካዳሚ ደግሞ ከአሥረኛ
እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት የተማርኩት በቅደም ተከተል
በሱዳን ኢንተርየርና በሜኖናይት ሚሲዮናውያን ሙሉ እርዳታ ነበር ።

በናዝሬት በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ለአራት ዓመታት ተማሪ
በነበርኩበት ዘመን በየሳምንቱ መጨረሻ ከአርብ እስከ እሁድ በየእረፍቱ
ወቅት ደግሞ ከሰኔ እስከ መስከረም በወንጂና ሸዋ በአሥራ ሁለት ልዩ
ልዩ የሸንኮራ አገዳ ማሳ ሠፈሮች ፤ በእግርና በቢስክሌት እየተመላለስኩ
ለሠራተኞች ወንጌልና ትምህርት አስተምር ነበር ። በተጨማሪም ከሠራ
ተኞቹ በፈቃዳቸው በተዋጣና ከሜኖናይት ሚሲዮናውያን በብድር በተ
ገኘ ገንዘብ በሸዋ ስኳር ፋብሪካ አጠገብ በዓለም ጤና ከተማ ከባለመሬቱ
በድርጅቱ ስም በተከራየው መሬት ላይ በ1954 የወንጂ - ሸዋ ሠራተኞች
ቤተክርስቲያንና የግል ትምህርት ቤት አሰራሁ ። የሁለተኛ ደረጃ ትም
ህርት ከጨረስኩ በኋላ ከ1957 እስከ 1958 የቤተክርስቲያኑና የትምህርት
ቤቱ ኃላፊና አስተማሪ በመሆን ለሁለት ዓመታት የአካባቢውን ሕዝብ
አገለገልኩ ። ዛሬ ትምህርት ቤቱ ከምስራቅ ሸዋ አስተዳደር አካባቢ
የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ ነው ።

በትውልድ አገሬ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ስማር በሕብረተሰቡ
ላይ በመሬትና በግብር ችግር ምክንያት ይደርስበት የነበረውን መከራ
ከዚህ በላይ ባጭሩ ጠቅሻለሁ ። አሁን ደግሞ ከ1953 እስከ 1958 በናዝሬት
ወንጂ አካባቢ በነበርኩበት ጊዜ ሆላንዳዊ ዓለም አቀፍ የግል ኩባንያ
በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ በወንጂ ሜዳ ላይ በነባሩ የጅሌ ማህበረሰብና በነ
ጠር ከጉልተኞችና ከመንግሥት ባለሥልጣኖች በመሬትና በግብር ችግር
ተሰደው በመምጣት ቅጥር ሠራተኞች በሆኑ ወዛደሮች ላይ ያካሄድ የነ
በረውን የሕይወት ጥፋትና የጉልበት ብዝበዛ የዓይን ምስክር ሆኜ አየሁ ።

በዚህ ረገድ ፤ ከ1944 እስከ 1954 ድረስ ፤ አንደኛ ፤ ኩባንያው የጅ
ሌን ነባር ማህበረሰብ ከወንጂ ቀበሌ አለምትክ ካሳና አድራሻ ነቀለ ።
ሁለተኛ ፤ የተባበሩት መንግሥታት የወባ ማጥፊያ ድርጅት በ1950
ዎቹ ከወንጂ አካባቢ የወባ ትንኝ እስኪያጠፋው ድረስ ከገጠር በመሬት
ችግር ምክንያት ተሰደው የመጡ የኩባንያው ሠራተኞች በመጀመሪያ
ዓመታት በወባ በሽታ በብዛት እንደሞቱና ከሞት የተረፉት ደግሞ በኩ
ባንያው ከባርነት በማይሻል ሁኔታ ሲበዘበዙ የዓይን ምስክር ሆኜ ለማ
የት ቻልኩ ። ይህ በወንጂ በጅሌ ማህበረሰብና በኩባንያው ሠራተኞች
ላይ ሲፈጸም በዓይኔ ያየሁት ሁኔታ የኢትዮጵያን ታሪክና የቀድሞውን
ሥርዓት ከሥሩ እንዳጠና ካነሳሱኝ ብዙ ሁኔታዎችና ምክንያቶች አንዱ
ሆነ ። ከእነዚህም ዋነኛው የመሬት ጥያቄ እንደሆነ ከዚህ በላይ ተገል
ጾአል ።



የታሪክ ጥናት በሚመለከት ፤ በ1958 በ28 ዓመት ዕድሜዬ ከሜኖ
ናይት ሚሲዮን በተሰጠኝ እስኮላርሽፕ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ
ሄድኩ ። በ1962 በቨርጅኒያ እስቴት ከኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ በታ
ሪክና በሃይማኖት ትምህርት የባችለርስ ዲግሪ አገኘሁ ። በ1963 በዋሽን
ግተን ዲሲ ከተማ ከሀዋርድ ዩኒቨርስቲ በታሪክ የማስትሬት ዲግሪ አገ
ኘሁ ። ቀጥሎም በከፍተኛ የትምህርት ውጤትና የውድድር ሚዛን የፎ
ርድ ፋውንዴሽን ፌሎውሺፕ ሽልማት አሸንፌ በግራጁየት ፌሎው ማ
ዕረግ አስፈላጊውን ጥናትና ሥራ በማጠናቀቅ በ1966 ከሀዋርድ ዩኒቨ
ርስቲ በታሪክና በፍልስፍና የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ አገኘሁ ። ከ1967 እስ
ከ1968 በአሜሪካ በቨርጂኒያ እስቴት በሪችማንድ ከተማ በቤርጂኒያ
ዩኒየን ዩኒቨርስቲ በረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ የአፍሪካ ጥናት ክፍል ኃላ
ፊና የታሪክ አስተማሪ ሆኜ ሠራሁ ።

በግንቦት 1968 በእናት አገር ጥሪ ወቅት የቨርጂኒያ ዩኒየን ዩኒቨር
ስቲ ሥራ በፈቃዴ ለቅቄ ወደ አገሬ በመመለስ ከ1968 እስከ 1969 በማ
ስታወቂያ ሚኒስቴር ፤ ከ1970 እስከ 1975 በባህል ሚኒስቴር በተለይ
የአብዮቱን ታሪካዊ መነሻና ሂደት እንዲሁም የኤርትራ ችግር በሚ
መለከት ሰፊ የጥናት ሥራ አካሂጃለሁ ። ከግንቦት 1975 እስከ ዛሬ ድረስ
በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በዋና የታሪክ ኤክስፐር
ትነት በኢትዮጵያ ታሪክ ፣ አብዮትና ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ
ተመሳሳይ ሥራ በማካሄድ ላይ እገኛለሁ ።

በአሜሪካ በትምህርትና በሥራ ምክንያት ለአሥር ዓመታት በቆ
የሁበት ዘመን የአገሪቱን ወቅታዊ የሥርዓትና የፖለቲካ ጉዳዮችን በሚ
መለከት በሰሜን አሜሪካ አብዮታዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
አባል ነበርኩ ። ከትምህርት አኳያ በፍልስፍና መሠረታዊ የሰው ፤ የሕብ
ረተሰብ ፤ የተፈጥሮ ፤ የሕይወት ፤ የእውቀት ፤ የንብረት ፤ የሕግ ፤ የሃይ
ማኖት ፤ የኤትክስ ፤ የርዕዮተ ዓለም ፤ የፖለቲካ ሥርዓትና የመንግሥት
ጉዳዮችን በሚመለከት ከምዕራብ ታላላቅ ፈላስፋዎችና ምሁራን በተ
ለይም ከፍራንሲስ ቤከን ፤ ከሬኔዲካርት ፤ ከጆርጅ በርክሊ ፤ ከባሩክ
እስፕኖዛ ፤ ከቶማስ ሆብስ ፤ ከጆን ላክ ፤ ከዴቪድሁም ፤ ከኢማኑኤል
ካንት ፤ ከጆርጅ ሄገል ፤ ከሰረን ክርከጋርድና ከካርል ማርክስ እንዲሁም
የታሪክ ትምህርት በሚመለከት ከሄገልና ከማርክስ ታላቅ ትምህርት
አግኝቻለሁ። በተጨማሪም በሀዋርድ ዩኒቨርስቲ ታዋቂው አፍሮ-አሜሪካ
ዊ የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ቻንስለር ዊሊያምስ በአፍሪካ ታሪክ የጂኦ
ፖለቲካና የውጭ ኃይሎች የተጽዕኖ ሚና በሚመለከት መሠረታዊ ትም
ህርት አስተምሮኛል ።

በውጭ አገር በልዩ ልዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና መስኮች የተማርኩት ትምህርት ሁሉ ከታሪክና ከፍልስፍና አኳያ የኢትዮጵያ ተጨባጭ የሥርዓትና የማህበራዊ ዕድገት ችግሮችን ለዓይነተኛው መፍትሔ በትክክል ለማወቅና ለሌሎችም ለማሳወቅ ተግባራዊ የእውቀት መሣሪያ ነው ። በዚህ ረገድ አንደኛ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በሀዋርድ ዩኒቨርስቲና በታላቁ የአሜሪካ የኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ በታዋቂ የታሪክ ምሁራን ምክርና ድጋፍ ከ1857 እስከ 1909 ድረስ ባለው ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ በተለይ ባካሄድኩት ጥናት መሠረት ፤ በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ መሠረታዊ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች በደቡብ የመሬት የብሔረሰብ ፤ የሃይማኖት የባህል ድርብርብ ጥያቄ በሰሜን ደግሞ የኤርትራ ልዩ የፖለቲካ ችግር እንደሆኑና የችግሮችም ታሪካዊ መነሻ በአገሪቱ ታሪክ በአለፈው ምዕተ ዓመት ለማዕከላዊው መንግሥት ምዕክልና በተካሄደው የአገር ግምባታ ትግል ወቅትና ሂደት ውስጥ እንደሆነ ለማወቅ ችያለሁ ። በኋላ የአብዮቱ ፍንዳታና ሂደት የተጠቀሱ ችግሮችን ታሪካዊ መነሻና መፍትሔ በሚመለከት የእኔን የታሪክ ግምገማና ግንዛቤ የበለጠ አጠናከረ ።

ሁለተኛ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብን ሕብረተሰብንና መንግሥትን ታሪካዊ ዕድገትና አንድነት በሚመለከት ደግሞ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ በተለይ በአለፉት 2500 ዓመታት ውስጥ በጥንታዊ የዶእማት ፤ የሳባ ፤ የግዕዝ ፤ የግሪክ ፤ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎች ተጽፈው በልዩ ልዩ ወቅቶች፤ መንገዶችና መሣሪያዎች በተገኙ የታሪክ መረጃዎች ላይ ፤ በብዙ ዘመናዊ የውጭ አገር ቋንቋዎች በተጻፉ የታሪክ መረጃዎች ላይ ፤ በዘመናዊ የስነ ልሳን መረጃዎች ላይ ፤ በአገሪቱ ጥንታዊ የትውፊት መረጃዎች ላይ ጥናት በማካሄድ በአገኘሁት ትምህርታዊ ግንዛቤ መሠረት ወደሚከተለው የታሪክ እውቀትና አቋም ላይ ደርሼበታለሁ ።

በዚህ ረገድ ፤ በረጅም የታሪክ ጉዞና ልምድ የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕዝብና ሕብረተሰብ ብሔራዊ አንድነት የተፈጠረው በጥንታዊውና በማዕከላዊው መንግስት ሥር በአገሪቱ ነባርና ተዛማጅ በሆኑ ናይሎቲካዊ ፤ ኦሞአዊ ፤ ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች መስተጋብር ባህላዊ መወራረስ ፤ በአገሪቱ ጥንታዊ የጁዳይዝም ፤የክርስትናና የእስልምና መለኮታዊ እምነቶችና ባህሎች መስተጋብርና መወራረስ እንደ ሆነ ለማወቅና ለማመን ችያለሁ ።

ዛሬ በድህረ አብዮትና በዘመነ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ማዕከላዊው በሀውርታዊውና ጥንታዊው መንግሥት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የብሔራዊ አንድነትና ዕድገት ታሪካዊ መሠረትና መሣሪያ እንደሆነ ተረድቻለሁ።



በዚህ በኢትዮጵያ መንግሥታዊና ባህላዊ መሠረት የአገሪቱ ሁሉም ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች በብሔራዊ አንድነትና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት ተሳስረው በሰላም በጋራ ብልጽግና የሚኖሩበትን አዲስ ማህበራዊ ሥርዓት መገንባት እንደሚገባና እንደሚቻል በራሴ የታሪክ ጥናት ተረድቻለሁ ።

በዚህ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ግንዛቤ መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የአብዮቱን ታሪካዊ መነሻና ሂደት ፤ የአገሪቱን በሀውርታዊ መንግሥትና ብሔራዊ አንድነት ፤ የኤርትራን ወቅታዊ ችግርና የሪፐብሊኩን ምስረታ በሚመለከት በልዩ ልዩ መንገዶችና መሣሪያዎች ማለትም በሕትመት ሥራ ፤ በስብሰባ ፤ በምሁራን ጉባኤ፤ በብሔራዊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ሚዲያ ኢትዮጵያ ኤ ክራድል ኦፍ ሂስትሪ ማለትም ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ በሚል ርዕስ የአገሪቱን የመጀመሪያ የታሪክ አትላስ ጨምሮ ከአንድ መቶ በላይ ጥናታዊ ጽሑፎችንና ንግግሮችን አቅርቤአለሁ ። በሪፐብሊኩ ምስረታ ጥናትና ሂደት ከኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ፤ ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በአገር ውስጥና በውጭ አገር በልዩ ልዩ መንገዶች ፤ መድረኮችና መሣሪያዎች የኢትዮጵያን በሀውርታዊ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በሚመለከት የግንዛቤ ሀሳብና አቋም ለሚመለከተው ሁሉ ባለኝ ችሎታ የማውቀውን ለማሳወቅ በማምንበት ለማሳመን ጥረት አድርጌአለሁ ።

በተጠቀሱት ጊዜያት ፤ መድረኮች ፤ መንገዶችና መሣሪያዎች በኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ላይ ላቀረብኳቸው የግንዛቤ ሀሳቦችና አስተያየቶች ከሕብረተሰቡ ከተለያዩ ክፍሎችና ግለሰቦች ማለትም ከሰፊው ሕዝብ ፤ ከባለሥልጣኖች ፤ በውጭ አገር ከኢትዮጵያ ተማሪዎችና ምሁራን ፤ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፤ በባህል ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ከሥራ ኃላፊዎችና ባልደረቦች በልዩ ልዩ ሥፍራዎች መንገዶችና ምክንያቶች የተሰጠኝ ድጋፍ በታሪክ ትምህርትና ሥራዬ ላይ ተጨማሪ ትጋትና ብርታት እንደሰጠኝ በኩራት እየገለጽኩ በዚህ አጋጣሚ ለተጠቀሱት ወገኖች ሁሉ ፤ እንዲሁም በአገር ውስጥና በውጭ አገር እኔን ከገጠር የገበሬ ጉልማሳ ላስተማሩ ሰዎችና የትምህርት ተቋማት በሙሉ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

በመጽሐፉ ሕትመት የንግድ ማተሚያ ቤት ሥራውን በከፍተኛ ጥራትና ፍጥነት ስለአከናወነልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው ።

እንዲሁም የመልካም ቤተሰብ አስተዋጽኦ በሚመለከት በዚህ ያል ተወሰነ የቤተሰብ ጊዜ ሕይወትና ባጀት በጠየቀ ረጅምና አስቸጋሪ በሆነ የታሪክ ጥናት ባለቤቴ ወይዘሮ ሽቶ ግርማና ልጆቼ ጸጋነሽና ትዕግሥት የሰጡኝ የመንፈስና የሞራል ብርታት ሳይታወቅ የማይታለፍ ነው ። በመጨረሻም መጽሐፉ በወጣትነታቸው ላለፉት ወላጆቼ ለአቶ ድሌቦ ሽለሞና ለወይዘሮ አሹሬ ደጉ መታሰቢያ ነው ።

ላ .ጌ. ድ.



# ክፍል አንድ

## የጥናቱ ቴዎሪና ስልት

## የኢትዮጵያ ምድር ፣ ሕዝብና መንግሥት

### 1. የታሪክና የቅድመ ታሪክ ትርጉም

በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ዘመን ፣ ማህበራዊ ሕይወትና ሥራ ቅድመ ታሪክና ዘመነ ታሪክ ተብሎ በሁለት ዋና ዋና ክፍለ ዘመናት ይከፈላል ። የሁለቱ ዘመናት የልዩነት ድንበር የታሪክ መረጃ ነው ። ቅድመ ታሪክ የሰው ልጅን ዘመን ፣ ሕይወትና ሥራ ከጊዜና ከባህል አንጻር በትክክል ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ የድርጅት ፣ የባህል የምርት ፣ የቅርጻ ቅርጽ ፣የጽሁፍና የሥራ መግሪያ መረጃዎች የማይገኙበት ክፍለ ዘመን ነው ። ዘመነ ታሪክ ደግሞ በዓለም ላይ የሰው ልጅን ማህበራዊ የአኗኗር ዘዴ ለይቶ ለማወቅ የሚረዱ የድርጅት ፣ የባህል ፣ የምርት መግሪያ ፣ የቅርጻ ቅርጽ ፣ የጽሁፍና የቋንቋ መረጃዎች የሚገኙበት ክፍለ ዘመን ነው ። በመሆኑም ታሪክ ማለት ከተጨባጭ መረጃ በመነሳት ፣ የእንስሳት እርባታ ፣ የእርሻ ፣ የገጠር ፣ የከተማ ፣ የንግድና የዕደ ጥበብ ተግባራትን ጨምሮ የህብረተሰብን ማህበራዊ ድርጅትና አኗኗር ፣ የሥራ ዓይነትና ክፍፍል የሚያስተምረን አጠቃላይ የጥበብ ዘርፍ የትምህርት ምንጭና መክፈቻ ነው ።

የቅድመ ታሪክ የመታወቂያ ገጽታዎች በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ጥበብ ከከርሰ ምድር የሚገኙ ጥንታዊ የድንጋይና የአጥንት መግሪያዎች ማለትም በቴክኒካዊ አነጋገር የፖሊኦንቶሎጂ ( Paleontology ) ግኝቶች እንደ ሚያስረዱን ፣ በዚህ ዓለም የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ከዛሬ አራት ሚሊዮን ዓመታት ገደማ በፊት በአፍሪካ አህጉር በሰሜን ከቀይ ባህር ጀምሮ በደቡብ እስከ ሞዛምቢክ ድረስ በሚገኘው በምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ መስመር ውስጥ ነው ።[1]

እንዲያውም ከሀዳር ፣ ከመልካ ቁንጥሬና ከእሞ ፖሊኦንቶሎጂያዊ ስፍራዎች የተገኙ ጥንታዊ የድንጋይና የአጥንት መግሪያዎች እንደሚያረጋ

[1] UNESCO,*General History of Africa I: Metheodology and African Pre-History* (1981), pp. 300-301.




**የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ ክልሎች ፣ በ1987**



ግጡት ፤ በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሰው ዘር ምንጭና መነሻ የሆነው ልዩ ምድር የኢትዮጵያ የአዋሽ - ኦሞ ወንዞች ክልል ነው ።[2]

የማህበራዊ ድርጅት ፤ የሥራ ዓይነትና ክፍፍል ፤ የቅርጻ ቅርጽና የጽሁፍ መረጃዎች የዘመንና የሥልጣኔ መለኪያ መስፈርቶች ናቸው በተባለው መሠረት ፤ ከቅድመ ታሪክ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ ባህላዊ የሥልጣኔ ሥራ የተጀመረው ከሞላ ጎደል ከዛሬ 6,000 ዓመታት በፊት በታችኛው የአባይ ወንዝ ዳርቻ በጥንታዊ ግብጽ ነው[3] ። በጥንታዊ ግብጽና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በንግድና በባህል የነበረው ግንኙነት በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ስፍራና ጊዜ ይገለጻል ።

የታሪክ መነሻና መሠረት የሰው ልጅን ሕይወትና ተግባር በተጨባጭ ከስፍራና ከጊዜ አንጻር በትክክል ከስልተ ምርትና ስርዓተ ማህበር አኳያ አገናዝቦ በዘዴ ለማወቅና ለማስተማር የሚያስችል የመሣሪያዎች የሁኔታዎችና የነገሮች መረጃ ነው ብለናል ። ዛሬ ዘመናዊ የሳይንስ ጥበብና የአሰራር ዘዴ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ሦስት መሠረታዊ የታሪክ መረጃ ዐይነቶችና ምንጮች አሉ ። እነዚህም (1) የሰነድ ( የጽሁፍ፤ የስዕል ፤ የቅርጽ) ፤ (2) የትውፊት (ባህላዊ የአፈ ታሪክ ወይም የኪነ ቃል ) እና (3) የስነ ልሳን ማለትም የቋንቋ ሳይንስ ( ሊንጉዊስቲስ ) መረጃዎች ናቸው ። አንድ ምሁር እነዚህን የተለያዩ የሰነድ ፤ የትውፊትና የስነ ልሳን መረጃዎች ከራሱ የግል የጥናት ዘዴና በአጠቃላይ ስለ ሰውና ስለ ተፈጥሮ ከአለው ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት ጋር አዋህዶና አቀነባብሮ ከጥሬው የታሪክ መረጃ ተግባራዊ የሆነ የታሪክ ግንዛቤ ፤ ዕውቀትና እውነት ለማወቅና ለማስተማር ይችላል ። የትላንትን ታሪካዊ ልምድ ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሰው ልጅን የነገውን የዕድገት አቅጣጫና አዝማሚያ ሊጠቁም ይችላል ።

ከዚህ ተግባራዊ የታሪክ ግንዛቤ በመነሳት ፤ በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብና ህብረተሰብን በተመለከተ መሠረታዊ የታሪክ መረጃ ፤ ይዘት ፤ ሂደት ፤ እውቀትና እውነት ምን ይመስላል ምንስ ሊያስተምረን ይችላል የሚለው ጥያቄ ተገቢና ወቅታዊ ነው ። ከዚህ በታች እንደሚታየው፤ በአንጻራዊ አባባል ፤ የኢትዮጵያ ምድርና ህዝብ በሶስቱም ማለትም በሰነድ ፤ በትውፊትና በስነ ልሳን መረጃ መስኮች ሰፊ የታሪክና የባህል ቅርስ አለው ።

---

[2] *Ibid*., pp. 412-19,438-48.

[3] C. Williams, *The Destruction of Black Civilization: Great Issues of A Race from 4500 B.C. To 2000 A.D.* (1971). p. 15.

## 2. የታሪክ መረጃና ትምህርት

ሥፍራና ጊዜ የመሆንና የመኖር ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው ። በመሆኑም የአንድ አገር ታሪክም በሥፍራና በጊዜ የተካበተ ጥቅል የሥራ ፣ የልምድ ፣ የድርጅት ፣ የትምህርት ፣ የዕደ ጥበብ ፣ የቴክኖሎጂ ፣ የስልተ ምርት ፣ የእምነትና የባህል ውጤት ማለትም የእውቀት ክምችት ፣ ምንጭና ግንዛቤ ነው ለማለት ይቻላል ። ዛሬ በዘመን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ታሪክን በጥናትና ምርምር ሚዛን በትክክል ለመግር ፣ ለማወቅ ፣ለመጻፍና ለማስተማር በቅድሚያ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ደግሞ

1. የታሪክ መረጃ
2. ዓይነተኛ የሆነ የታሪክ ትምህርትና ሙያ
3. የታሪክ ፍልስፍና ናቸው ።

ስለሆነም በድህረ አብዮት የኢትዮጵያን ረጅምና ውስብስብ የሆነ ታሪክ ከስልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር አንጻር በሥፍራና በጊዜ በሳይንሳዊ ሚዛን በትክክል ለማጥናትና ለማወቅ ፤—

1. በአገር ውስጥ በጥንታዊ የደአማት የሳባ ፣ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉየኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከወርቅ ፣ከነሐስና ከመዳብ ከተሠሩ ጥንታዊ ገንዘቦች ጋር ፤

2. ከውጭ ደግሞ የጥንታዊ ግብጻውያን ስዕላዊ የሃይሮግላፊክስ ( Egyption Hieroglyphics ) መረጃ ከብዙ ጥንታዊ የዕብራይስጥ ፣ የግሪክ ፣ የሮማውያን ፣ የአረብ ጸሐፊዎችና የታሪክ ባለሙያዎች ከጻፉት መጻሕፍት ጋር ፤
3. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በግዕዝ ቋንቋ በብራና ላይ የተጻፉ የኢትዮጵያ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የቅዱሳን ገድሎች ፤

4. ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በየጊዜው በምዕራብ የዲፕሎማሲ መልእክተኞች ፣ ሚሲዮናውያን ፣ የአገር ጐብኚዎችና ምሁራን ስለ ኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በብዙ ዘመናዊ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍት ፤
5. ከቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የኢትዮጵያ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች የሕግ መዛግብትና የመሥሪያ ቤት ሰነዶች ፤
6. የትውፊትና የስነ ልሳን መረጃዎች መሠረታዊና አስፈላጊ የሆኑ የትምህርትና የእውቀት ምንጮችና መግሪያዎች ናቸው።



ጥንታዊ ግብጻውያን በዓመተ ዓለም በግምት ከ2800 እስከ 1300 ድረስ ለ1500 ዓመታት በሁለቱም በባህርና በምድር ማለትም በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በአፍሪካ ቀንድ ከጥንታዊው የፑንት አገር ጋር ለረጅም ዘመን የንግድና የሃይማኖት ግንኙነት እንደነበራቸው የአገሩንም ሕዝብ ፣ እንስሳት ፣ እጽዋት ፣ እዝርዕት ፣ የእርሻና የንግድ ምርቶች ፣ ሃይማኖትና አማልክት ጨምሮ በስዕልና በጽሑፍ የሚገልጹ ብዙ ጥንታዊ የሃይሮግላፊክስ መረጃዎች አሉ ። [1]

በአገር ውስጥ ደግሞ በአራቱ ጥንታዊ የደአማት ፣ የሳባ ፣ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 1000 ዓመተ ምሀረት ድረስ በ1500 ዓመታት ውስጥ የተጻፉና በ450 የሚቆጠሩ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በአለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በሰሜን ኢትዮጵያ በአረቢያ ፣ በሱዳንና በግብጽ በድምር ከ50 ከሚበልጡ ታሪካዊ ሥፍራዎች በ30 በሚቆጠሩ ምሁራንና ተመራማሪዎች ተገኝተው አሁን በብዙ ዘመናዊ ቋንቋዎች ትርጉም ለምርምር አገልግሎት ቀርበዋል ። [2]

ከእነዚህ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከቅርብ ዓመታት በፊት ከኤርትራና ከትግራይ የተገኙትና በዓመተ ዓለም ከ430 እስከ 330 ድረስ ባለው በአንድ ምዕተ ዓመት ውስጥ ራሳቸውን የደአማት ነገሥታት ብለው በሚጠሩ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ነገሥታት በሁለቱም በደአማትና በሳባ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ ከአሥር በላይ ዜና መዋዕሎች [3] በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ በአንድ አክሱማዊ ንጉሥ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ተጽፎ ከአዱሊስ ከተማ የተገኘው ታሪካዊ ሰነድ ፣ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ብዙ ዜና መዋዕሎች በተለይ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክ በሚመለከት ቁልፍ የእውቀት ምንጮችና መግሪያዎች ናቸው ።

የኢትዮጵያን የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ በሚመለከት ደግሞ በ1332 የተጻፈው የአጼ ዓምደጽዮን ዜና መዋዕል ፣ ሁለት ታዋቂ የአረብ የታሪክ ጸሐፊዎች አልማሪና ማክሪዚ በቅደም ተከተል በ1335 እና በ1435 አካባቢ ስለ ሰባቱ የኢትዮጵያ እስላማዊ የይፋት - አዳል ፣ የደዋር የአራባቢኒ ፣ የሀዲያ ፣ የሻርካ ፣ የባሊና የደራ መንግሥታት የጻፉት ሁለት የታሪክ መጻሕፍት ፣ በ1434-1468 የተጻፈው የአጼ ዘርዓያዕቆብ ዜና መዋ

---

[1] Richard Pankhurst, *An Introduction to the Economic History of Ethiopia*, (1961), pp.3-6.

[2] E. Bernand, A. J. Drewes, R. Schneider, et F. Anfray,eds, *Recuell des Inscriptions DeL'Ethiopie Des Periodes Pre - Axoumite et Axoumite* (Forthcoming).

[3] Roger Schneider, "Les *Debuts* De *L*'Histoire Ethiopienne," *Documents Histoire Civilisation Ethiopienne*, RCP 230, CNRS,fasc.7 .(1976), pp.51-54.

ዕል ፤ በ1535 የተጻፈው የኢማም አህመድ ግራኝ—ዜና መዋዕል ፤
በ1563-1597 የተጻፈው የአጼ ሠርፀድንግል ዜና መዋዕል ፤ በ1593
በአባ ባሕሪ የተጻፈው የኦሮሞ ፍለሳ ታሪክና በ1605-1632 በጸሐፊ ትእ
ዛዝ ተክለ ሥላሴ የተጻፈው የአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል የዘመኑ ቁልፍ
የታሪክ ምንጮች ናቸው ። [4]

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን ማዕከላዊ የአጼው መንግ
ሥት ምስረታ በሚመለከት ሦስቱ የአጼ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ፤
የአጼ ምኒልክ ዜና መዋዕልና በ1945 <u>በኢትዮጵያ ከጥንታውያን የፍርድ
መዛግብት የተገኘና የተዘጋጀ የፍትሐብሔር ሕጋዊ ድርጅት</u> በሚል
ርዕስ በአራት ቅጾች የተሰበሰበው ግዙፍ የሕግ መጽሐፍ የዘመኑ
ታሪክ መሠረታዊ ምንጮችና መሣሪያዎች ናቸው ።

<u>ሊንጉዊስቲክስ</u> ማለትም ስነ ልሳን ዛሬ ገና በማደግ ላይ የሚገኝ
አዲስ የቋንቋ ሳይንስ ነው ። የሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ በአንድ በተወሰነ
ሥፍራና ጊዜ በሚገኙ ቋንቋዎች መካከል በድምጽ ፤ በቃላት ፤ በአረፍተ
ነገር ምስረታና በአጠቃላይ የቋንቋን ውስጣዊ ባህሪ በመመርመር በቋ
ንቋዎች መሀል የሚታየውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በማስረዳት እነ
ዚህን ቋንቋዎች በሚናገሩ ሰዎች መካከል በሥፍራና በጊዜ የነበረውንና
ያለውን ታሪካዊ ግንኙነት በአጠቃላይ መንገድ የሚያሳይ የትምህርት
ጥበብና ዘዴ ነው ።

በዚህ አኳያ ለምሳሌ የዘመናችን ታዋቂ የሊንጉዊስቲክ ምሁራን
በሕዝቦች መካከል ያለውን ሊንጉዊስቲካዊ ፤ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነት
በማጥናት በአያሌ መቶ የሚቆጠሩ የሰሜን ፤ የምዕራብና የምስራቅ አፍ
ሪካ ጥንታዊና ዘመናዊ ቋንቋዎችን “ የአፍሮ - እስያ ቋንቋዎች ”በሚል
ጥቅል ስያሜ የጥንታዊ ግብጽ ፤ የበርበር ፤ ቻዳዊ ፤ ናይሎ - ሳራዊ ፤ አሞ
አዊ ፤ ኩሻዊና ሴማዊ ቋንቋዎች በማለት በብዙ ጂኦግራፊያዊ ፤ ባህላዊና
ታሪካዊ አካባቢዎች መድበው በአፍሪካ ሕዝቦችና ቋንቋዎች መካከል
ከጥንት ጀምሮ ለብዙ ሺህ ዓመታት የነበረውንና ያለውን አህጉራዊ የዘ

[4] G. W. B. Huntingford, tr.and ed., *The Glorious Victories of AmadaSeyon King of Ethiopia* (1965); Ibn Fadl A. Omari, *Masalikel Absar fi Mamalik el Masar*,tr. and ed.by G. Demombynes (1927); Maqrizi, *The Book of the True Knowledge of the Moslem Kings in Abyssinia*,tr. by G. W. B. Huntingford (Typescript 1955); J. Perruchon, tr.and ed., *Les Chroniques de ZaraYaeqob et de Baeda Maryam* (1813); Arab-Faqih, *Histoire de la Conquete de L'Abyssinie*, tr. and ed.by R. Basset (1897); Bahrey, *History of the Galla* in C. F. *Beckingham and* G. W, B. *H*untingford, trs and eds., *Some Records of Ethiopia* 1593-1646 (1954); *Historia Regis Sara Dengll* 1563-1597, tr and ed., C. Rossini (1907);

ተክለ ሥላሴ ፤ <u>የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632</u> (ያልታተመ ዜና መዋዕል
ቡብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት አዲስ አበባ) ።



ርና የባህል ግንኙነት በአጠቃላይ መልኩ ያሳያሉ።[5] ዛሬ ከእነዚህ ከአፍሮ
እስያዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች በተለይ ኦሞአዊ ሙሉ በሙሉ፤
ኩሻዊና ሴማዊ በአብዛኛው ናይሎ - ሳራዊያን ደግሞ በከፊል የሚገኙት
በኢትዮጵያ ምድር ነው ።

በዚህ በኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ብዛትና አን
ድነት ነገር ፤ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በግምት ከ1890 እስከ 1960
ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ የምዕራብ በተለይም የጀርመንና የኢጣሊያን
ምሁራን የአገሪቱን ስምንቱን ሴማዊ የግዕዝ ፤ የትግረ የትግራይ ፤ የአማራ
የአደሬ ፤ የጉራጌ ፤ የአርጎባና የጋፋት ቋንቋዎችንና ማህበረሰቦችን የእ
ስተያየታቸው መነሻ በማድረግ በ500 ዓመተ ዓለም አካባቢ በአፍሪካ
ቀንድ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ መካከል የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክ
ሱማውያንን ከፍተኛ መንግሥትና ሥልጣኔ “ የፈጠሩት ” ከአረቢያ
ቀይ ባህርን ተሻግረው የመጡ “ ሀበሻ ” እና “ ዓጋዚያን ” የሚባሉ
ሁለት ሴማዊ ነገዶች ናቸው የሚል መላምት ቲሲስ ማስተማራቸው ይታ
ወሳል ። ይህን ቲሲስ ከአስተማሩ የምዕራብ ምሁራን የኢጣሊያኑ
ኮንቲ ሮሲኒ (1872-1949) እና የጀርመኑ ኢኖሊትማን ( 1875-1958)
በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀሱ ናቸው ። [6]

ይሁን እንጂ አሁን ከ1950ዎቹ ወዲህ የዘመናችን ከፍተኛ የሊንጉዊ
ስቲክስ ሳይንስ በትክክል እንደሚያስተምረን “ ሴማዊ” ሕዝብና ቋንቋ
በጥንታዊ አረቢያ ከመገኘቱ በፊት በአፍሪካ ቀንድ ቢያንስ የሁለት ሺህ
ዓመታት ቅድሚያ ነበረው ።[7] በሌላ አባባል ፤ ዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስ
ሳይንስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ብሔረሰቦች መካከል የነበረውንና ያለውን
ጥንታዊ ፤ ታሪካዊና ባህላዊ አንድነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብና
ሥልጣኔ ምንጩና መሠረቱ የአፍሪካ ምድር መሆኑን ጨምሮ በትክክል
የሚያስተምረን የምርምር ዘዴና ጥበብ ነው ።

በመጨረሻም ዛሬ ዘመናዊ የምርምር ዘዴና ጥበብ በደረሰበት የዕ
ድገት ደረጃ <u>ትውፊት</u> ማለትም <u>አፈ ታሪክ</u> በምሁራን ዘንድ ከጽሑፍና
ከቋንቋ መረጃዎች ጋር አብሮ የሚቆጠር የትምህርትና የእውቀት ምንጭ

[5] J.H. Greenberg, *Africah Linguistic Classifican in* UNESCO, General African History, 8 vols (1981), I, pp. 292-308; M.L. Bender, The Ethiopian Nilo-Saharans (1975).

[6] E. Littmann, *Sabaische, Griechische Und Altabessinische Inschriften* in *Deutsche Aksum-Expedition Book IV* (1913); Conti Rossini. “ Expeditions et possessions des Habasat en Arabie, ” *Journal Asiatique*, ser. 18 (1921); E. Ullendorff, *The Semitic Languages of Ethiopia*(1955).

[7] D.N. Levine, *Greater Ethiopia* (1974), pp. 19-31; G. Husdon, “Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory, *Abbay*, ” No. 9 (1978). pp. 71-72.

ሆኖአል ። በመሆኑም በዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ሦስቱም ማለትም የጽሑፍ ፣ የትውፊትና የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎችና መጣሪያዎች በእነ ልግሎት ላይ ውለዋል ።

## 3. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ አካባቢ

የኢትዮጵያ ምድር የአፍሪካ እምባና የውሃ ጋን ነው ። በአፍሪካ ቀንድ የምትገኘው ኢትዮጵያ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ መካከል ከምድር ወገብ በላይ በግምት ከ3 እስከ 18 ዲግሪ ሰሜናዊ ላቲትዩድና ከ33 እስከ 48 ዲግሪ ምስራቃዊ ሎንግቲዩድ ክልል ውስጥ ሲሆን ፣ የአገሪቱ ከሰሜን እስከ ደቡብና ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ጫፍ ድረስ ያለው ርዝመት ተመሳሳይ ሆኖ ይኸውም በአጋዝ 15 ዲግሪ ወይም 1660 ኪሎ ሜትር ነው ።

ታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የኢትዮጵያን ምድር በሰሜን ምዕራብና በደቡብ - ምስራቅ የተራራ ሰንሰለቶች ሲከፍል በውስጡ ወደ ውጭ አገር የማይፈሱ ታላላቅ የዝዋይ ፣ የላንጋኖ ፣ የሻላ ፣ የአባያታ ፣ የአዋሳ ፣ የአባያ ፣ የጫሞና የቱርካና ሐይቆች ከታላቁ አዋሽ ወንዝ ጋር ይገኙበታል ።

በታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በሁለት የተራራ ሰንሰለቶች የተገመሰው የኢትዮጵያ ምድር ከፍታው ከባህር ጠለል እስከ 4543 ሜትር ይደርሳል ። የአገሪቱ ከፍተኛው ስፍራ በሰሜን ምዕራብ የራስ ደጀን ተራራ ሲሆን የእሱም ከፍታ ከባህር ጠለል ወደ ላይ 4543 ሜትር ነው ። ዝቅተኛው ስፍራ ደግሞ በሰሜን ምስራቅ በቀይ ባህር አጠገብ የዳሎል ስምጥ ሸለቆ ቦታ ሲሆን የእሱም ዝቅታ ልክ ከባህር ጠለል ወደታች 116 ሜትር ነው ።

በኢትዮጵያ ከባህር ጠለል ወደ ላይ ከፍታው በአማካይ እስከ 2000 ሜትር የሚደርሰው ስፍራ ዝቅተኛው ወይም ቆላማው አካባቢ ነው ። ከፍታው ከባህር ጠለል በአማካይ ከ2000 ሜትር በላይ የሆነው ሥፍራ ደግሞ ከፍተኛው ወይም ደጋማው አካባቢ ነው ። ከቅርብ ጊዜ በፊት በአንድ ጥናት እንደተመለከተው ፣ ከኢትዮጵያ ጠቅላላ 1,250,282 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት 769,000 ወይም 61 በመቶ ቆላማው መሬት ሲሆን ፣ 482,282 ወይም 39 በመቶ ደጋማው መሬት ነው ።[1]

[1] United Nations, Development Programme, *A study of Nomadic Areas for Settlement*, Part I,II, III (RRC: Addis Ababa, 1983), II, pp. 2-3.



በ1986 ከኢትዮጵያ ጠቅላላ 46 ሚሊዮን ሕዝብ 43 ሚሊዮን ወይም 93 በመቶ የሚሆነው ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት በ482,282 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 39 በመቶ በሆነ ደጋማው መሬት ላይ ብቻ በግብርና ፣ በእንስሳት እርባታ ፣ በዕደ ጥበብና በንግድ ተግባራት ተሰማርቶ ሲኖር ፣ 3 ሚሊዮን ወይም 7 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት በ769,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 61 በመቶ በሆነ ሰፊ ቆላማው መሬት ላይ በዘላንነትና በአዳኝነት ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ እንደሚኖር ታውቋል ።[2]

በኢትዮጵያ ደጋማው ክልል የዓመቱ የዝናብ መጠን በአማካይ ከ700 እስከ 2000 ሚሊሜትር ፣ በቆላማው አካባቢ ደግሞ በአማካይ ከ 500 እስከ 2000 ሚሊ ሜትር ይደርሳል ። በደጋማው አካባቢ የዓመቱ ወርሃዊ የዝቅተኛውና የከፍተኛው ሙቀት መጠን በአማካይ ከ13 እስከ 28 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ፣ በቆላማው አካባቢ ደግሞ ከ20 እስከ 28 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይደርሳል ።[3]

ከዚህ ከአገሪቱ ተጨባጭ ተፈጥሮአዊ የአየር ንብረት ሁኔታ የተነሳ በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ታላላቅ የሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች አቅጣጫ ከቆላማው ወደ ደጋማው አካባቢ ሆኖ ይታያል ። በመሆኑም በቆዳ ስፋት አነስተኛ የሆነው የኢትዮጵያ ደጋማውና ተራራማው መሀል አገር ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ የአገሪቱ የሕዝብ ፣ የባህል ፣ የመንግሥትና የሥልጣኔ መሠረትና ማዕከል ሆኖ መገኘቱ ከአገሪቱ ከተፈጥሮ ሁኔታ ጋር በቅርብ የተያያዘ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት ነው ለማለት ይቻላል ።

በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የኢትዮጵያ ምድር የአፍሪካ የውሃ ምንጭና ጋን ነው መባሉ ግልጽ ነው ። በዚህ እኳያ ከዓለም አቀፉ የቀይ ባህር ርዝመት ከ1000 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የጠረፍ ክልል ነው ። በመሀል አገር ታላላቅ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችና ወንዞች ከሰሜንና ከምዕራብ ተራራዎች የሚነሱ ታላላቅ የባርካ ፣ የጋሽ ፣ የተከዜ ፣ የመረብ ፣ የአባይ ፣ የጊቤ ፣ የዲዴሳ ፣ የጉጀብ ፣ የሶባት ፣ የባሮ የአኮቦ ፣ የኦሞ ወንዞችና ታላቁ የጣና ሐይቅ ከደቡብ ምስራቅ ተራራዎች ከሚፈልቁ ታላላቅ የዋቢ ሸበሌ ፣ የዳዋና የገናሌ ወንዞች ጋር የኢትዮጵያ ከፍተኛ የውሃ ሀብት ናቸው ።

ከሰሜንና ከምዕራብ ተራራዎች የሚፈልቁ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞች ከታላቁ ጣና ሐይቅ ጋር አገር አቋርጠው የሱዳንና የግብጽ አጐራባች አገሮችን በማለፍ ወደ ሜዲቴራኒያን ባህር ሲገቡ ከደቡብ ምስራቅ

[2] የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ፣ ጠረፍ አካባቢዎች (1978) ገጽ14 ።

[3] UNDP, *Nomadic Areas*, II, pp. 6-7.


ተራራዎች የሚፈልቁ ወንዞች ደግሞ የሶማሊያ አጐራባች አገር አቋር ጠው በሕንድ ውቅያኖስ የሚፈሱ ጅረቶች በመሆናቸው የኢትዮጵያ ወንዞች አገሪቱን ከአካባቢው አገሮች ጋር በኢኮኖሚ ፤ በባህልና በፖ ቲካ የሚያገናኙ ዓለም አቀፍ የሀብትና የሕይወት ምንጮችና የጂኦ ፖለቲካ ገጽታዎች ናቸው ለማለት ይቻላል ።

በአጭር አነጋገር ፤ የሰውን ልጅ መሠረታዊ የምግብና የሕይወት ጥያቄ በተመለከተ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት ጥንት ከእሳተ ገሞራ ፈሳሽ በቅዝቃዜ የተፈጠረ ጥልቅና ለም የአፈር ሀብት ያላት አገር ናት ።

4. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

በዘመናዊ የአርኪኦሎጂና የፓሊአንቶሎጂ ጥበብና ምርምር ፤

1. በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ ከሀደር የተገኘውንና እስከ አራት ሚሊዮን ዓመታት የተገመተ ዕድሜ ያለውን የጥንቱን ሰው አጽም ፤
2. ከኦሞ ወንዝ ዳርቻ የተገኘውንና እስከ ሦስት ሚሊዮን ዓመታት የተገመተ ዕድሜ ያለውን የጥንቱን ሰው የአጥንት መሣሪያ ፤
3. በደቡብ ሸዋ በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ ከመልካ ቁንጡሬ የተገኘውንና እስከ አንድ ተኩል ሚሊዮን ዓመታት የተገመተ ዕድሜ ያለውን የጥንቱን ሰው የድንጋይና የአጥንት መሣሪያ



ከአራት ሚሊዮን ዓመታት በፊት ሉሲ/ድንቅነሽ የመጀመሪያው ሰው አፅም ከሀደር አዋሽ ታሪካዊ ሥፍራ ።

በአንድነት በስፍራና በጊዜ በማገናዘብ ዛሬ የዓለም ታዋቂ ምሁራን



የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ በዓለማችን የሰው ልጅ የመነሻው ሥፍራ እን ደሆነ ወደ አንድ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት ደርሰውበታል ።[1]

ከእነዚህ እስከ ዛሬ ድረስ ለዓለም የሰውን ልጅ እውነተኛ ምንጭና ባህላዊ የዕድገት መነሻ ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል ከአሳዩት ከጥንታዊ የሀደር ፤ የኦሞና መልካ ቁንጡሬ ፓሌአንቶሎጂያዊ የድንጋይና የአጥንት መሣሪያ ሥፍራዎች ሌላ ፤በቅርቡ ቅድመ ታሪክ ዘመን የሰውን ልጅ ዘመናዊ የሆነ አብዮታዊ የመሣሪያ ፤ የምርት ፤ የአሳብ ፤ የባህልና የድር ጅት ዕደገት እምርታ የሚያሳዩ ብዙ በሰው እጅ ከድንጋይ የተሠሩ ጥን ታዊ የዋሻ ውስጥ ስዕሎችና የመቃብር ላይ ሀውልቶች ተገኝቷል ።[2]

በሐረርጌ በለጋ ኦዳ ዋሻ ድንጋይ ላይ በ3500 ዓመታት ዕድሜ ክልል የተገመተው ጥንታዊ የእንስሳትና የሰዎች ስዕል ፤ በሲዳሞ በሻቤ ዋሻ ድንጋይ ላይ በ3000 ዓመታት ዕድሜ ዘመን የተገመተው ተመሳሳይ የእንስሳት ስዕል ፤ እንዲሁም በሐረርጌ ፤ በአርሲ ፤ በሲዳሞና በደቡብ ሸዋ በየመንደሩና በየመንገድ ዳሩ ቁመውና ወድቀው በአካባቢው ነዋሪዎች በትውፊታዊ አባባል “ የአህመድ ግራኝ” ድንጋዮች እየተባሉ የሚጠሩ የረዥም ዘመን ዕድሜ ያላቸው ብዙ የመቃብር ላይ ትክል የድንጋይ ሀውልቶች



የረጅም ዘመን ዕድሜ ያለው የቅድመ ታሪክ ሀውልት ከጥያ ሸዋ

[1] UNESCO,*General History of Africa*, 8vols.(1981-88), I,pp.413,437.

[2] National Museum (Addis Ababa), "Historial Sites of Ethiopia," Written-docu ment, July 30,1985; F.Anfray, "Les Steles du sud Shoa st Sidams," *Amnales D Ethiopie*, No. 12(1982); R. Joussaume, *Lemegalithisme en Ethiopie: Monuwents Funeraires Proto-Historique du Harar*(1979).

ከተጠቀሱ ከኢትዮጵያ ብዙ የቅርብ ጊዜ ቅድመ ታሪክ ቅርሶች ጥቂቶቹ ናቸው ።

ከእነዚህ ጥንታዊ የመቃብር ላይ ሀውልቶች አንዳንዶቹ በተለይም በሐረርጌ ደጋማው ክልል የሚገኙ " ከርቦን-14 " በተባለው የትምህርት መግሪያ ተጠንተው በ4000 ዓመታት የሚገመት ዕድሜ እንዳላቸው ታውቋል ።[3]

በአፍሪካ ቀንድ በጽሑፍና በቅርጽ ዘገባ በስምና በአካላዊ መልክ ተቀርጸው በሥፍራና በጊዜ በትክክል የታወቁ የመጀመሪያ ሰዎች በ1500 ዓመተ ዓለም አካባቢ ማለትም ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ፑንታውያን ፤ በ500 ዓመተ ዓለም ገደማ ከዛሬ 2500 ዓመታት በፊት ደግሞ ደአማታውያን ናቸው ።

ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በ1500 ዓመተ ዓለም አካባቢ ፐረሁ በተባለ ንጉሥና አጢ በተባለች ንግሥት የሚገዙ ፤ በከተማና በገጠር የሚኖሩ በእርሻና በንግድሙያ የሰለጠኑና የተሰማሩ ፤ በሃይማኖት የተፈጥሮ አማልክት ፤ መቅደስና ካህናት የነበሩአቸው በጥንቱ ዓለም ታሪክ " ፑንታውያን" ተብለው የሚጠሩ ጥንታዊ ሰዎች በቀይ ባህር ምዕራባዊ ጠረፍ በዛሬው ኤርትራና ጂቡቲ አካባቢ እንደነበሩ ፤ የግብጽ ንግሥት ሃትሸፕሱት ( 1504-1482) አምስት የንግድ መርከቦች ወደ ምድረ ፑንት በላከችበት ጊዜ በአንድ መርከበኛ ተስሎ አሁን በምድረ ግብጽ በአንድ ጥንታዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ በሚገኘው የስዕል መረጃ በትክክል ታውቋል ።[4]

በዘመኑ ከምድረ ፑንት ወደ ግብጽ በሚላኩ የንግድ ዕቃዎች ዝርዝር የአፍሪካ ቀንድ ዕጣን ፤ ከርቤ ፤ ሙጫ ፤ ቀረፋ የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመም ፤ ወርቅ ፤ የቤት እንስሳት ፤ የአውራሪስ ቀንድ ፤ የዝሆን ጥርስ ፤ የተለያዩ የዱር አራዊቶች የሰጕን እንቁላልና ላባ ይገኙበታል ።

በዓመተ ዓለም በግምት ከ2800 እስከ 1300 ድረስ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በጥንታዊ ግብጽና ፑንት አገሮች መካከል ለረጅም ዘመን የቆየው የንግድና የባህል ግንኙነት ባልታወቀ ምክንያት ከተቋረጠ በኋላ በዓመተ ዓለም ከ1300 እስከ 332 ማለትም ግብጽ በግሪኮች እስኪተያዘበት ድረስ ለአንድ ሺህ ዓመታት በግብጽና

---

3 *Ibid.*, Monuments Funeraires, pp. 101-103.

4 J.Doresse, *Histoire Sommaire de la Corne Orientale de L Afrique* (1971), pp. 47-56; Pankhurst, *Economic Histor y*, pp.5-6.



በአፍሪካ ቀንድ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት እንደነበራቸው የሚያሳይ ታሪካዊ መረጃ እስከ ዛሬ ገና አልተገኘም ።

ይሁን እንጂ በጥንታዊ ግብጽና ፑንት መካከል የነበረው ግንኙነት ከሰነድ አኳያ በተቋረጠበት የሽግግር ዘመን በአካባቢው በተፈጥሮ አቀማመጥና በአየር ንብረት ከፑንት ምድር ጋር የቀረበ ግንኙነት ባለው በደቡብ አረቢያ ፤ እንደ ፑንትም በዕጣን ምርትና ንግድ የታወቁ ጥንታዊ ትንንሽ የሚናውያን ፤ የሳባውያን ፤ የካታባውያንና የሃድራማውን ባላባታዊ የጠረፍ ንግድ አገሮች ተነስተው ከግብጽ ፤ ከሚሶፖታሚያና ከሜዲትራንያን አገሮች ጋር በምዕራብና በሰሜን አረቢያ የሲራራ ንግድ መንገዶች አዲስ ግንኙነት እንደ ጀመሩ ታውቋል ።[5]

ይህ በደቡብ አረቢያ የተፈጠረው አዲስ የዕጣን ምርትና ንግድ በአፍሪካ አህጉር በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በግብጽና በፑንት አገሮች መካከል ለረጅም ዘመን በነበረው የንግድ ግንኙነት ላይ የውድቀት ተጽዕኖ እንዳሳደረበት መገመት ይቻላል ።

በሆኑ ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች በግብጽና በፑንት መካከል የነበረው ታሪካዊ ግንኙነት በዓመተ ዓለም ከ1300 አካባቢ ጀምሮ በ500 ገደማ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ መካከል በዛሬው ኤርትራ - ትግራይ ቀበሌ የኢትዮጵያ ጥንታዊው የደአማታውያን መንግሥትና ሥልጣኔ[6] እስኪነሳ ድረስ በአፍሪካ ቀንድ ታሪካዊ የሕብረተሰብና የመንግሥት ዕድገት ምን ይመስል እንደነበር ፤ ወይም በፑንታውያንና በደአማታውያን መካከል በሥፍራና በጊዜ በቋንቋና በባህል ምን ዓይነት ግንኙነት እንደነበረ የሚያሳይ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ገና አልተገኘም ።

ምንም እንኳን በዓመተ ዓለም በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በሰሜን ኢትዮጵያ በኤርትራ - ትግራይ ደጋማው ቀበሌ በዘውዳዊ ስርዓት ተደራጅቶ በሰነዳዊ መረጃ በታወቀው በደአማታውያን መንግሥትና በጥንታዊ ፑንታውያን መካከል በሥፍራና በጊዜ ፤ በቋንቋና በባህል የነበረውን ግንኙነት የሚያስረዳ ታሪካዊ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ባይገኝም በሚከተሉት አያሌ የውስጥና የውጭ ምክንያቶችና ማስረጃዎች ሁለቱም የፑንትና የደአማት ሕዝቦች በአንዱ አፍሪካ ቀንድ የአንዱ አዳጊ የዘውድ ሥርዓት ተከታታይ የዕድገት ደረጃዎችና ምዕራፎች እንደሆኑ መገመት ይቻላል ። በዚህ አኳያ ፤

---

5 "History of Arabia," *The New Encyclopaedia Britanica*, I, pp. 1043-44.

6 Schneider, "Les Debuts De L Histoire Ethiopia" pp. 53-54; R. Schneider, "Deux Inscriptions Sudarabique du Tigre," *Bibliotheca Orientale*, vol. 30, No.5-6 (1973), pp.385-89.

አንደኛ ፣ ከሁሉ በፊት ጥንታዊ የጥንትና የደአማት አገሮች በቅ
ደም ተከተል የተገኙበት የአፍሪካ ቀንድ አንድ አካባቢ ነው ። ሁለተኛ ፣
ከዘመነ ጥንት እስከ ዘመነ ደአማት ድረስ በአካባቢው የኢትዮጵያን ጥን
ታዊ የመንግሥት ዕድገት እንቅስቃሴና አቅጣጫ የሚያደናቅፍ ውጫዊ
ግፊት ወይም ውስጣዊ ተጽዕኖ መከሰቱን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ምክ
ንያት ወይም መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም ።

ሦስተኛ ፣ የደአማታውያን መንግሥትና ሥልጣኔ በዓመተ ዓለም
በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታውቆ በሰነድ
የተገኘበት ወቅትና ሁኔታ የመንግሥቱን ታሪካዊ መነሻ መቼና እን
ዴት እንደነበር ስለማያመለክትና አንድ መንግሥት በባህላዊና ማህበራዊ
ዕድገት በራሱ ፊደልና ጽሕፈት በከፍተኛ ደረጃ የታወቀበት ጊዜ ገና
የተፈጠረበት ዘመን ነው ተብሎ በዘልማድ ስለማይታሰብ ፣ በኢትዮጵያ
ረጅም ታሪክ የዘመነ ጥንት ፍጻሜና የዘመነ ደአማት ሽግግራዊ መነሻ
ቢያንስ ከ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ ጀምሮ እንደሆነ መገመት ከአግባብ
ውጭ አይሆንም ።

በዚህ በዘመነ ደአማት መነሻ ጥያቄ በኤርትራ ከመጠራና ከሰከሴ
በትግራይ ደግሞ ከየሀ ፣ ከሀውልቲ ፣ ከእንዳጭርቆስ ፣ ከአዲገለመና ከአ
ዲቀዋህ ጥንታዊ ከተሞች በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ጥበብና ጥናት የተገኙ
ብዙ ከሸክላ ፣ ከድንጋይና ከብረት የተሠሩ የምርት መሣሪያዎች የቤት
ዕቃዎች ፣ የጌጣጌጥ ፣ የሕንጻ ፣ የሀውልት ፣ የመቅደስ ፣ የቤተ መንግሥት
የዙፋን ፣ የመንግሥት አርማ ፣ የሕግ ፣ የፊደልና የጽሑፍ መረጃዎች [7]
ስልጣኔው በዓመተ ዓለም ገና በስድስተኛው ወይም በአምስተኛው ምዕተ
ዓመት በአዲስ የተፈጠረ ነገር ሳይሆን ከዚያ በፊት በራሱ ቋንቋ ፤ ኢኮ
ኖሚ ፣ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ አማልክት ፣ ካህናትና ነገሥታት በዘውዳዊ
ሥርዓት ተደራጅቶ ለረጅም ዘመን የኖረ አንድ ጥንታዊ አገር ፣ መንግሥ
ትና ሥልጣኔ እንደ ነበር በብቃት ይጠቁማሉ ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ስለ ጥንታውያንና ደአማታውያን ከውጭና
ከአገር ውስጥ የተገኙ ውሱን የጽሑፍ መረጃዎች በአፍሪካ ቀንድ ለዛ
ሬው በሀውርታዊ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ታሪካዊ መነሻና
መሠረት የሆኑ ጥንታዊ ሕዝቦችን በቂ ስዕል አያሳዩንም ። ዛሬ ይህን
ጥያቄ በአስተማማኝ ሁኔታና መንገድ የሚመልሰው ዘመናዊ የሊንጉ
ዊስቲክ መረጃና ሳይንስ ነው ።

---

7 F. Anfray, "Recherches Archeologiques en Ethiopie" *Academic Des Inscriptions et Belles-Letteres* (1978), pp.715-16.



በዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ በትክክል እንደታወቀው ፤ የኢ
ትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ዋና ምንጮችና መሠረቶች የአገሪቱ አራቱ ነባርና
ተዛማጅ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ናይሎቲካዊ ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ከአ
ራቱ የወጡና ከሰባ በላይ የሚቆጠሩ የቋንቋ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች
ናቸው ። በአገሪቱ ሰሜን የጥንቱ የጥንትና የደአማት ሰዎች ሆኑ በደቡብ
ጥንታዊ የዋሻ ስዕልና የመቃብር ላይ ትክል ሀውልት የሠሩ በስም የማይ
ታወቁ ጥንታዊ ሰዎች ሁሉ ከአራቱ የኢትዮጵያ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ናይሎ
ቲካዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ውጭ አይሆኑም ።

በአለፉት ብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ በተለይም ከዘመነ አክሱም
ወዲህ የኢትዮጵያ አራቱን ነባርና ተዛማጅ ኩሻዊ ፤ ሴማዊ ፤ ናይሎቲካ
ዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችንና ማህበረሰቦችን በሥፍራና በጊዜ አንድ
በሀውርታዊ የኢትዮጵያ አገርና ሕብረተሰብ ያደረጉ ዋና ዋና ኃይሎች
ሁኔታዎችና ሂደቶች ደግሞ ፣

1. በልዩ ልዩ ምክንያቶችና መንገዶች የተካሄዱ ታላላቅ የሕዝብ
   እንቅስቃሴዎች ፣
2. የኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ፣
3. የኢትዮጵያ ታላላቅ መለኮታዊ የጁዳይዝም ፣ የክርስትናና የእስ
   ልምና ሃይማኖቶች ናቸው ለማለት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ አንድነት የተገነባው በእነዚህ ታሪ
ካዊ ኃይሎች መስተጋብር እንደሆነ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት አግባብ
ባለው ሥፍራና ጊዜ በዝርዝር መረጃዎች ፣ ማስረጃዎችና ምሳሌዎች የበ
ለጠ ይብራራል ።

## 5. ኢትዮጵያና ዓለም

የኢትዮጵያ ታላቁ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የምስቱ ጥንታዊ የአፍሪካ ፣ የእስያና የአውሮፓ አህጉራትና ሕዝቦች የመገናኛ ጉዳናና ድልድይ በሆነው በቀይ ባህር እስትራቴጂያዊ ክልል በዘመነ ክርስትና የመጀመሪያ አንድ ሺህ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከዘመኑ ታላላቅ የአረቢያ ፣ የኑቢያ - ሚሮዌ ፣ የግብጽ ፣ የሮማውያንና የፋርስ ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር እንደ ዘመኑ ዓለም አቀፍ ሁኔታና አሠራር በንግድ ፣ በሃይማኖት ፣ በዲፕሎማሲና በጦርነት ጉዳዮች የቀረበ ጂኦፖለቲካዊ መስተጋብር የነበረው አንድ የአፍሪካ ኃያል መንግሥትና ሥልጣኔ ነበር ።


በመሆኑም የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት ከሥር መሠረቱ በትክክል ለማወቅ እንዲረዳን እነዚህ የተጠቀሱት ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት በሙሉ ወይም በከፊል በየዘመኑ ከኢትዮጵያ ተከታታይ መንግሥታት ጋር እንዲሁም በእርስ በርሳቸውም መካከል የነበሩአቸውን ጂኦፖለቲካዊ ግንኙነቶች በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ስፍራና ጊዜ ማገናዘብ የማይታለፍ የይዘትም የስልትም ጥያቄ ነው ።

የዓለምን ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ በተመለከተ ፤ በታችኛውና በላይኛው የአባይ ወንዝ ዳርቻ ግብጻውያንና ኑቢያውያን በመካከለኛው ምስራቅ በታይግረስና በኤፍራጥስ ወንዞች አካባቢ ማለትም በሜሶፓታሚያ ባቢሎናውያን ፤ አሴሪያውያንና ፋርሶች ፤ በደቡብ ምስራቅ አውሮፓ በኤጂያን ባህር አጠገብ ግሪኮች ፤ በአረቢያ ሳባውያን ፤ በደቡብ አውሮፓ በሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ ደግሞ ሮማውያን በመጀመሪያ ረድፍ የሚጠቀሱና በየዘመናቸውና በየአካባቢያቸው በግዛትና በኃይል ሚዛን ጉዳይ እርስ በርሳቸው ሲዋጉ በፈረቃ ያለፉ ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ናቸው ።

ከእነዚህ በ3100 አመተ አለም አካባቢ በታላቁ ሚነስ ከሜንፈስ መዲናው በአንድ ዘውዳዊ መንግሥት ስር ከማደራጀቱ በፊት ጥንታዊ ግብጽ የቦስቱ የአፍሪካ ፤ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት የመገናኛ ድልድይ በሆነው ምድር ማለትም በሜዲትራኒያን ባህር በፍልስጤም በሲናበረሃና በአባይ ወንዝ የመጀመሪያው ፏፏቴ መካከል “ የታችኛው ግብጽና የላይኛው ግብጽ” ተብሎ ለረጅም ዘመን በሰሜንና በደቡብ በሁለት የተከፈለ የብዙ መሳፍንቶችና አማልክቶች አገር ነበር [1] ።

---

[1] Chancellor Williams. *The Destruction of Black Civilization: Great Issues of A Race from 4500 B.C. To 2000 A.D.*




የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦች ስርጭትና ስብጥር

በባርያ በገበሬ በዕደ ጥበብ ሙያተኛ በወታደር በቄስ የተገነባ አስደናቂ የጥበብ ስራው በሃይሮግላፊክስ ጽሁፍ ፣ በግዙፍ የአማልክት መቅደሶችና በነገሥታት ፒራሚዶች ተቀርጾ በታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ የታወቀለት የጥንቱ ግብጽ የአፍሪካ የእስያና የአውሮፓ ሕዝቦች የመገናኛ ድልድይ ሆኖ በዓመተ ዓለም ከ3100 እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በ38 ምዕተ ዓመታት ፣ ከውስጥ ዲናስቲዎች ማለትም ሥርወ መንግሥታት ተብለው በሚጠሩና በፈረቃ በተነሱ በቁጥር ከ30 በላይ የነገስታት “ ዘሮች” እና ከውጭ ደግሞ በዓመተ ዓለም በግምት ከ1720 እስከ 1220 በሃይክሶስ ፤ ከ730 እስከ 656 በኑቢያ ፤ ከ656 እስከ 525 በአሴሪያ ከ525 እስከ 404 በፋርስ ፤ ከ332 እስከ 30 በግሪክ ፤ ከ30 ዓመተ ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ እንዲሁም በሮማውያን ወራሪዎች ሲገዛ ኖሮ ፤በመጨረሻም ከ642 ወዲህ በአረብና በቱርክ ወራሪዎች እጅ የወደቀው አንድ ጥንታዊ አገርና ስልጣኔ ነው ።

በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ስፍራና ጊዜ ሁሉ እንደተገለጸው ፤ እነዚህ የግብጽ ነገሥታትና ወራሪዎች በሙሉ ወይም በከፊል እንደ የዘመኑ የዓለም ሁኔታና አሠራር በየዘመኑ ከተነሱ የኢትዮጵያ መንግሥታት ጋር በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ በሮች በንግድ በሃይማኖትና በባህል የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው

በጥንትና በመካከለኛ ዘመናት የዓለም ታሪክ “ ኩሽ” ፤ “ ኢትዮጵያ ” ፤ “ ኑቢያ ” ፤ “ ናፓታ ” ፤ “ ሜሮዌ” ፤ “መኩሪያ ”፤“አልዋ” እና “ ፋንጅ ወይም ስናር ” ተብለው በብዙ ስሞች የሚታወቁ ሕዝቦችና አገሮች[2] በግምት ከ3000 ዓመተ ዓለም እስከ 1820 ዓመተ ምህረት ድረስ በአርባ ስምንት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በአባይ ሸለቆ ከሰሜን በአስዋን አጠገብ ከአባይ ወንዝ የመጀመሪያው ፏፏቴ አንስቶ በደቡብና በምሥራቅ እስከ የአክሱማውያን ኢትዮጵያ ጠረፍ ድረስ ባለው ምድር በየጊዜው በፈረቃ የተነሱ ልዩ ልዩ አጐራባች የአፍሪካ አገሮችና መንግሥታት ናቸው ።

ከእነዚህ “ኩሽ” ፤“ኑቢያ” እና “ናፓታ” ለተጠቀሱት ሕዝቦችና አገሮች የጥንታዊ ግብጻውያንና ሴማውያን ልዩ ልዩ ስሞች ናቸው ። ግሪኮች ግን የተጠቀሱትን ጨምሮ ከግብጽ በታች የሚገኙ የጥቁር አፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን በሙሉ “ ኢትዮጵያ ” እና “ ኢትዮጵያውያን ” በማለት በወል ይጠሩ እንደነበር ይታወሳል ። “ ሜሮዌ ” ለጥንታዊ ኑቢያ በኋላ የግሪኮች የሮማውያንና የአክሱማውያን ስም ነው ። “ መኩ

2 -Ibid; pp. 59-60; R. I. Rotberg, *A political History Tropical Africa*, (1965) pp. 5-12



ሪያ ” ፤ “ አልዋ ” እና ፋንጅ” ወይም “ ስናር ” ደግሞ በኋላ የተነሱ ምስት የአካባቢው ንዑስ መንግሥታት ናቸው ።

ከጊዜው በኋላ በጦርነት ፣ በሃይማኖትና በንግድ በአካባቢው የተስፋፉት አረቦች የተጠቀሱ አጐራባች የአፍሪካ አገሮችን “ ሱዳን ” በሚል አዲስ ስም መጥራት ጀመሩ ። “ሱዳን” ወይም “ብላድ አስሱዳን” የሚለው ቃል ራሱ ደግሞ ለጥቁር አፍሪካ ምድርና ሕዝብ ከአረቦች በወል የተሰጠ ስም ነው ። ባጭሩ የግሪኮቹ “ ኢትዮጵያ ” እና የአረቦቹ “ ሱዳን” ሁለቱም በየበኩላቸው ለጥቁር አፍሪካ ምድርና ሕዝቦች የወል ስሞች እንደሆኑ ማጤን ተገቢ ነው ።[3]

በዓመተ ዓለም ከ2700 እስከ 950 ድረስ ኩሽ - ነቢያ የግብጻውያን ገባር አገር ነበር ። በኋላ ግን በዓመተ ዓለም ከ730 እስከ 565 ድረስ ግብጽ ራሱ ለኑቢያ ነገሥታት ገባር ሆነ ። በ30 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ግብጽን ከግሪኮች ከያዙ በኋላ በሰሜናዊ ኑቢያ - ሜሮዌ ላይ ለተወሰነ ጊዜ የመስፋፋት ፖሊሲ መውሰዳቸው ታውቋል[4] ። በመጨረሻም በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ የአካባቢው የኖባ ዘላን ሕዝቦች ግብጽን ከሚገዙ ሮማውያን ጋር የጥቅም ህብረት ፈጥረው ለሜሮዌ መንግሥትና ስልጣኔ ውድቀት ወሳኝ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ተረጋግጧል[5] ። ከዚያ በኋላ በላይኛው አባይ ሸለቆ ሁለቱም ሚሮዌና ኖባ በአክሱማውያን የአጼው በሀውርታዊ መንግሥት ስር ሆኑ ።[6]

በዓመተ ዓለም ከ332 ጀምሮ የግብጽ በግሪኮችና በሮማውያን ስር መሆን በአንድ በኩል ለደቡብ አረቢያና ለሜሮዌ መንግሥታት ውድቀት በሌላ በኩል ግን በአካባቢው ዓለም ማለትም በአፍሪካ ቀንድ በቀይ ባህር በላይኛው አባይ ሸለቆና በአረቢያ ለአክሱማውያን መንግሥት አለም አቀፍ ዕድገትና መስፋፋት አንድ ውጫዊ አስተዋጽኦ አደረገ ።

በዚህ ረገድ በ332 ዓመተ ዓለም በታላቁ እስክንድር መሪነት የግሪክ ጦር ግብጽን ከፋርሶች ወስዶ ከያዘና በታላቁ እስክንድር ስም የእስክንድሪያ መዲና ከተቆረቆረ በኋላ በሚቀጥሉት 300 ዓመታት በግብጽ ምድር ላይ ቶለማውያን ( Ptolemaic Kings ) የተባሉ የግሪክ ነገሥታት ተነሱ ። የቶለማውያን ነገሥታት በዘመኑ በእጣን ምርትና ንግድ በዓለም ታዋቂ የነበረውን ደቡብ አረቢያን ከጐን በመተው ለንግድና ለአደን

3 *Ibid; Tropical Africa*, pp. 5-9
4 P. L. Shinnie, Meroe: *A Civilization of the Sudan* (1967), pp. 45-48.
5 *Ibid*; p. 56.
6 *Ibid*; pp. 52-56.

ተግባራት ትኩረታቸውን በአፍሪካ ምድር በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ ሰላጤ ጠረፎች ላይ ማድረጋቸው ታውቋል ።[7]

በዚህ ሁኔታና ወቅት በቀይ ባህር ዳርቻ የኢትዮጵያ የአዱሊስ ወደብ በሜድትራኒያን ባህርና በህንድ መካከል የተስፋፋው ዓለም አቀፍ ንግድና ባህል ኬላና መናኸሪያ በመሆን አደገ ። በአጭሩ በዚህ የሽግግር ዘመን በአክሱማውያን በግብጻውያንና በግሪኮ-ሮማውያን መካከል በንግድ በባህልና በሃይማኖት በተለይ የጠበቀ ግንኙነት ተፈጠረ ። የአክሱማውያን መንግሥት በአካባቢው በራሳቸው ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች የውድቀት ዕድል በአጋጠማቸው በሜሮዌና በአረቢያ ላይ በንግድና በፖለቲካዊ ጉዳዮች የራሱን ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው የዘመኑ ታሪክ ያስተምረናል ።

በ30 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ግብጽን ከግሪኮች ከያዙ በኋላ በዘመኑ በመካከለኛው ምስራቅ ኃያል ከነበረው ከፋርሳውያን የአጼ መንግሥት ጋር በንግድና በኃይል ሚዛን ጉዳይ ዓለም አቀፍ ትግል እንደነበራቸው ይታወሳል ። በተጨማሪም በአካባቢው የአፍሪካ ምድር ማለትም በቀይ ባህርና በላይኛው የአባይ ሸለቆ ክልል የቢጃና የኖባ ዘላኖችና ወንበዴዎች በሮማውያን ንግድና ይዞታ ላይ በየጊዜው አደጋ ማድረስ ጀመሩ ። በመሆኑም ሮማውያን በአካባቢው በፋርሳውያን በኖባውያንና በቢጃውያን ላይ ከአክሱማውያን ጋር የጋራ ጥቅምና ስምምነት እንደነበራቸው ታውቋል ።[8]

ከዚህ በላይ በአጭርና በጥቅል በቀረቡ ዓለም አቀፍ ታሪካዊ ሁኔታዎችና ሂደቶች ነበር የኢትዮጵያ የአክሱማውያን በሀውርታዊ መንግሥት በንግድና በኃይል ሚዛን ጉዳዮች ከዘመኑ የሮማውያንና የፋርሳውያን ኃያላን መንግሥታት ጋር በብቃት እየታገለ በአካባቢው የአፍሪካ ቀንድ፣ የቀይ ባህር ፣ የደቡብ አረቢያና የላይኛው አባይ ሸለቆ የበላይ ኃይል በመሆን ያደገውና የተስፋፋው ።

በኋላ ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፣ ሉአላዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት ከአረብ ፣ ከቱርክና ከአውሮፓ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር የሚኖረው ጂኦፖለቲካዊ መስተጋቢር አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ከዚህ በታች ይታያል ።

7 Doresse, *Historie Sommaire*, pp. 66-67.
8 Y.M. Kobishchanov, *Axum* (1979), pp.36-37.



## 6. የጂኦፖለቲካ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ በጥንት ዘመን

በአጭር አነጋገር ፣ ጂኦፖለቲካ የአንድ አካባቢ ወይም አገር የጅኦግራፊያ የእስትራቴጂ ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መስተጋብርና መገለጫ ነው ። በዚህ አኳያ በእስትራቴጂያዊው አፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ብሔራዊ ሕልውና ፣ ሕይወትና ነጻነት ከሁለቱ ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ ነው ። በኢትዮጵያ ታሪክ ለቀይ ባህርና ለአባይ ሸለቆ ጠረፎችና ወሰኖች ወሳኝ ሚና የሰጡ ጅኦግራፊያዊ ፣ አካባቢያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ እስትራቴጂያዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ብዙ ናቸው ። ከእነዚህም መካከል ፣ ደራሲው ከአሁን በፊት በአንድ ሌላ አጋጣሚ እንደአለው ፣

" 1ኛ፣ የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ጠረፎችና ወሰኖች ኢትዮጵያን ከውጭ ዓለም ጋር የሚያገናኙ በሮችና ድልድዮች ናቸው ።

" 2ኛ ፣ ሁለቱም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠረፎችና ወሰኖች ከጥንት ጀምረው የአገሪቱ ዋና የንግድ መግቢያና መውጫ በሮች ናቸው ።

" 3ኛ ፣ ሁለቱም የባዕዳን ወረራ በሮች ናቸው ።

" 4ኛ ፣ በሁለቱም ታሪካዊ ጠረፎችና ወሰኖች አማካይነት ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ ከአካባቢው የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች ጋር የቆየና የጠበቀ ባህላዊና ታሪካዊ ግንኙነቶች መሥርታለች ።

" 5ኛ ፣ ከዚህም የተነሳ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ጠረፎችና ወሰኖች ዓለም አቀፋዊ ሰላምና እጥታ መፈለግ ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ቋሚ ዓላማና ተግባር መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል ።[1]

በዚህ ረገድ በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1300 ድረስ ለ1500 ዓመታት ጥንታዊ ግብጻዊያን በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በመርከብና በሲራራ ነጋዴዎች አማካይነት በአፍሪካ ቀንድ ከጥንታዊው ፑንት " የሀበሻ ፣ የአግልክትና የቅመማቅመም "[2] አገር ጋር የረጅም ዘመን ግንኙነት እንደነበራቸው ይታወሳል ።

በዓመተ ዓለም መጨረሻ አምስት ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ዶአማታውያን አገርና መንግሥት ከአረቢያ ጋር በሃይማኖት

1 ላጵሶ ድሌቦ ፣ " የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ ፣ የምጽዋ ሲምፖዚየም ( ጥር 1974) ፣ ገጽ 22-23 ።
2 Doresse, *Histoire Sommaire*, p.51.

በንግድና በባህል የቀረበ ሉአላዊ ግንኙነት እንደነበረው በደአማትና በሳባ ቋንቋዎች በተጻፉ የዘመኑ ዜና መዋዕሎች ተመልክቷል ።

በዚህ ነገር ከደአማት ነገሥታት አንዱ የነበረው የረበሀ ልጅ " ድል አድራጊው " ንጉሥ ለመነ ለዝክረ አማልክት በጻፈው ዜና መዋዕሉ ራሱን " የደአማታዎያን ፤ የሳባውያን ፤ የአበራውያን የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ " አገሩን ደግሞ " ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ "[3] በማለት ከዛሬ 2500 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፤ ሉአላዊና በሀውርታዊ መንግሥት በአረቢያ ከሳባውያን ጋር የነበረውን የቀረበ ግንኙነት አመልክቷል ።[4]

በዓመተ ዓለም ከ332 እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በድምር ለ970 ዓመታት ግብጽ በግሪኮችና በሮማውያን ሥር እንደነበር ይታወቃል ። በዚህ ወቅት ግሪኮ - ሮማውያን ከግብጽ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ የንግድ በሮችና መስመሮች በአፍሪካ ቀንድ ከጥንታዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በንግድ ፤ በሃይማኖትና በባህል የቀረበ ሉአላዊ ግንኙነት እንደነበራቸው በአክሱማውያን ዘመን የግሪክ ቋንቋና የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት መገኘትና መስፋፋት አንድ ታሪካዊ ማስረጃ ወይም ምሳሌ ነው ።

የኢትዮጵያ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣን የሦስቱ የአፍሪካ ፣ የእስያና የአውሮፓ አህጉራትና ሕዝቦች የመገናኛ ጐዳናና ድልድይ በሆነው በቀይ ባህር እስትራቴጂያዊ ክልል በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ ምዕተ ዓመታት ከዘመኑ ታላላቅ የአረቢያ ፤ የኑቢያ - ሚሮዊ ፤ የግብጽ የግሪክ ፤ የሮማውያንና የፋርስ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር በልዩ ልዩ መስኮች ፤ መንገዶችና ወቅቶች የቀረበ ዓለም አቀፍ ግንኙነት እንደ ነበረው ይታወሳል ። በዘመኑ በተለይ በአክሱማውያን በግብጻውያንና በግሪክ ሮማውያን መካከል በንግድ ፤ በባህል ፤ በቋንቋ ፤ በሃይማኖትና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች የጠበቀ መስተጋቢር ነበር ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ፤ በዚህ ወቅት የአክሱማውያን መንግሥት በአካባቢው በራሳቸው ውስጣዊ ቅራኔዎች ከውጭ እንዲሁም በግሪኮ- ሮማውያን ዓለም አቀፍ ግፊት የውድቀት ዕድል በአጋጠማቸው

[3] Schneider,''Inscriptions Sudarabiques,p. 387.

[4] በረጅም ጊዜ ጥናትና ምርምር በዘመናችን የደአማትን ሥልጣኔ ለዓለም በትክክል ያሳወቁት ታዋቂው ምሁር አር ሽናይደር እንደ ተረጐሙት ፤ በዚህ በንጉሥ ለመነ ዜና መዋዕል የተጠቀሱት "ሳባውያን" ከአካባቢው የሳባ አገር በስፈራ ይሁን በቅጥር ወይም በስነዱ ውስጥ በወል ባልተብራራ ተግባር መጥተው በአገሩ በደአማት መንግሥት ሥልጣን ስር የሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች ወይም ገባሮች ነበሩ ።



በሚሮዌና በአረቢያ ጥንታዊ አገሮች ላይ በንግድ ፤ በግዛትና በፖለቲካ መስኮችና መንገዶች የራሱን የተጽዕኖ ክልሎች በመፍጠር አራቱን አጐራባች የአፍሪካ ቀንድ ፤ የቀይ ባህር ፤ የአረቢያና የአባይ ሸለቆ አገሮችንና ሕዝቦችን በአንድ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ስር አደረገ ።

የዘመኑ የአካባቢው ዓለም አቀፍ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ በዝርዝር ሲጤን ፤ በ30 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ግብጽን ከግሪኮች ከያዙ በኋላ በዘመኑ በመካከለኛው ምስራቅ አንድ ኃያል አገር ከነበረው ከፋርሳውያን የአጼ መንግሥት ጋር በንግድና በኃይል ሚዛን ጉዳዮች በኃይል ተጋጩ ።

በተጨማሪም በአፍሪካ አህጉር በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ክልል ኃይለኛ የነበሩ የቤጃና የኖባ ዘላን ማህበረሰቦች በሮማውያን ግዛትና የንግድ መስመሮች ላይ በየጊዜው ጉዳት ማድረስ ጀመሩ ። በመሆኑም ሮማውያን ከግብጽ ይዞታቸው በአባይ ሸለቆ ፤ በቀይ ባህርና በአረቢያ አካባቢዎች በፋርሳውያን ፤ በቤጃውያንና በኖባውያን ተጻራሪዎቻቸው ላይ ከአክሱማውያን የአጼ መንግሥት ጋር ዓለም አቀፍ የጋራ ጥቅምና ስምምነት ነበራቸው ።

ባጭሩ የኢትዮጵያ የአክሱማውያን ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት ፤ ማኒ (216-276) የተባለው ፋርሳዊ ጸሐፊ በዘመነ ክርስትና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት እንዳስቀመጠው ፤[6] ከሮማውያን ፤ ከፋርሳውያንና ከቻይና የአጼ መንግሥታት ጋር ተቆጥሮ ፤ ከዘመኑ የዓለም አራቱ ኃያላን የአጼ መንግሥታት አንዱ ፤ በአካባቢው ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባህር ፤ የላይኛው አባይ ሸለቆና የአረቢያ የበላይ መንግሥትና ዓለም አቀፍ ሥርዓት ሆኖ ለማደግና ለመስፋፋት ችሏል ።

በዚህ ረገድ በቴዎሪም በተግባርም መንግሥትና ሥልጣኔ ሁለት በቅርብ የተያያዙ ነገሮች ናቸው ። መንግሥት በሰፊ ትርጉም በአንድ በተወሰነ ስፍራና ጊዜ የአንድ የተወሰነ መሬት ፤ ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ድርጅታዊና ሕጋዊ አንድነትና ትስስር ነው ። ከሶስቱ መሠረታዊና አስፈላጊ አካላት አንዱ እንኳን ባይኖር ወይም ቢጐድል በቴዎሪም በተግባርም መንግሥት የሚባል ድርጅትና አሳብ አይኖርም ። በሌላ በኩል ደግሞ በመሬት ፤ በሕዝብና በፖለቲካ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንጅትና ድርጅት የሚፈጥረው የመንግሥት ሥርዓት የሰለጠነም ያልሰለጠነም ሊሆን ይችላል ።

[5] Kobishchanov, *Axum*, pp. 36-37.

[6] *Ibid.*, p. 59.

በተግባራዊ ትርጉም ሥልጣኔ የከተማና የገጠር ተግባራት ዕድገትና ክፍፍል ፤ የእርሻና የንግድ ተግባራት ፤ የግል መሬት ይዞታ ፤ የጽሕፈትና የገንዘብ አገልግሎት የመለያ ገጽታዎች የሆኑበት አንድ ባህላዊ የህብረተሰብ ሥርዓት ወይም የዕድገት ደረጃ ነው ። በዚህ አጭር ትርጉም መንግሥት የሥልጣኔ መሠረትና ቅድመ ሁኔታ ነው ። ሥልጣኔ ግን የመንግሥት ገላጭ ባህርይ አይደለም ። መንግሥት የአንድ የተወሰነ መሬት ፤ ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ቅንጅት ሲሆን ሥልጣኔ ግን አንጻራዊ ባህላዊና ማህበራዊ የዕድገት ደረጃ ነው ።

በመሆኑም የተጠቀሱ የሥልጣኔ ገጽታዎች ቢኖሩም ባይኖሩም በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ በተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ቅንብርና ቅንጅት የሚፈጠር የመንግሥት ድርጅትና ሥርዓት በእርግጥ ሊኖርና ሊሠራ ይችላል ። ስለዚህ የሥልጣኔ አለመኖር ወይም ለውጥ የመንግሥት አለመኖር ወይም የመንግሥት ለውጥ እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ሲወድቅ መንግሥቱ ግን ሳይወድቅ በሌላ አቅጣጫ በሥፍራና በጊዜ እያደገና እየተስፋፋ መሄድ ትምህርታዊ የሆነ የታሪክ ግንዛቤ ይሰጠናል ።

በዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ሕብረተሰብ በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ታሪካዊ ወቅት የአንድ የተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንብርና ቅንጅት በመሆኑ አንድ ሉአላዊ መንግሥት ፤ እንዲሁም ባህላዊ የእርሻ የከተማ የንግድ ፤ የጽሕፈትና የገንዘብ ገጽታዎች ፤ ሥራዎችና አገልግሎቶች ያሉት ማህበረሰብ በመሆኑ ደግሞ አንድ ሥልጣኔ ነበር ለማለት ይቻላል ። ስለዚህ የአክሱማውያን " መንግሥት " እና " ሥልጣኔ" የሚለው አባባል ትክክለኛ አባባል ነው ።

በኋላ ግን በአያሌ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ሂደቶችና ኃይሎች የአክሱማውያን የሥልጣኔ ገላጭ የከተማ ፤ የንግድ ፤ የጽሕፈትና የገንዘብ ገጽታዎችና ሥራዎች በከፊል ወይም በሙሉ እየጠፉ ሲሄዱ በአንድ በተወሰነ መሬት ፤ ሕዝብና ማዕከላዊ የፖለቲካ ሥልጣን ሕጋዊ ግንኙነት የተመሠረተው መንግሥት ግን በማዕከላዊ የዘውድና የሃይማኖት ድርጅቶችና ሥራዎች ተጠናክሮ በሥፍራና በጊዜ በአዲስ መልክአምድራዊ አቅጣጫ እያደገና እየተስፋፋ እንደሚሄድ ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል ።

ከጥንት እስከ ዛሬ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ህልውና ሕይወትና ታሪክ በአካባቢው ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ የጂኦፖለቲካ ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ ነው የሚል ቲሲስ ከዚህ በላይ ቀርቧል ። ከዚህም የተነሳ



የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ መነሻም ፍጻሜም ከሁለቱ የተፈጥሮ አካባቢዎች ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ ታሪካዊ ምንጭና መሠረት የሰሜን ኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ እንደሆነ የተረጋገጠ ተጨባጭ ጂኦግራፊያዊ ነገር ነው ። አክሱማውያን ከዚህ ከሰሜኑ ደጋማ ምንጭና መሠረት በመነሳት በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ጠረፎችና በሮች በውጪ ዓለም ከአረቢያ ፤ ከሕንድ ፤ ከሚሮዌ ፤ ከግብጽ ፤ ከግሪክ ፤ ከሮማውያን ጋር ንግዳዊና ባህላዊ ግንኙነት እንዴት እንደፈጠሩ ከዚህ በላይ አይተናል ። ይህም ታሪካዊ መስተጋቢር የአክሱማውያንን መንግሥትና ሥልጣኔ በዘመኑ አንድ ታላቅ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት አደረገው ።

በዚህ አኳያ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የአክሱማውያን መንግሥትና ስልጣኔ እያደገ ሲሄድ በአንጻሩ በቀይ ባህር ፤ በአባይ ሸለቆና በአረቢያ የነበሩ ጥንታዊ የሚሮዌና የሳባ አገሮችና መንግሥታት በራሳቸው ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች በውድቀት ሂደት ላይ እንደነበሩ አይተናል ።

ከዚህም የተነሳ የአክሱማውያን ነገሥታት ገዳር ፤ የእዛና ዘሩ ናዊ ሀውልት የተከለው ንጉሥ ፤ ኢዛናና ካሌብ ግዛታቸውንና ንግዳቸውን በልዩ ልዩ መንገዶችና መጓሪያዎች በሁለቱም በአረቢያና በላይኛው አባይ ሸለቆ አካባቢዎች በማስፋፋት አገሪቱ ከጥንቱ የውጭ ዓለም ጋር በንግድ ፤ በባህልና በሃይማኖት የነበራትን ግንኙነት የበለጠ እንአጠናከሩት ይታወሳል ። [7]

ነገር ግን በመጨረሻ ከስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ አያሌ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችና ኃይሎች አክሱማውያን በቀይ ባህርና በላይኛው አባይ ሸለቆ በንግድና በእስትራቴጂ የነበራቸውን ብሔራዊ ይዞታና ጥቅም ማዳከም ጀመሩ ። በዚህ ወቅትና አኳያ ፤

አንደኛ ፤ አክሱማውያን በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ በሮችና ጠረፎች ከግሪኮ-ሮማውያን ዓለም ጋር የነበራቸው ንግዳዊና ባህላዊ ግንኙነት እየተዳከመ ሄደ ።

ሁለተኛ ፤ አረቦችና ፋርሳውያን በወታደራዊ ሕብረትና እርምጃ በአረቢያ የአክሱማውያንን የባህር ማዶ ይዞታና ተጽዕኖ ደመሰሱ ። [8]

[7] Mc Crindle, tr. and ed., *The Christian Topography of Cosmas* (1897), pp 59-66; A. J. Drewes, *Inscriptions De L'Ethiopie Antique* (1962), pp. 88, 102; W.F. Jamme *Sabaean Inscriptions From Mahram Bilais (Marib)* (1962), pp. 132-133; Littmann. *DAF* IV, *Inscriptions*, nos. 4, 6-11; Sergew Hable Selassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History* (1972), pp. 124, 148.

[8] *Ibid.*, pp. 145-158.

ሦስተኛ ፣ በሰባተኛው ምዕተ ዓመት በነቢዩ መሀመድ በአረቢያ የተጀመረው የአረቦች ሁል አቀፍ ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ከአረቢያ ጋር መካከለኛውን ምስራቅና ግብጽን በቀጥታ በመያዝ አክሱማውያን በቀይ ባህርና በላይኛው አባይ ሸለቆ ለረጅም ጊዜ የነበራቸውን ብሔራዊ ጥቅምና የፖለቲካ ተጽዕኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጻረር አዲስ ዓለም አቀፋዊ ኋይል ሆነ ። አክሱማውያን በንግድና በባህል በተለይም በአዲሱ የክርስትና ሃይማኖት አማካይነት ከግሪክ - ሮማውያን ዓለም ጋር የነበራቸውን ታሪካዊ ግንኙነት በማሰናከል አገሪቱን ወደ ረጅሙ የብቸኝነትና የገለልተኝነት ዘመን አስገባ ። ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ በ1780 ይህን የአገሪቱን የረጅም የገለልተኝነት ዘመን ያስተዋለው አንድ ታዋቂ የታሪክ ምሁር “ ኢትዮጵያውያን ዓለምን ረስተውትና እነርሱም በዓለም ተረስተው ለአንድ ሺህ ዓመታት ጊዜ አንቀላፉ ”[9] በማለት የግንዛቤ አስተያየቱን ሰንዝሮአል ።

አራተኛ ፣ አክሱማውያን ነገሥታት በላይኛው አባይ ሸለቆ ያስገብሩት በነበረው በቀድሞ የሚኖዌ አገር ኖበዲያ፣ ማኩሪያና አሉዲያ (አለዋ) የተባሉ ሦስት ሉአላዊ ንዑስ የኑቢያ መንግሥታት [10] ተነስተው አገራቸውን ( አክሱማውያንና የቤጃን ሰዎች ጨምሮ ) ከውጭ ኃይሎች ተጽዕኖ ነጻ አደረጉት ።

አምስተኛ ፣ በሰሜን ምስራቅ በቀይ ባህርና በላይኛው አባይ ሸለቆ (ኑቢያ) መካከል ቀድሞ በአክሱማውያን የአጼ መንግሥት የፖለቲካ ተጽዕኖ ሥር የነበሩ የቤጃ ሰዎች ደግሞ ናቅስ ፣ ባልቅን ፣ ባዝን ፣ ጃርንና ካትብ በተባሉ አምስት ንዑሳን ነጻ መንግሥታት ተደራጅተው ነጻ አገሮች ሆኑ ።[11]

ስድስተኛ ፣ በ642 ከኑቢያ በስተሰሜን ግብጽን አረቦች ከሮማውያን ያዙ ።[12] በግብጽ የተመሠረተው ጠንካራ የአረብ ይዞታ ኢትዮጵያን ለሚቀጥለው ረጅም ዘመን ከምዕራብ ዓለም እንደሚለይ በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል ።

በአጭሩ በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ከዚህ በላይ የተገለጸው የአካባቢው የየመን ፣ የቤጃ ፣ የኑቢያና የግብጽ አገሮችና ሕዝቦች ፖለቲካዊ ሁኔታ አክሱማውያን በቀይ ባህርና በላይኛው አባይ ሸለቆ በሮችና ጠረ

---

9 E.Gibbon, *The Decline and fall of the Roman Empire*, vol. 5,p. 66.

10 UNESCO, *History of Africa, II*, pp. 326-331.

11 J.S. Trimingham, *Islam in Ethiopia* (1952), pp. 49-51.

12 UNESCO, *History of Africa, II*, p. 331.



ፎች በኩል ከጥንት ጀምረው ከውጪ ዓለም ጋር በቀጥታ የነበራቸውን ንግዳዊና ባህላዊ ግንኙነት በማዳከም ከጊዜ በኋላ በአንድ በኩል ለአክሱማውያን ሥልጣኔ ውድቀት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ ለአገሪቱ ሉአላዊ ፣ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግስት ከሰሜን ወደ መሀል ፣ ደቡብ ምዕራብና ምስራቅ አቅጣጫዎች ዕድገትና መስፋፋት ውጫዊ ግፊት ሆነ ። በዚህ ውጫዊ ግፊትና ተጽዕኖ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ሲወድቅ በአንጻሩ የአገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት ከክርስትና ሃይማኖት ጋር በአፍሪካ ቀንድ በሥፍራና በጊዜ የበለጠ እያደገና እየተስፋፋ ሄደ ።

## በመካከለኛው ዘመን

የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥት ከግብጽ ፣ ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ ጋር የነበረው ታሪካዊ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ግንኙነት አካባቢው በአዲሱ ዓለም አቀፋዊ የአረቦች እንቅስቃሴ ከተያዘ በኋላ ቢቋረጥም ፣ በአባይ ሸለቆና በቀይ ባህር በሮችና ጠረፎች ከተጠቀሱት አገሮችና ሕዝቦች ጋር የንግድና የሃይማኖት ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አልቀረም ።

በዘመነ አክሱም ፍጻሜ በሰሜኑ ደጋ በአገው ምድር ክርስቲያናዊ የዛጉኤ ስርወ መንግሥት ( 1100-1270) እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ በሀርላ - ሀዲያ ምድር በኤደን ባህረ ሰላጤና በጊቤ መካከል ከ890 አካባቢ ጀምሮ የሸዋ ፣ የይፋት - አዳል ፣ የደዋሮ ፣ የአራባቢኒ ፣ የሻርካ ፣ የሀዲያ የባሊ ሱልጣኔቶችን ጨምሮ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማሩ ብዙ እስላማዊ መንግሥታት ተከሰቱ ።[13]

ከዘመነ አክሱም በኋላ የኢትዮጵያ ሁለቱም ክርስቲያንና እስላም የገዥ መደቦች በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ በሮች በተለይም በሃይማኖትና በንግድ ጉዳዮች ከአዲሱ የአረብ ዓለም ጋር ግንኙነትን ፈጽመው ያቋረጡበት ወቅት ወይም የአረብ አገሮችና መንግሥታት ራሳቸውም ቢሆኑ የአገሪቱን የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ታሪካዊ ወሰኖች አልፈው በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያን ሉአላዊ ግዛትና ሥልጣን ለመድፈር በቀጥታ የሞከሩት ሁኔታና ጊዜ አልነበረም ።

በዘመኑ በአውሮፓ ወራሪው የክርስቲያን ዓለምና በአካባቢው የእስላም ዓለም መካከል በግብጽና በመካከለኛው ምስራቅ ለሶስት ምዕተ ዓመታት በተካሄደው በታላቁ “ የመስቀል ጦርነት ” በታሪክ ለመጀመሪ

---

13 Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 55-63.

ያ ጊዜ የክርስቲያንና የእስላም ሃይማኖቶችና ተከታዮቻቸው አብረው በብሔራዊ አንድነትና ነጻነት በሰላም የኖሩበት ጥንታዊውና በሀውርታዊው የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ከአንዱም ተፋላሚ ወገን ጐን ሳይሰለፍ የገለልተኝነት ፖሊሲ እንደወሰደው አይረሳም ። ይህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ የውጭ ፖሊሲ አቋም ዛሬ በጥሞና መታወስና መታወቅ ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ እንደሚከተለው ባጭሩ ቀርቧል ።

በዚህ ነገር የኢትዮጵያ የአገው ዘመን መንግስት የምዕራብ አውሮፓ ክርስቲያን ዓለምና የአፍር እስያ የእስላሙ ዓለም በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ ዓለም አቀፋዊ የበላይነትን ለመያዝ ከ1095 እስከ 1365 ድረስ ለረጅም ጊዜ በታሪክ “ የመስቀል ጦርነት” በሚል ስያሜ የሚታወቀውን ሁለ አቀፍ ወታደራዊ ፤ ፖለቲካዊ ፤ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ትግል አካሂደው በመጨረሻ ወራሪው አውሮፓ በአፍር እስያ እጅ ሽንፈት ደረሰበት ።

የሁለቱም ማለትም የክርስቲያንና የእስላም ሕዝቦች አገር በሆነችው ኢትዮጵያ በዘመኑ ከሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች ጋር የነበራትን ግንኙነት በትክክል ለማገናዘብና ትምህርት ለመውሰድ በቅድሚያ የተፋላሚዎቹን አነሳስና አሰላለፍ በጥቅሉ ማጤን ትምህርታዊ ግንዛቤ የሚያዳብር ጠቃሚ የስልትም የይዘትም ተግባር ይሆናል ።

ከታሪክ ዘገባ እንደሚታወሰው ፤ ነቢዩ መሐመድ በ632 በአረቢያ በመዲና ከተማ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 712 ድረስ በ80 ዓመታት ውስጥ ብቻ የነቢዩ የአረብ ተከታዮችና ተባባሪዎች በወረራና በዘረፋ ሰይፍ በአካባቢው ጥንታዊ የባይዛንታውያንንና የፋርሳውያንን ኃያላን የነበሩ አጼ መንግሥታትንና ሥልጣኔዎችን ደምስሰው በምትካቸው የነቢዩን ሁል አቀፍ የሃይማኖት ፤ የፖለቲካና የባህል ትምህርት በምስራቅ ከሕንድ ጀምሮ በምዕራብ እስከ ሰሜን አፍሪካና ደቡብ ምዕራብ አውሮፓ ማለትም እስከ እስፓኝ ድረስ በሶስት ክፍለ አህጉራት በማዕበላዊ ኃይልና ፍጥነት አስፋፉት ። [14]

በዚህ ሁኔታ የኡማያድ ፥ የአባሲድ ፥ የፋጢማ ፥ የማምሉክና የኦትማን ካሊፎችና ሱልጣኖች የተባሉ በቅደም ተከተል የአረቢያ ፥ የሶሪያ ፥ የኢራክ ፥ የግብጽና የቱርክ ፊውዳል ነገሥታትና መሳፍንቶች ከሜካ ፥ ከደማስቆ ፥ ከባግዳድ ፤ ከካይሮና ከኢስታንቡል ጥንታዊ ከተሞች በኢትዮጵያ ጠረፍ የሕንድ ውቅያኖስና የቀይ ባህር ዳርቻዎችን ጨምሮ የመካከለኛውን ምስራቅ ፤ የሰሜን አፍሪካንና የደቡብ አውሮፓን አገሮችና ሕዝቦች በአንድ ላይ ለረዥም ዘመን በሃይማኖታዊ ጦርና ሕግ ጥቀቅጠው ገዙ ።

[14] *The New Encyclopaedia Britannica*, vol. 9,pp. 926-930.



ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የአረብ ወራሪዎች ከቀይ ባህር ደሴቶችና የጠረፍ ወደቦች አልፈው በአጠገባቸው በአፍሪካ ቀንድ ወደ ኢትዮጵያ ምድር በሰይፍ ዘመቻ ሊገቡ አልቻሉም ። በሌላ በኩል ግን በቀይ ባህር ከዳህላክ ደሴትና በኤደን ባህረ ሰላጤ ከዜላ ወደብ በኩል በወረራ ሰይፍ ሳይሆን በግለሰብ የአረብ ነጋዴዎችና የሃይማኖት ሰባኪዎች አማካይነት በኢትዮጵያውያን ምርጫና ፍላጐት የነቢዩ መሀመድ የሃይማኖትና የፖለቲካ ትምህርት ገና በአክሱማውያን ዘመን በቀጥታ ከአረቢያ ወደ ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ገብቶ ተስፋፋ ።[15]

በዚህ ወቅት በግምት ከ890 እስከ 1300 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በምስራቅ ከዜላ ጠረፍ ጀምሮ በመሀል አገር እስከ ጊቤ ወንዝ አካባቢ በሚገኘው በደቡብ ምስራቅና በደቡብ መሀል ኢትዮጵያ በጥንቱ የሀርላ - ሀዲያ ምድር በንግድና በእርሻ የተሰማሩ ጥንታዊ የሸዋ ፤ የይፋት - አዳል ፤ የደዋሮ ፤ የሀዲያ ፤ የአራባቢኒ ፤ የሻርካ ፤ የባሊና የደራ ሱልጣኔቶች ተከሰቱ ።

ከዘመነ አክሱም በኋላ በተከታታይ በተነሱ የኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት የሚከተሉ የአጼ መንግሥት ነገሥታት በአፍሪካ ቀንድ በደቡብ ምስራቅ ከተጠቀሱትና የእስልምና ሃይማኖት ከሚከተሉ የአካባቢ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር በአንድ አገር ተቻችለው የኖሩበት ሁኔታ በዘመኑ የአውሮፓ ክርስቲያን መንግሥታትና ሕዝቦች ይከተሉት ከነበረው ከጸረ እስላም አመለካከትና ፖሊሲ በዓይነት ልዩ እንደነበር ማጤን ጠቃሚ የግንዛቤ አሳብ ይሰጣል ።

በሰባተኛው ምዕተ ዓመት አረቦች በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ እንዲሁም በደቡብና በምስራቅ አውሮፓ የወረራና የዘረፋ ዘመቻ በሚያካሂዱበት ወቅት በአውሮፓ የቀድሞ ሮማውያንን የአጼ መንግስትና ሥልጣኔ በወረራ ያፈረሱ አዋጋዊ የፍራንክና የጀርመን ሰፋሪ ነገዶች በክርስትና ሃይማኖትና በፊውዳል ሥርዓት በመደራጀት ላይ እንደነበሩ ይታወሳል ።

እንደሚታወቀው እነዚህ የቀድሞ የፍራንክና የጀርመን ወራሪና አዋጋዊ ነገዶች እስከ አሥረኛው ምዕተ ዓመት ድረስ በምዕራብ አውሮፓ በሮማዊው ፓፓ የበላይ መሪነት አንድ አህጉራዊ የካቶሊክ ክርስትና ሃይ

[15] S. Tedeschi, “ Note Storiche Sulle Isole Dahlak ” *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies*, 3 vols. (Addis Ababa, 1966), I, pp. 54-55; G.W.B. Huntingford, “ Arabic Inscriptions in Southern Ethiopia,” *Antiquity*, vol. 29 (1955); pp. 230-33; OMARI, *Masalik*; Maqrizi, *Moslem Kings*; U. Braukamper, *Geschiche des Hadiya Sud-Athiopiens* (1980).

ማኖት እየተከተሉ በብዙ ፊውዳላዊ ክርስቲያን መንግሥታት ሥር ተደራጁ ።

ከዚያ በኋላ ከ1095 እስከ 1365 ድረስ በሶስት ምዕተ ዓመት ውስጥ የተጠቀሱት አዲስ የአውሮፓ ፊውዳል ነገሥታትና ባላባቶች በሮማዊው የካቶሊክ ፓፓ ቅስቀሳና በደቡብ አውሮፓ አዲስ የዓለም ገበያ ከሚፈልጉ የኢጣሊያ ነጋዴ የከተማ ከበርቴዎች በተሰጣቸው ከፍተኛ የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ መካከለኛውን ምስራቅ ከግብጽ ጋር ከእስላማዊ የአረብና የቱርክ ሕዝቦችና መንግሥታት በመሣሪያ ኃይል ለመያዝ በታሪክ “ የመስቀል ጦርነት ” ተብሎ የሚታወቁትን ዘጠኝ የወረራ ዘመቻዎችን አካሄዱ ፡ [16]

በመጀመሪያው ወቅት ( 1095-1099) ክርስቲያን የአውሮፓ ወራሪዎች በመካከለኛው ምስራቅ የኢየሩሳሌምን ቅዱስ ከተማ ጨምሮ አራት ንዑስ አገሮችን ከእስላሞች ለመያዝ ቢችሉም ፤ በ1189 በሱልጣን ሳላዲን ቀራጥ መሪነት እስላሞቹ የኢየሩሳሌምን ከተማ መልሰው ወሰዱ ። ከዚያ በኋላም የአውሮፓ የመስቀል ጦረኞች ለረዥም ዘመን ቢዋጉም በመጨረሻው የሽንፈት ዕድል አጋጠማቸው ። በመሆኑም እስከ 16ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ አውሮፓ በአፍሮ እስያ ለመስፋፋት ያካሄደው ሙከራ ለጊዜው በሽንፈት ተገታ ።

የአውሮፓ ክርስቲያኖችና የአረብ - ቱርክ እስላሞች በመካከለኛው ምስራቅ በመስቀል ጦርነት እንደዚህ ሲተናነቁ የኢትዮጵያ የአጼ መንግስት በዛጉኤ ነገሥታት አመራር ከጦርነቱ ገለልተኛ በመሆን ፤ በአካባቢው ከግብጽ ፤ ከፍልስጤምና ከየመን አገሮችና መሪዎች ጋር በተለይ በሃይማኖትና በንግድ መስኮችና ጉዳዮች መልካም ግንኙነት እንደነበረው የዘመኑ ታሪክ ያሳየናል ። በዚህ ወቅትና አኳያ ፤

አንደኛ ፤ በግብጽ በእስላማዊ የአገር መሪዎችና በኢትዮጵያ ነገሥታት ስምምነት የግብጹ ኮፕትክ አቡን በየጊዜው በእምነት ጉዳይ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የበላይ መሪ ሆኖ በመሾም በሁለቱ የአባይ ወንዝ አገሮችና መንግሥታት መካከል የመገናኛ ድልድይ ሆኖ ያገለግል ነበር ። በዚህ መንገድ ከውጭ ዓለም ክብረ ነገሥትና ፍትሐ ነገሥት ጨምሮ ብዙ ጥንታዊ መጻሕፍት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይታወሳል ።

[16] *The Encyclopaedia Britannica* (1965), vol. 6,pp.828-



ሁለተኛ ፤ በ1189 የኢየሩሳሌምን ጥንታዊና ታሪካዊ ከተማ ከአውሮፓ ወራሪ ክርስቲያኖች እጅ ነጻ ያደረገው ሱልጣን ሳላዲን ከኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ የኢየሩሳሌም ከተማ የአምልኮ ቦታ ሰጠ ።[17]

ሶስተኛ ፤ በ1172፤ በ1194 እና በ1209 በተከታታይ ከኢትዮጵያ የአጼ ቤተ መንግሥት በካይሮ ወደ ግብጽ ቤተ መንግሥት በልዩ ልዩ ብሔራዊ ጉዳዮች የተላኩ ከፍተኛ የልዑካን ቡድኖች በየጊዜው ሚሽኖቻቸውን በተሳካ ሁኔታ አከናውነው እንደ ተመለሱ ታውቋል ።[18]

አራተኛ ፤ በኢትዮጵያ በአገው ዘመነ መንግሥት በአካባቢው በተለይ በኢትዮጵያና በየመን መንግሥታት መካከል በንግድና በባህል የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት እንደነበር ተመዝግቧል ። በዚህ ነገር ለምሳሌ ከ981 እስከ 1159 ድረስ በየመን አገር በዛብጹ ከተማ ናጃህና ናፍስ በተባሉ ሁለት ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ትግልና ድል የተፈጠረው “ የባኒናጃህ” አዲስ ስርወ መንግሥት ለሁለት ምዕተ ዓመታት ጊዜ የመንን እንደገዛ ይታወሳል ።[19]

በዚህ በባኒናጃህ የየመን ስርወ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያና በየመን አጐራባች አገሮች መካከል በባህል ፥ በንግድና በፖለቲካ መስኮች በጣም የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት ተፈጠረ ። በዘመኑም በአፍሪካ ቀንድ የዚላ ወደብ የኢትዮጵያ ዋናው የንግድ ዕቃዎች መግቢያና መውጫ በር ሆነ ። [20]

አምስተኛ ፤ ከመጀመሪያ ጀምረው የኢትዮጵያ እስላሞች የጥንቱን የደቡብ ምስራቅ ሱልጣኔቶች ጨምሮ በአረቢያ ፤ በመካከለኛው ምስራቅና በግብጽ ከአረብ - እስላም ዓለም ጋር በንግድና በሃይማኖት ሁል ጊዜ የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት እንደነበራቸው የታወቀ ነው ።

ባጭሩ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የዘመኑ ሁለቱ የዓለም ባላንጣዎች የፖርቱጋልና የቱርክ ኃያላን መንግሥታት ከውጭ በአካባቢው እስ ኪገኙ ድረስ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ታሪካዊ ጠረፎችና በሮች በኩል ከአረብ - እስላም ዓለም በኢትዮጵያ ሉአላዊ ፤ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግስት ላይ በይፋ የተሰነዘረበት ብሔራዊ ጥቃትና ጥፋት በታሪክ አይታወቅም ።

[17] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 56.
[18] Sergew H. Selassie, *Ethiopian History*, p. 262.
[19] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 61.
[20] Sergew H. Selassie, *Ethiopian History*, p. 263.

በመስቀል ጦርነት ዘመን ወራሪ የአውሮፓ ክርስቲያኖች በመካከለኛው ምስራቅ የእስላሙን ሀብታምና የተደራጀ ኃይል መቋቋም ካቃታቸው በኋላ ከ1165 ገደማ ጀምሮ “ ቄሱ ዮሐንስ” የሚባል በእስላም ጠላቶቻቸው ላይ ሊረዳቸው የሚችል አንድ ሀብታምና ኃያል የሆነ የአንድ የክርስቲያን መንግሥት መሪ በአካባቢው ዓለም በውል ባልታወቀ ሥፍራ ይኖራል የሚል ወሬ በመስማት በኋላ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ የፖርቱጋል መልክተኞች በሸዋ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ደርሰው የነገሩን ሁኔታ እስኪያረጋግጡ ድረስ የተባለውን ኃያል ክርስቲያን አገርና መሪ በአካባቢው ለማግኘት በምድርና በውሃ ላይ ጉዞ እየፈለጉት ሲባዝኑ ኖሩ ። [21] በዚሁ ፍለጋቸው መጨረሻ ፖርቱጋሎች በመርከብ ጉዞ በደቡብ አፍሪካ ጫፍ አልፈው በ1498 በእስያ ወደ ታላቁና ጥንታዊው የሕንድ መለስተኛ አህጉር ደረሱ ።[22]

በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ በዓለም አቀፍ ንግድና በኃይል ሚዛን ጥያቄ በሕንድ ውቅያኖስ ፣ በፋርስና በአረብ ባህረ ሰላጤዎችና በቀይ ባህር ላይ በፖርቱጋልና በቱርክ የአጼ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ረጅም ጦርነት በዘመኑ በኢትዮጵያ የውጭና የውስጥ ጉዳዮች ላይ አዲስ የጂኦፖለቲካ ግፊትና ተጽዕኖ አስከተለ ።

በዚህ ረገድ የፖርቱጋል ሰላይ ፔድሮ ኮቪልሃ በግብጽ ፣ በመካከለኛው ምስራቅ ፣ በሕንድ ፣ በደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ጠረፍና በአረቢያ ምስጢራዊ ዓለም አቀፍ የስለላ ሥራዎች በማካሄድና የሥራውንም ዘገባ ወደ አገሩ በመላክ በመጨረሻ በ1494 በዜላ በር ወደ አገሪቱ ገብቶ በሸዋ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግስት ደረሰ ። [23]
ሰላዩ ከአገሪቱ ተመልሶ እንዳይወጣ ተደርጎ በኢትዮጵያ ኖሮ ሞተ ።

በኋላም ፖርቱጋሎች ወደ ሕንድ በወረራ እንደደረሱ የመጀመሪያ ወታደራዊ ጥረታቸው ከሕንድ አገር በምድርና በባህር ላይ ጉዞ በአካባቢው የአረብ - ፋርስ አቀባዮችና በኢጣሊያ የዘመኑ ድምበር ዘለል መርከበኛ ነጋዴዎች ትብብር በቀይ ባህር ፣ በፋርስ ባህረ ሰላጤ ፣ በመካከለኛው ምስራቅና በግብጽ በኩል አልፎ ወደ ደቡብ አውሮፓ ይደርስ የነበረውን የምስራቅ ቅመማቅመም ንግድ ( የበርበሬ ፣ የቀረፋ ፣ የዝንጅብል . . .

[21] J. Doresse, *Ethiopia*, (1959), p. 95.

[22] Getahun Dilebo, “Early Portuguese Imperialism in Ethiopia, 1490-1632: Origins, Responses, and Consequences,”
MA Theses (Haward Univ.,1971), p. 32

[23] *Ibid.*, p. 30.



ወዘተ ንግድ ) በሕንድ ውቅያኖስ ፣ በደቡብ አፍሪካ ጫፍና በአትላንቲክ ውቅያኖስ በኩል በምዕራብ አውሮፓ ወደ አገራቸው እንዲደርስ ማድረግ ነበር ። [24]

በዚህ የወረራ ጥረታቸው ከ1498 እስከ 1507 ድረስ በሕንድ ፣ በፋርስ ባህረ ሰላጤና በቀይ ባህር ዓለም አቀፍ ሽብር በመፍጠርና ታላቅ የሕይወትና ንብረት ጥፋት በማስከተል ፖርቱጋሎች በዘመናዊ የጦር መርከብ ኃይል ከላይ የተጠቀሱ አካባቢዎችን ፣ የጠረፍ ወደቦችንና ከተሞችን ከመቆጣጠር በስተቀር በተለይም የፋርስና የየመን መሀል አገሮችንና ሕዝቦችን መያዝ በፍጹም አቃታቸው ። [25]

በመሆኑም በ1508 በሕንድ የፖርቱጋል እንደራሴና የጦር አዛዥ የነበረው አፎንሶ ዳልቡኬርኬ ( 1453-1515) በአካባቢው የእስላም ዓለም ላይ ከኢትዮጵያ ጋር “ የመስቀል ” ጦርነት ለመክፈት በዜላ በር በኩል በሸዋ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት አንድ የመልእክተኞችን ቡድን ላከ ። [26]

በ1509 የልዑል ልብነ ድንግል (1508-1540) ሞግዚት በነበረችው ዝነኛ በእቴጌ እሌኒ የሚመራው የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት በአጸፋው ማቴዎስ በሚባል አርመናዊ ነጋድራስ መሪነት አንድ የዲፕሎማቲክ ሚሽን በአውሮፓ ወደ ፖርቱጋል ቤተ መንግሥት ላከ ። [27]

በአጸፋው ከአሥር ዓመታት በኋላ በ1520 የፖርቱጋል ዲፕሎማቲክ ሚሽን ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት መጣ ። የሚሽኑ አባሎች እስከ 1526 ማለትም እስከ ኢማም አህመድ ግራኝ ጦርነት ዋዜማ ድረስ ለስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ ቆዩ ። [28] በኢትዮጵያና በፖርቱጋል የአጼ መንግሥታት መካከል እንደዚህ ያለ ዓለም አቀፍ የጸረ እስላም ዓለም ሴራና ዲፕሎማሲ ሲካሄድ ሳለ በ1516 ቱርኮች የግብጽን እስትራቴጂያዊ አገር በቀጥታ ይዘው በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ በፖርቱጋሎች ላይ ዘመቻ ከፈቱ ። [29]

በሕንድ ውቅያኖስና በቀይ ባህር እስትራቴጂያዊ ቀበሌዎች በፖርቱጋልና በቱርክ የአጼ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው አዲስ ጦርነትና በዚሁ ወቅት በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል የተከሰተው ጸረ

[24] *Ibid.*, p. 34.
[25] Ibid., pp. 34-37.
[26] *Ibid.*, p. 37.
[27] *Ibid.*, p. 41.
[28] *Ibid.*, pp. 52-58.
[29] *Ibid.*, pp. 39,51,65,

እስላም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በኢትዮጵያ ሉአላዊ ፤ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት ላይ ያስከተሉት ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊ ፤ ማህበራዊ ፤ ሃይማኖታዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ብዙና ዘላቂ ናቸው።

አንደኛ ፤ በ1526 አጼ ልብነ ድንግል ከፖርቱጋል ሚሽን ጋር ለፖርቱጋል ንጉሥ ፤ ለሮማዊው ፓፓና በሕንድ ለፖርቱጋል መንግሥት እንደራሴ በላካቸው ደብዳቤዎች የቀይ ባህሩን የሱዋኪን ፣ የምጽዋና የዳህላክ ደሴቶችን ከዜላ ወደብ ጋር ለፖርቱጋል መንግሥት ሰጣቸው ። በተጨማሪም ከአካባቢው የእስላም አገሮች ጋር ( ግብጽን ጨምሮ ) የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረውን ታሪካዊ ግንኙነት ማቋረጡን ወይም እንደሚያቋርጥ አስታወቀ ። በአካባቢው የእስላም ዓለም ላይ ከፖርቱጋሎች ጐን በጦርነትም እንደሚሰለፍ ገለጸ ። የሮማዊ የካቶሊክ ፓፓውን መንፈሳዊ የበላይ ሥልጣን መቀበሉንም አረጋገጠ ። [30] ባጭሩ በ1526 ደብዳቤዎቹ አጼ ልብነ ድንግል የኢትዮጵያን አገርና መንግሥት በፖርቱጋል መንግሥትና በሮማዊው ፓፓ ሥር አደረገ ።

ሁለተኛ ፤ እንደዚህ ከደመኛ ጠላታቸው ከፖርቱጋል ጋር ግምባር በመፍጠሩ የአካባቢው የእስላም አገሮችና መንግሥታት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የአጼ መንግስት ላይ በጥፋት ሴራ ተነሱ ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ በየጊዜው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልምድ መሠረት ለሃይማኖታዊ አምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ የኢትዮጵያ ምዕመናንን የአካባቢው እስላሞች በመንገድ መግደል ጀመሩ ። [31] በአካባቢው የእስላም ዓለም በፖርቱጋል ወረራና ዘረፋ ጦርነት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ የደረሰባቸው የአረብ ፤ የፋርስና የቱርክ ዜጐች ከ1527 እስከ 1543 ኢማም አህመድ ግራኙ በአጼ ልብነ ድንግል ላይ የአመጽ ጦርነት በከፈተበት ጊዜ የኢማሙ ምንደኛ ወታደሮች በመሆን ለአጼው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ሽንፈትና ለኢማሙ ድል አስተዋጽኦ አደረጉ ።

ሶስተኛ ፤ በጦርነቱ ሂደትና ፍጻሜ ቱርኮች ኢማም አህመድ ግራኙን በመደገፍ ፖርቱጋሎች ደግሞ በአጼው ማዕከላዊ መንግሥት ጐን በመሰለፍ ሁለቱም ባላንጣ የዘመኑ የዓለም ኃያላን መንግሥታት በየፊናቸው በአፍሪካ ቀንድ የየራሳቸውን ገበያና የፖለቲካ ጥቅም ለማስፋፋት በሃይማኖት ሽፋን ከውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጣዊና ብሔራዊ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት በአገሪቱ ላይ ታላቅ የባዕዳን ጥቃትና ጥፋት አስከተሉ ።

[30] *Ibid.*, pp. 58-60.

[31] *Ibid.*, p. 75.



አራተኛ ፤ ከጦርነቱ በኋላ ሁለቱም ተፎካካሪ የቱርክና የፖርቱጋል የዘመኑ የዓለም ኃያላን መንግሥታት በየፊናቸው አገሪቱን በሃይማኖትና በአካባቢ ፖለቲካ በማለያየት የኢትዮጵያን ሉአላዊ ጥንታዊና በሀውርታዊ ሕዝብና መንግሥት ለመያዝና ለመግዛት ከ1541 እስከ 1632 ድረስ በጠቅላላው ለአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ያልተሳካ ረጅም ሴራ አካሂደው ሁለቱም በተባበረና በተሳካ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ብሔራዊ አንድነት ፤ ትግልና ድል በሽንፈት ከአገሪቱ ወጡ ። [32]

## በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም

በ1095-1365 የመስቀል ጦርነት በተፈጥሮ ሀብትና በሰው ብዛት አነስተኛ ደሀ የሆነው ክርስቲያን አውሮፓ በእሲያና በአፍሪካ አህጉራትና ሕዝቦች ላይ ለመስፋፋት የወሰደው የወረራ እርምጃ በእስላም የአረብና የቱርክ ሕዝቦች ታላቅ ትግልና ድል መቀልበሱ ይታወሳል ። ከዚያ በኋላ ከ1365 እስከ 1490 ድረስ ንዑስ የአውሮፓ አህጉር የጠመንጃ ፣ የመርከብና የባህር ላይ ጦር ቴክኖሎጂን ፈጥሮ በከፍተኛ ደረጃ ገነባ ።

በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በተጠቀሱ ዘመናዊ የጦርና መገናኛ መሣሪያዎች አውሮፓውያን በፖርቱጋልና እስፔን የጠረፍ መንግሥታት አመራር በወቅቱ በዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከትንሹ የአውሮፓ አህጉር ኋላ ቀር የሆኑ የእስያ ፤ የአፍሪካና የአሜሪካ ጥንታዊና ሀብታም አህጉራትንና ሕዝቦችን ከአትላንቲክና ከሕንድ ውቅያኖሶች መውረርና መዝረፍ ጀመሩ ። በአሜሪካና በአውስትራሊያ አህጉራት ጥንታዊ ነባር ሕዝቦችን ከሞላ ጐደል አጥፍተው ራሳቸው በነዋሪነት ሰፈሩ ። አህጉራቱንም ኮሎኔዎቻቸው አድርገው ያዙ ።

ወራሪው ትንሹ አውሮፓ በጠመንጃና በመርከብ መሣሪያዎች ኃይል ከእስያ ከአፍሪካና ከአሜሪካ ሀብታምና ጥንታዊ አህጉራት በዘረፋው ታላቅ የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ጉልበት ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት እስከ አስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት የካፒታሊዝም ሥርዓትን ገነባ ። የካፒታሊዝም ሥርዓት በአውሮፓ በአንድ በተወሰነ ብሔራዊ ምድር ፣ ኢኮኖሚ ፣ ቋንቋና ባህላዊ ስነ ልቦና ለተመሠረተ ለአዲሱ ብሔረ መንግስት ዕድገት ወሳኝ ታሪካዊ መሠረትና መሣሪያ ሆነ ።

በመጨረሻም በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት የምዕራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ብሔረ - መንግሥታት በካፒታሊዝም ሥርዓት በወዛደርና በማሽን ጉልበት ከብሔራዊ ገበያና ፍላጐት በላይ የሚያመ

[32] *Ibid.*, Chapter V, VI; Rossini, *Historia Sarsa Dengel*, parts. 4-6.

ርቱ እርካሽ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወስደው ለመሸጥና በአገራቸው ለበለጠ የኢንዱስትሪ ምርት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን በዘረፋ ለማግኘት አሁን በተለይ የአፍሪካና የእስያ አህጉራትንና ሕዝቦችን በኮሎኒያዊ ግዛቶችና በፖለቲካ የተጽዕኖ ክልሎች ከፋፍለው በቀጥታ በጦር ኃይል በመያዝ በታሪክ " ኢምፔሪያሊዝም " የካፒታሊዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ተብሎ የሚታወቅ አዲስ የወረራና የዘረፋ ዘመንና ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ አስፋፉ ።

በዚህ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ታሪካዊ ጠረፎች በኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ላይ እስከ ዛሬ ድረስ ለሁለትም ምዕተ ዓመታት በሥፋራና በጊዜ ያልተቋረጠ አዲስ የወራሪዎችና የኢምፔሪያሊስቶች ጥቃትና ጥፋት ተሰነዘረ ።

በዚህ ረገድ በ1798-1799 በግብጽ ምድር በእንግሊዞችና በፈረንሳዮች መካከል በተካሄደው ጦርነት ወቅትና በኋላ በግብጽ የቱርክ አጼመንግሥት እንደራሴ የነበረው አልባኒያዊው መሐመድ ዓሊ (1769-1849) ከ1516 ጀምሮ በቱርክ አጼ መንግሥት ሥር ግብጽን ለረጅም ዘመን ይገዛ የነበረውን የማምሉክ የገዥ መደብ በመሣሪያ ኃይል ደምስሶ በምትኩ በእንግሊዞችና በፈረንሳዮች የገንዘብና የቴክኒክ እርዳታ በቱርክ አጼ ዘውድ ሥር የግብጽን ዘመናዊ ጥገኛ መንግሥትና አዲስ የቱርክ - ግብጽ ገዥ መደብ ፈጠረ ።

በ1820 የመሐመድ ዓሊ የቱርክ - ግብጽ ወራሪ ጦር በላይኛው አባይ ሸለቆ በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ድምበር ከ1500 ጀምሮ የነበረውን ናይሎቲካዊ የፋንጅን (የሰናር) ሉአላዊ መንግሥት አጥፍቶ አገሩን "ሱዳን" በሚል አዲስ የአረብ ስም የግብጽ ኮሎኒ አደረገው ። ከ1820 እስከ 1876 ድረስ ተስፋፊ መሐመድ ዓሊና ወራሾቹ በአውሮፓና አሜሪካ ምንደኛ የጦር አማካሪዎችና አዛዦች እርዳታ በሜዲትራኒያን ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ መካከል የአባይ ሸለቆንና የአፍሪካ ቀንድን ከቀይ ባህርና ከአረቢያ ጋር በቱርክ-ግብጽ የአጼ መንግሥት ሥር ለማደራጀት ያልተሳካ ታላቅ ጥረት አደረጉ ።

ነገር ግን በዚሁ ወቅት በዓለም ንግድና መገናኛ ታሪክ አብዮታዊ ለውጥ ያስከተለው የስዊዝ ካናል መከፈት ለጥገኛው የግብጽ መንግሥትና ለቀይ ባህር ጂኦፖለቲካ ታሪክ አዲስ ዓለም አቀፍ ሚና በመስጠት በኢምፔሪያሊዝም እግር ስር የግብጽን ውድቀት በኃይል አፋጠነ ። በዚህ አኳያ በጉንደትና በጉራዕ ጦርነቶች በአውሮፓና በአሜሪካ ምንደኛ አዛዦች የተመሩ የግብጽ ወራሪ ወታደሮች በኢትዮጵያ ጦር በተከታታይ ከተደመሰሱ በኋላ በመጨረሻ በ1882 ከስዊዝ ካናል ጋር የግብጽ ወኪል መንግሥት ራሱ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች በቀጥታ እንደ ኮሎኒ ተያዘ ። የሱዳን ማህዲስቶች በእንግሊዝና በግብጽ ወራሪዎች ላይ በነጻነት አመጽ ተነሱ ።



በ1882 ስዊስ ካናል ፣ ግብጽና የአባይ ሸለቆ በቀጥታ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች ከተያዙ በኋላ በ1884- 1885 የምዕራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የአፍሪካ አህጉርና ሕዝብን በኮሎኒ ግዛቶችና በተጽዕኖ ክፍሎች በቅርጫ ተከፋፍለው ለመያዝ በጀርመኑ በርሊን ከተማ ተሰባስበው በይፋ ተስማሙ ። በበርሊኑ የኢምፔሪያሊስቶች ዓለም አቀፍ ሴራ ጉባኤ በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሉአላዊና በሀውርታዊ አገርና መንግሥት በምስቱ ኃያላን የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይና የኢጣሊያ ኢምፔሪያሊስቶች መካከል እንዲሸነሸን በድፍረት ተወሰነ ። በተጨማሪም በዚሁ ወቅት ከአባይ ሸለቆ ጠረፍ የሱዳን ማህዲስቶች በኢትዮጵያ ላይ የወረራ ጦርነት በመክፈት ይልቁኑ በኢምፔሪያሊስቶች እጅ የአገራቸውን ውድቀት አፋጠኑ ።

በአገሪቱ የሰሜንና የምስራቅ እስትራቴጂያዊ ጠረፎች አራት ጥንታዊና ታሪካዊ ቀበሌዎች ከብዙ ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች ጋር በአዲስ የባዕዳን ስያሜ "ኤርትራ ፤ "የፈረንሳይ ሶማሌላንድ" ፤ "የእንግሊዝ ሱማሌላንድ " እና " የኢጣሊያ ሱማሌላንድ " ተብለው በቀጥታ በምስቱ ኃያላን የኢጣሊያ ፤ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ጦር ለጊዜ ቢያዙም በ1880ዎቹና በ1890ዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ከሱዳን ወራሪዎችና ከተጠቀሱ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር በጦርነትና በዲፕሎማሲ ታላቅ መስዋዕትነት ከፍሎ ባካሄደው ወሳኝ ትግል የአገሪቱን ብሔራዊ ነጻነትና አንድነት ከኢምፔሪያሊዝም ጥፋት አዳነ ።

በመጨረሻም በ1935 የኢጣሊያ ፋሽስቶች ከኤርትራና ከኢጣሊያ ሶማሌላንድ ኮሎኒዎች በታንክ ፣ በመድፍ ፣ በጦር አይሮፕላንና በመርዝ በታጠቁ በ300,000 ወራሪ ወታደሮች በታሪክ ታላቁን የኮሎኒ ጦርነት በመላ ኢትዮጵያ ላይ በምድርና በሰማይ ከፈቱ ። ይሁን እንጂ ከ1935 እስከ 1941 ድረስ ለአምስት ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ባካሄደው ብሔራዊ ትግል በ1941 አገሪቱን ከኢጣሊያ ፋሽዝም ነጻ አወጣ በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ብሔራዊ ጸረ- ኢምፔሪያሊዝም ትግሉን አጠናክሮ በመቀጠል በ1952 የአገሪቱን ታሪካዊውን የኤርትራ ክፍለ ሀገር በ1941 በኢጣሊያ ፋሽዝም እግር ከተተው ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ነጻ አወጣ ።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የፋሽዝምና የኢምፔሪያሊዝም ቁስል ገና ሙሉ በሙሉ ሳይድን በሀያኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ በአካባቢው በአዲስ የተከሰቱና ነዳጅ ዘይት አምራች የሆኑ ብዙ የአረብ መንግሥታት በአገሪቱ የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲክ ላይ አንድ ሌላ የአደጋ ዘመንና ምዕራብ ከፈቱ ። በመሆኑም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የተጠቀሱ የአረብ መንግሥታት በተለይ በኤርትራ

የተነሱ የውስጥ ተጻራሪ ኃይሎችን በሃይማኖታዊ ፖለቲካ በገንዘብና በመሣሪያ በማስታጠቅ የአገሪቱን ጥንታዊ ፣ ሉአላዊና በሀውርታዊ መንግሥት ለማጥፋት ያልተሳካ ሴራ በማድረግ በሕይወትና ንብረት ታላቅ ብሔራዊ ጉዳት አስከተሉ ።

ጂኦፖለቲካ በአንድ አገር ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ እንደ አካባቢውና እንደ ዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረታዊ የዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ወይም አፍራሽ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የጅኦግራፊያ ፣ የስትራቴጂ ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መገለጫና መስተጋቢር እንደሆነ ይታወቃል ።


በዚህ ረገድ ፣ የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ረጅም የነጻነት ታሪክ እንደ ዘመኑ ተጨባጭ ዓለም አቀፍ ሁኔታና ሂደት በአገሪቱ ብሔራዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ መሠረታዊ የልማት አስተዋጽኦና የአፍራሽ ተጽዕኖ ፈረቃ ሲያስከትል እንደኖረ በዚህ ጽሑፍ ከዚህ በላይ በአጭርና በጥቅል ተመልክቷል ።

በጥንት ዘመን በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ጠረፎችና የንግድ መስመሮች ጥንታዊ ግብጻውያን ፣ ሳባውያን ፣ ግሪኮችና ሮማውያን በየዘመናቸው በንግድ ፣ በሃይማኖትና በባህል ከአፍሪካ ቀንድ ጋር የነበራቸው የረጅም ዘመን ግንኙነት ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ፑንታውያን ፣ ደአማታውያንና አክሱማውያን ሉአላዊ አገሮችና መንግሥታት ዕድገትና ዓለም አቀፍዝና ገንቢ አስተዋጽኦ እንደ አደረገ ከታሪክ ሰነድና ጥናት ታውቋል ።

በሌላ በኩል በመካከለኛው ዘመን በአካባቢው ሁል አቀፍና ዓለም አቀፍ የአረቦች ኃይልና እንቅስቃሴ ፣ በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በንግድና በኃይል ሚዛን ጥያቄ የፖርቱጋሎችና የቱርኮች ፣ ግጭት ፣ በአስራ ዘጠነኛውና በሀያኛው ተከታታይ ምዕተ ዓመታት ደግሞ ዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝምና የፋሽዝም ግፊት ፣ እንዲሁም በቅርቡ ነዳጅ ዘይት አምራች የሆኑ የአረብ መንግሥታት ክተት በኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ ላይ አፍራሽ ተጽዕኖ አሳድሯል ። በድምሩ በአለፉት አምስት ምዕተ ዓመታት የተጠቀሱት የውጭ ተፃራሪ ኃይሎች በልዩ ልዩ መንገዶችና ወቅቶች በአገሪቱ ብሔራዊና ማህበራዊ ዕድገት ጉዳና ላይ ብዙ እንቅፋቶችን በመፍጠር ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚገኝበት ኋላቀር የዕድገት ደረጃ ታላቅ አስተዋጽኦ እንደ አደረጉ ታሪክ ያስተምረናል ።

ለወደፊቱም የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በፍጥነት አዲስ ብሔራዊ የጠረፍ ዕድገትና ልማት ፖሊሲና ፕሮግራም ቀይሶ ተግባራዊ እስኪያደርግ ድረስ ምናልባትም በአገሪቱ አጠቃላይ ብሔራዊ ዕድገትና ልማት ጉዳይ ላይ የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ አፍራሽ ተጽዕኖ በበለጠ ሁኔታ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይችል ይሆናል ።





# ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ታሪክ ዕድገትና ሂደት

### 1. በጥንት ዘመን ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 1270 ዓመተ ምህረት ፑንት የሀበሻ ፤ የአማልክትና የቅመማ ቅመም አገር በ2800 ዓመተ ዓለም

### የታሪክ መረጃ

የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች የተጻፈ ታሪክ ከዛሬ ወደ ኋላ እስከ ጥንቱ ፈርኦናዊ ግብጻውያን ዘመን ድረስ ቢያንስ 4800 ዓመታት ይደርሳል ። በሰሜን ከቀይ ባህር ወደብ ሱዋኪን ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ እስከ ጉአርዳፉይ ጫፍ ድረስ የሚገኘውን የአፍሪካ ቀንድ የጠረፍ ቀበሌ ጥንታዊ ግብጻውያን በወል ስያሜ “ የፑንት ፣ የቅመማቅመምና የአማልክት ”[1] አገር የአገሩን ሕዝብ ደግሞ “ ሀበሻ ”[2] ብለው ይጠሩት ነበር ። በጥንቱ የግብጽ ስዕላዊ ሃይሮግላፊክስ ጽሑፍና ታሪክ ታዋቂ ምሁር ፕሮፌሰር ጆን ዶሬስ እንደሚሉት በአፍሪካ ቀንድ ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት “ ሀበሻ ” የሚለው ስያሜ ታሪካዊ አመጣጡ ምናልባትም ከዚህ ከጥንቱ ፑንታውያን ስም ሊሆን ይችላል ።[3]

### የፑንት ምርትና ንግድ

የጥንቱ ግብጻውያን ስዕላዊ ሃይሮግላፊክስ (Egyption Hieroglyphics) እንደሚያመለክተው ፤ የዚያ ጥንታዊ የአፍሪካ አገርና መንግሥት ሱሁሬን (2743-2731) እና ሃትሼፕሱትን (1504-1482) የመሳሰሉ በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1300 ድረስ በነበረው ረጅም ዘመን ውስጥ በፈረቃ የተነሱ ከአምስተኛው እስከ አስራ ስምንተኛው ስርወ መንግሥታት

---

J. Doresse, *Histore Sommaire De La Corne Orientale De L'Afrique* (1971) pp 48-58; J. Leclant, "L'Exploration Des Cotes De La Mer Rougue: A La quete De Pount et Des Secretes De La Mer-Erythree" *Annales D' Ethiopie*, vol. 11 (1978), pp. 69-73.

[2] *Ibid., Histoire Sommaire*, pp. 55-56.

[3] *Ibid.*, pp. 61,63.



መሪዎች በሁለቱም በባህርና በምድር ላይ ጉዞ ማለትም በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ በርችና መስመሮች በየወቅቱ የመርከብና የሲራራ ነጋጋዴዎች ወደ ምድረ ፑንት ይልኩ ነበር ።[4] በአባይ ሸለቆ በር ወደ ምድረ ፑንት የሚወስደው የግብጻውያን የሲራራ ንግድ መንገድ ከሰሜን ምዕራብ በኑቢያ - አትባራ - ባርካ በኩል እንደ ነበር በዘመኑ ማለትም በጥንታዊ ግብጽ ጽሑፍና ታሪክ ታዋቂ የሆኑ ምሁራን ይገምታሉ።[5]




ከ3500 ዓመታት በፊት በቀይ ባህር ዳርቻ የፑንታውያን ወደብ ከግብጻውያን መርከቦች ጋር ።

---

[4] *Ibid.*, p. 51.

[5] Leclant.,, Pount et Mer Erythree,,, p. 72.



ከ3500 ዓመታት በፊት በቀይ ባህር ዳርቻ የፑንታውያን
ወደብ ከግብጻውያን መርከቦች ጋር ።

በዘመኑ በመርከብና በሲራራ ንግድ ከምድረ ፑንት ወደ ግብጽ በሚወስዱ ብዙ ዓይነት የማዕድን ፤ የእንስሳት ፤ የአዝርዕት ፤ የእጽዋት ፤ የአእዋፍና የአራዊት ምርቶች ዝርዝር ውስጥ ልዩ ልዩ የብረታ ብረት ፤ የወርቅ ፤ የብር ፤ የነሐስ ፤ የመድኃኒትና የጌጣጌጥ ዕቃዎችና ቀለሞች ፤ መጫዕጣን ፤ ከርቤና ቀረፋ ፤ የዝሆን ጥርስ ፤ የአውራሪስ ቀንድ ፤ የሰጐን እንቁላል ፤ የሰጐን ላባ ፤ ድብ ፤ የድብ ፤ ቆዳ ፤ ቀጭኔ ፤ ቀበሮ ፤ ዝንጀሮ ፤ ሰሉግ ውሻ ፤ አህያ ፤ ኮርማ ፤ በሬ ፤ ጥጃ ፤ ልዩ ልዩ የእንጨት ውጤቶች ለዓይነት የሚጠቀሱ የአፍሪካ ቀንድ መደበኛ ሀብቶች ናቸው ። [6]

ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በ1500 ዓመተ ዓለም ታላቋ የግብጽ ንግሥት ሃትሼፕሱት በካፒቴን ነሃሲ አዝማችነት ወደ ፑንት ከላከቻቸው አምስት የንግድ መርከቦች ጋር የነበረው አንድ የግብጽ ሰዓሊ የፑንትን አንድ የወደብ መንደር ከሰዎች ፤ ከቤቶች ፤ ከእንስሳትና እታክልቶች ጋር የአገሩን ፐረሁ የተባለ ንጉሥና አጢ የተባለች ንግሥት ጨምሮ በወደቡ ከመርከቦች ጋር የሚያሳይ አንድ ታላቅ የስዕል ሰነድ ለዓለምና ለታሪክ ትቶ አልፎአል ። ይህ እስከ ዛሬ በምድረ ግብጽ በሃትሼፕሱት መቅደስ ውስጥ የሚገኘው ቅጂ በዚህ መጽሐፍ ከዚህ በላይ የቀረበው ስዕል የኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የሰነድ መረጃ ነው ። [7]

## የደአማታውያን መንግሥት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 100 ዓመተ ምህረት

### የታሪክ መረጃ

በአፍሪካ ቀንድ “ ከፑንት የሀበሻ የአማልክትና የቅመማቅመም አገር ” በኋላ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የታወቀው አገርና ሕዝብ በዓመተ ዓለም በመጨረሻ አምስት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ በዛሬ ደቡባዊ ኤርትራና ሰሜናዊ ትግራይ የነበረው ጥንታዊ የደአማት መንግሥት ነው ። [1]

የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማት መንግሥትና ሥልጣኔ በሚመለከት ፤ በደአማትና በሳባ ቋንቋዎች የተጻፈ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ መረጃ የተገኘው በኤርትራና በትግራይ አብዛኛው ከየሀ ፤ ከመጠራ ፤ ከከስከሴ ፤ ከሐ

[6] Sergew H. Selassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History to* 1270(1972), PP. 22-23.

[7] Leclant, “ Pount et Mer Erythree” p. 70.

[8] Shneider, “Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne” pp. 47-54;Anfray, “ Recherches Archeologiques en Ethiopie,” pp.715-16.



ውልቲ ፤ ከአዲቀዋህ ፤ ከአዲገለሞና ከእንዳጭርቆስ ጥንታዊና ታሪካዊ ቦታዎች ነው ። ከእነዚህ ከዘመን ደአማት ጽሑፎች መካከል ፤

1. ወአረነሀየውተ ፤ ረዳአመ ፤ ረበሀና ለመን የሚባሉ የአራት ነገሥታትን ስሞች ፤
2. ሰመአተመአኩተን የተባለች የአንዲት ንግሥትን ስም ፤
3. ነረመ ፤ ጸደቀን ፤ ሸመን ፤ ረበና አበከወደመ ተብለው የሚታወቁ የአምስት ብሔራዊ አማልክትን ስሞች ፤
4. አስተር ፤ ሀወበሰ ፤ አለመቀሀ ፤ ደተሀመየመና ደተበአደን ተብለው የሚጠሩ የአምስት በዘመኑ በመካከለኛው ምስራቅና በአረቢያ የታወቁ የውጭ አማልክትን ስሞች ፤

የያዙ በድምር አስራ ሦስት አጫጭር የነገሥታት ዜና መዋዕሎች በተለይ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክና ጂኦፖለቲካ በተመለከተ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መሠረታዊ ሰነዶች ናቸው ። [2]

በእነዚህ ሰነዶች መሠረት በደአማት አገርና መንግሥት ሰለመመፈተረነና ወረነረየደነ የተባሉ ሁለት ተከታታይ ስርወ መንግሥታት ወይም የነገሥታት ወገኖች ነበሩ ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱ የደአማት ነገሥታት ወአረነሀየወተና ረደአመ ከመጀመሪያው ስርወ መንግሥት ረበሀና ለመን ደግሞ ከሁለተኛው ስርወ መንግሥት እንደነበሩ በዜና መዋዕሎቹ ተመልክቷል ። [3] ይህም ሁኔታ በቅድመ አክሱም የኢትዮጵያ ጥንታዊ ደአማት በሀወርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ እንደነበር ያመለክታል።

### ደ' ማት የኢትዮጵያ የሥልጣኔ መነሻ

በአመዛኙ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው የደአማታውያን ጽሑፎች በዓይነትና በዕድገት ደረጃ ልዩ በሆኑ በሁለት ቋንቋዎችና በሁለት የጽሕፈት ሥርዓቶች ወይም ዘዴዎች ( Monumental Writing and Cursive Writing ) ማለትም በቁም የጌጥና በስድ የተራ ጽሕፈት ሥርዓቶች የተጻፉ ሰነዶች ናቸው ። [4]

ከሁለቱ ቋንቋዎች አንዱ ከነስልተ ጽሕፈቱ በዘመኑ በደቡብ አረቢያ ከነበረው ከሳባ ጥንታዊ ቋንቋና የቁም ጽሕፈት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ በዘመኑ ታሪክና ጽሕፈት ታዋቂ በሆኑ ምሁራን ዘንድ ታምኖበታል ። [5]

[2] *Ibid.*, “ Recherches” p. 715; Schneider, “ Inscriptions Sudarabiques” pp.387-89.

[3] *Ibid.*, “ Inscriptions Sudarabiques,” p. 389.

[4] Schneider, “Les Debuts De L Histoire Ethiopienns” pp. 49,51.

[5] *Ibidè.*

ሁለተኛው ቋንቋ ግን ከነስልተ ጽሕፈቱ በዘመኑም ሆነ ከዚያም በፊት ወይም በኋላ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያልተገኘና በዓይነት አዲስና ልዩ ከመሆኑም በላይ በዕድሜም አኳያ ከሳባውያን ቋንቋ ፤ ፊደልና ጽሕፈት ቅድሚያ ያለው የአገሩ የደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋና ጽሕፈት ነው ። በተጨማሪም በኋላ በዘመነ አክሱም የኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋና ጽሕፈት ከዚሁ ከደአማታውያን ቋንቋና ጽሕፈት እንደመነጨ በታዋቂ ምሁራን ተገልጾአል ።[6]



ከ2500 ዓመታት በፊት የደአማታውያን ሀውልት ከትግራይ

እንደዚህ በአገሩ መንግሥታዊ ሰነዶች ማለትም በነገሥታት ዜና መዋዕሎች ከደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋ ጽሕፈትና አማልክት ጋር የውጭ አማልክት ፤ ቋንቋና ጽሕፈት መገኘት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ሕዝብና መንግሥት ከአካባቢው ዓለም ጋር በተለይም በአረቢያ

[6] *Ibid.*, "On the Evolution of the Ethiopian Writing," Lecture Text. (Addis Ababa, 1982), p. 5; "On the Daamattite State, Kings, Gods", Written Note to the Author (Addis Ababa, 1982).




ከሳባውያን ጋር ለረጅም ዘመን በንግድ ፣ በሃይማኖት ፣ በቋንቋና በባህል የቀረበ ታሪካዊና ጂኦ ፖለቲካዊ ግንኙነት እንደነበረው በተጨባጭ ያሳያል ።

በዚህ ጉዳይ እንዲያውም ከደአማት ነገሥታት አንዱ የረበህ ልጅ " ድል አድራጊው " ንጉሥ ለመነ በዜና መዋዕሉ ራሱን " የደአማታውያን ፣ የሳባውያን ፣ የአበራውያን የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ "[7] በማለት በዘመኑ የነበረውን የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥት በሀውርታዊ ጥንቅር በአጭርና በጥቅል ገልጾታል ።

በዜና መዋዕሉ " የደአማታውያን ፣ የሳባውያን ፣ የአበራውያን ፣ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ " የሚለው የንጉሥ ለመነ የዙፋን ስም የደአማት መንግሥትና ሕብረተሰብ በእርግጥ እንደዛሬውም ኢትዮጵያ በሀውርታዊ አገር እንደነበር ያሳያል ። ከረጅም ጊዜ ጥናትና ምርምር በኋላ በዘመናችን የደአማትን ሥልጣኔ ለዓለም በትክክል ከአሳወቁ ምሁራን አንዱ እንደተረጎሙት ፣[8] በዚህ በንጉሥ ለመነ ዜና መዋዕል የተጠቀሱት "ሳባውያን" ከአካባቢው የሳባ አገር በሰፈራ ይሁን በቅጥር ወይም በሰነዱ ውስጥ በግልጽ ባልተብራራ ተግባር መጥተው በአገሩ ሕግ ስር የሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች ወይም ገባሮች ነበሩ ።

ይህ በጥንታዊ ኢትዮጵያና አረቢያ መካከል በዘመነ ደአማት የነበረው ታሪካዊና ጂኦፖለቲካዊ ግንኙነት በኋላ በዘመነ አክሱም በተጠናከረ ሁኔታ በመቀጠል በዘመነ ክርስትና የመጀመሪያ ምዕተ ዓመታት ለተወሰነ ጊዜ አረቢያ ራሱ የኢትዮጵያ የባህር ማዶ ገባር ግዛት ሲሆን ከዚህ በታች ይታያል ።



የአዱሊስ ከተማና ሰነዳዊ ሀውልት በ525

[7] *Ibid.*, " Inscriptions Sudarabiques" p. 387.

[8] *Ibid.*, p. 388; " Ethiopian Writing," p. 5.

## የአክሱማውያን መንግሥት በዘመነ ክርስትና ከ100 እስከ 1100

### የታሪክ መረጃ

በዘመነ ክርስትና የኢትዮጵያ የአክሱማውያን የአጼ መንግሥት በሥፍራና በጊዜ የደአማታውያን መንግሥት ዕድገትና መስፋፋት ሲሆን ፤ በዘመኑ ታሪክ መሠረታዊ የመረጃ ምንጮች ደግሞ የሚከተሉ ናቸው ።

1. በ150 አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የአክሱም ከተማ በሰነድ የተገኘበት በግሪኩ ክሉድዮስ ቶለማይ የተጻፈው የጅኦግራፊያ መጽሐፍ ( Cudius Ptolemy, Geographia )[1]

2. በግምት በሁለተኛው ምዕተ ዓመት በትክክል በማይታወቅ ዘመን ስሙ ባልተጠቀሰ በአንድ የግሪክ መንገደኛ የኤርትራ ባህር ፕሪፕለስ ማለትም የኤርትራ ባህር ላይ ጉዞ ( The Periplus of the Erythraean sea) በሚል ርዕስ ተጽፎ የመጀመሪያው አክሱማዊ ንጉሥ ዞስካሌስ ስሙ የተገኘበት ታሪካዊ መጽሐፍ ፤[2]

3. ስሙ ከኖረበት ዘመን ጋር ከሰነዱ ገጽ የጠፋበት አንድ አክሱማዊ ንጉሥ በግምት በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕተ ዓመታት መካከል በአዱሊስ የወደብ ከተማ በግሪክ ቋንቋ በአንድ የድል ሀውልት ላይ ለዝክረ አማልክት ከቀረጸው ታሪካዊ ጽሑፍ በ525 ኮስማስ የግሪክ መንገደኛው ነጋዴ ገልብጦ ያቆየው ሰነድ ፤[3]

4. በ250 አካባቢ በአረቢያ ስለ “ ሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደራት ” በሳባ ቋንቋ የተጻፈው ሰነድ ፤[4]

5. በ250 አካባቢ በኢትዮጵያ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው “ የአክሱማውያን ንጉሥ ገዳር ” ዜና መዋዕል[5] ( በአረቢያ ንጉሥ ገዳራትና በኢትትዮጵያ ንጉሥ ገዳር በሁለት ልዩ ሥፍራዎችና ቋንቋዎች የአንድ አክሱማዊ ንጉሥ ስሞች እንደ ሆኑ በጥናት ታውቋል ። )

[1] Sergew H. Selassie, *History*, pp. 72, 75.

[2] G.W.B. Huntingford, tr. and ed., *The periplus of the Erythraean Sea*(1980), pp. 12.20.

[3] Cosmas, *The Christian Topography of Cosmas*, tr. and ed. by W.Mc Crindle (1897), pp. 59-66

[4] A.Jamme, *Sabaean Inscriptions from Mahram Bilqis* (*Marib*) (1962), pp. 132-33.

[5] Drewes, *Inscriptions*, pp. 88,102.



6. በ270 አካባቢ በኢትዮጵያ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው “ የአክሱማውያን ንጉሠ ነገሥት ስምብሩትህስ ታላቁ ” ዜና መዋዕል[6]፤

7. በአራተኛው ምዕተ ዓመት በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ የአጼ ኢዛና ብዙ ዜና መዋዕሎች ፤[7]

8. በስድስተኛው ምዕተ ዓመት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው የአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ፤[8]

9. በስድስተኛው ምዕተ ዓመት በሳባ ቋንቋ የተጻፈው በአረቢያ የአክሱማውያን የአጼ መንግሥት እንደራሴ የአብርሃ ዜና መዋዕል ፤[9]

10 ከሶስተኛው ምዕተ ዓመት እስከ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከሀያ በላይ አክሱማውያን ነገሥታት በኢትዮጵያና በአረቢ ከወርቅ ከመዳብና ከነሐስ አሰርተው በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፈባቸው ብዙ ገንዘቦች[10] የዘመነ አክሱም ታሪክ በሚመለከት ቁልፍ የመረጃና የእውቀት ምንጮች ናቸው ።

### የግዛተ አጼ ግምባታና ስፋት

በጂኦግራፊያ መጽሐፉ የአክሱምን ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመዘገበው ቶለማይ በኋላ ሌላ የግሪክ ደራሲ የኤርትራ ፔሪፕለስን በጻፈ ጊዜ በአክሱማውያን ዙፋን ላይ ዞስካሌስ የሚባል ወጣት ንጉሥ እንደነበር ታውቋል[11] ። የአገሩም መዲና በመሀል አገር የአክሱም ከተማ እንደ ነበር ተጽፎአል ። በኤርትራ ፔሪፕለስ ደራሲ ቃል ፤ ዞስካሌስ የግሪክ ቋንቋ የሚያውቅ በአገሩ ጠረፍ በአዱሊስ የወደብ ከተማ የሚካሄደውን ዓለም አቀፍ ንግድ በግል የሚቆጣጠር ብልህ ንጉሥ ነበር ።

ይህ የንጉሥ ዞስካሌስ የግሪክ እውቀትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀለት የንግድና የጠረፍ ፖሊሲ በዘመኑ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በተለይ ከግብጽና ከግሪኮ - ሮማውያን ዓለም ጋር በንግድና በባህል የነበረውን የቀረበ ግንኙነት ያመለክታል ።

[6] *Ibid.*, p. 106.

[7] Littmann, *DAE*, IV, *Inscriptions*, Nos. 4 6-11,pp. 4-35.

[8] Sergew H. Selassie, *Ethiopia*, p. 124

[9] *Ibid.*, pp. 148, 153.

[10] R. Pankhurst, *An Introduction to the Economic History of Ethiopia* (1962) pp.401-405.

[11] Huntingford, Periplus, p. 21.

በዞስካሌስ ዘመነ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ የአክሱማውያን የጠረፍ ግዛት ክልል በቀይ ባህር ዳርቻ በሰሜን ከዛሬው ፖርት ሱዳን አካባቢ ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ የኤደን ባህረ ሰላጤ ዳርቻ ይደርስ እንደነበር ተጽፎአል [12] ። በተጨማሪም በወቅቱ በቀይ ባህር ዳርቻ የአዱሊስ ዓለም አቀፍ የወደብ ከተማና ንግድ በአክሱማውያን መንግሥት ቁጥጥር ስር እንደነበር ተመልክቷል [13] ።

ከዘመነ ዞስካሌስ በኋላ የአክሱማውያን መንግሥት በሁለቱም የቀይ ባህር ጠረፎች ማለትም በሰሜን ኢትዮጵያና በአረቢያ የነበረውን የግዛት ስፋት እንዲሁም በኢትዮጵያና በግሪኮ-ሮማውያን ዓለም መካከል በንግድ ፤ በቋንቋ ፤ በባህልና በሃይማኖት እያደገ የሚሄደውን የጂኦፖለቲካ መስተጋብር የበለጠ የሚያሳየን በአዱሊሱ የድል ሀውልት ላይ ለዝክረ አማልክት በአንድ ድል አድራጊው አክሱማዊ ንጉሥ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው ታሪካዊ ሰነድ ነው ።

በአዱሊስ የድል ሀውልት ላይ ዘዩስ ፤ አሬስና ፖሲደን ለተባሉ የግሪክ ታዋቂ አማልክት ክብር የመታሰቢያ ጽሑፍ ያስቀመጠው አዋጊው የአክሱማውያን ንጉሥ በዛሬ የደቡብ ኤርትራ ደጋማ አካባቢ በጽሑፉ ስሙ በግልጽ ካልተጠቀሰ ስፍራ ተነስቶ በሰሜን ኢትዮጵያና አረቢያ በእግርና በመርከብ ጦር ያካሄዳቸውን ብዙ የጠረፍ ፀጥታና የግዛት ማስፋፊያ ዘመቻዎችን እንደሚከተለው ይዘረዝራል ። በጽሑፉ ቃል ፤ ንጉሡ ፤

በአንደኛው ዘመቻ በዛሬ ትግራይና ጐንደር አካባቢዎች፤ ጋዝ ( ግዕዝ ወይም አጋዚያ ) ፤ አጋሜ ፤ አዋ ( አድዋ) ፤ ሰግይ ፤ ትእሞ ፤ ጋምቤላ ፤ ዘንገበን ፤ አገበ ፤ ትማ ፤ አታገውስ ፤ ከላና ሰሜን ተብለው የሚጠሩ አስራ ሁለት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን በመንግሥቱ ግዛት ስር አስገባቸው ።

በሁለተኛው ዘመቻ ፤ በሰሜን ምዕራብ በግምት በቀይ ባህርና በአትባራ ወንዝ መካከል ለዘን ፤ ዘአ ፤ ገበለ ፤ አትልሞ ፤ ቤጃና ተንገናይቴ ተብለው የሚጠሩ ስድስት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን በመያዝ የመንግሥቱን የወሰን ክልል በአባይ ሸለቆ እስከ ኑቢያና ግብጽ ጠረፎች አስፋፋ ።

በሦስተኛው ዘመቻ ከትግራይ በስተ ደቡብ ምሥራቅ በግምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ኤደን ባህረ ሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በእጣን ምርትና ንግድ ታዋቂ በነበረው ምድር አነን ፤ ምጤን ፤ ሰሰአ ፤

[12] Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 79,86, 94; *Kobishchanov*, *Axum*, pp. 55,58-59.

[13] *Ibid.*, *Axum*, p. 57



ርሀሲና ሰለቴ ተብለው የሚጠሩ አምስት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን የመንግሥቱ ግዛቶች አደረጋቸው ።

በአራተኛው ዘመቻ የንጉሡ ጦር በእግርና በመርከብ ከአፍሪካ አህጉር ቀይ ባህርን ተሻግሮ በምዕራብ አረቢያ ጠረፍ በሰሜን ምዕራብ በወቅቱ የሮማውያን ይዞታ ከነበረው ከለኡኮመ ( Leuki - Kome ) ወደብ ጀምሮ በምሥራቅ እስከ ሳባ አገር በደቡብ ደግሞ እስከ የባቤልማንደብ ሰርጥ አካባቢ ድረስ ዘመቻ በማካሄድ በመካከላቸው ኪናይዶኮልፒቴና አራብቴ ተብለው የሚጠሩ ሁለት ስትራቴጂያዊ የጠረፍ አገሮችን የመንግሥቱ የባህር ማዶ ቀበሌዎች አድርጎ በቀጥታ ያዛቸው ።

ይህ በአክሱማውያን ጦር በአረቢያ የተካሄደው ዘመቻ የጂኦፖለቲካ ማብራሪያ ይጠይቃል ። በዚህ ጉዳይ በ30 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ግብጽን ኮሎኒያቸው አድርገው እንደያዙ ይታወሳል ። ከዚያ በኋላ በ100 ዓመተ ምህረት አካባቢ በግብጽና በሕንድ መካከል በቀይ ባህር መስመር ላይ ይካሄድ የነበረውን ዓለም አቀፍ ንግድ ለመቆጣጠር እንዲያስችላቸው ሮማውያን በባህሩ ምሥራቃዊ ዳርቻዎች የተወሰኑ የአረቢያ ወደቦችን ያዙ [14] ።

ይህ ሁኔታ በተፈጥሮ አቀማመጡ የዓለም ጂኦፖለቲካ ማዕከል የሆነውን ቀይ ባህርን ከአረቢያ ጋር በወቅቱ ሦስት የዓለም ኃያላን አገሮች በነበሩ በሮማውያን ፤ በፋርሳውያንና በአክሱማውያን የአፄ መንግሥታት መካከል በንግድና በኃይል ሚዛን ጥያቄ የጅኦፖለቲካ ትግል ሜዳ አደረገው ። [15] በመሆኑም በመጨረሻ አክሱማውያን በምሥራቃዊ የቀይ ባህር ዳርቻ የአረቢያን የኪናይዶኮልፒቴና የአራብቴን እስትራቴጂያዊ የጠረፍ አገሮች በቀጥታ ይዘው በተወዳዳሪ ዓለም አቀፍ ኃይሎች ላይ ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር የተገደዱ ይመስላል [16] ።

በዚህ ነገር ከዘመነ ደአማት ጀምሮ በአረቢያ ሚናውያን ፤ ሳባውያን፤ ካታባውያን ፤ ህምያራውያንና ሃድራማውያን የተባሉ እርስ በርሳቸው ዘወትር ለኃይል ሚዛን የሚዋጉና በዕጣን ምርትና ንግድ የተሰማሩ ንዑስ ሴማዊ የአረቢያ መንግሥታት እንደነበሩ አይዘነጋም ።

ከእነዚህ ንዑሳን የአረቢያ አገሮች ሳባውያን በእርስ በርስ ጦርነት ጊዜያዊ የኃይል ሚዛን አግኝተው የአረቢያ አውራ መንግሥት በመሆን ለተወሰነ ጊዜ በኢትዮጵያ ከደአማታውያን መንግሥት ጋር በንግድና

[14] Sergew H, Selassie, *History*, p. 72.

[15] Drewes, *Inscriptions*, p. 105; Kobishchanov, *Axum*, pp. 46, 59.

[16] *Ibid.*, *Inscriptions*, p. 106.

በባህል የቀረበ ግንኙነት ለመፍጠር እንደቻሉ አሁን በዘመናችን ከጥንታዊ ደአማታውያን ከተሞች በአርኪኦሎጂያዊ ጥናት የተገኙና ከዚህ በላይ የተገለጹ የሳባውያን ታሪካዊ ቅርሶች ማስረጃዎች ናቸው ።

ነገር ግን ከላይ እንደተገለፀው በዓመተ ዓለም መጨረሻ ምዕተ ዓመታት በግብጽ ቶለማዊ ግሪኮች ለንግድና ለአደን ተግባራት ከአረቢያ ይልቅ ለአፍሪካ ቀንድ ሁኔታዎችና ምርቶች የቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ፤ በቀይ ባህር የንግድ መስመር ላይ በግብጽና በሕንድ መካከል ቀጥተኛ የሆነ የንግድ ግንኙነት በመፍጠር በአካባቢው በአንድ በኩል ለአረቢያ ንዑስ አገሮች ሂደታዊ ድክመትና ውድቀት በሌላ በኩል ደግሞ ለአክሱማውያን መንግሥታዊ ዓለም አቀፍ ዕድገትና መስፋፋት አመቺ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታዎች እንደፈጠሩ ይታወሳል ።

በዚህ ጊዜ በደቡብ አረቢያ ጠረፍ አካባቢ በተለይ አዲሱ የህምያራውያን ንዑስ መንግሥት ( Himyarite State ) ተነስቶ በሳባውያን መንግሥት ላይ የኃይል ሚዛን በማግኘት በአንድ በኩል መላ አረቢያን ከስሩ ለማደራጀት በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ኃይሎችን በተለይም የሮማውያንንና የአክሱማውያንን ጂኦፖለቲካዊ ግፊት ለመከላከል ያልተሳካ ብሔራዊ ትግል ጀመረ ።

በዚህ ወቅት በደቡብ አረቢያ "ሀበሻ" ፤ " ሀበሻት " ፤ "ሀበሳት" ወይም " አበሻ" በሚሉ ልዩ ልዩ ስያሜዎች የሚታወቅ አንድ የጠረፍ አገር ከአራብቴ በስተምሥራቅ ከህምያሪያ በስተምዕራብ ከሳባ በስተ ደቡብ ነበር ።

በ250 አካባቢ በአረቢያ በሳባ ጽሑፍ " የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደራት " በኢትዮጵያ ደግሞ በግዕዝ ጽሑፍ " የአክሱም ንጉሥ ገዳር " ተብሎ በአንድ ወቅት በሁለት ልዩ ስፍራዎችና ቋንቋዎች በሁለት ልዩ የስም አጠራሮች የሚታወቅ አንድ የአክሱማውያን ንጉሥ እንደ ነበር ይታወሳል ። [17]

ነገር ግን በአዱሊስ ሰነድ በአረቢያ ከተጠቀሱ የለኡኮመ ፤ የኪናይደኮልፐቴና የአብራቴ አገሮች ጋር የሳባ ፤ የሀበሻና የህምያሪያ አገሮች አብረው አልተጠቀሱም ። አሁን ደግሞ ስለ " ሀበሾችና አክሱማውያን ንጉሥ ገደራት " በአረቢያ በሳባ ቋንቋ በተጻፈው ዜና መዋዕል ከሀበሻ ፤ ከህምያሪያና ከሳባ አገሮች ጋር ለኡኮመ ፤ ኪናይደኮልፐቴና አራብቴ አልተጠቀሱም ።

[17] Jamme, Sabaean Inscriptions, p. 123; A Caquot et, A. J. Drewes, " Les Monumentts Recueillis A Maqalle", *Annales D' Ethiopie*, vol. 1(1955), pp. 33,37.



በመሆኑም በአረቢያ የሀበሻ ወይም የአበሻ አገር የአክሱማውያን የባህር ማዶ ይዞታ የሆነው በአዱሊስ በሰነድ ከተጠቀሱ ከኪናይደኮልፐቴና አራብቴ አገሮች መያዝ በኋላ እንደሆነ መገመት ይቻላል ።

ስለ " ሀበሾችና አክሱማውያን ንጉሥ ገደራት " በሚናገረው ጽሑፍ አክሱማውያን በአረቢያ ከሀበሻ ግዛታቸው አጠገብ ከበስተምስራቅ የሚገኘውን የህምያራውያን አገር ጨምረው ለመያዝ በመጀመሪያ ደረጃ የተሳካ ወታደራዊ እርምጃ እንደወሰዱ ተመልክቷል ። ይሁን እንጂ በመጨረሻ ህምራያውያንና ሳባውያን በአክሱማውያን ላይ ህብረት ፈጥረው ጊዜያዊ የድል ሚዛን ስለአገኙ አክሱማውያን በሰላም ውል ተስማምተው ለጊዜው ከህምያሪያ ወደ ሀበሻ ግዛታቸው እንደተመለሱ የተባለው ሰነድ ይገልጻል ። [18]

ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ንዑስ የሳባና የህምያሪያ አገሮች በአጠገባቸው ከነበረው ከሃድራማት ጋር በአክሱማውያን እጅ ገብተው እስከ 575 ድረስ ገባር የባህር ማዶ ግዛቶች እንደሆኑ የሦስቱ አክሱማውያን ነገሥታት የኢዛና ፤ የካሌብና የአብርሃ ዜና መዋዕሎች ያሳያሉ ።

የአዱሊስን የድል ሀውልት የተከለው የአክሱማውያን ንጉሥ በሁለቱ የቀይ ባህር ጠረፎች በሰሜን ኢትዮጵያ የጀመረው ታሪካዊ የአገር ግምባታ ፖሊሲና የተግባር እርምጃ እስከ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ በሁሉም አቅጣጫ ተጠናክሮ ወደ ፊት እንደቀጠለ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የሳባ ሰነድ ፤ በኋላ ደግሞ የአክሱማውያን ነገሥታት የአፄ ስምብሩትህስ ፤ የአፄ ኢዛና ፤ የአፄ ካሌብና የንጉሥ አብርሃ ዜና መዋዕሎች ከኮስማስ ዘገባ ጋር ታሪካዊ ማስረጃዎች ናቸው ። [19]

በዚህ ረገድ አንደኛ ፤ ከዚህ በላይ በአዱሊስና በሳባ ሰነዶች እንደተመለከተው ፤ አክሱማውያን የቀይ ባህርን ሁለቱንም የምዕራብና የምስራቅ ጠረፎች በቀጥታ ይዘው በእስትራቴጂ ፤ በንግድና በጂኦፖለቲካ ለ አላዊ ፖሊሲ በመካሄድ በዘመኑ ዓለም በብቃት ብሔራዊ ጥቅምና ክብር አስከብረው ኖሮዋል ።

ሁለተኛ ፤ በ270ዎቹ ዓመታት በግሪክ ቋንቋ በተጻፈ ዜና መዋዕሉ "የአክሱማውያን ንጉሠ ነገሥት ስምብሩትህስ ታላቁ" የሚለው የአገር መሪው መንግሥታዊ ስመ ማዕረግ የአክሱማውያን መንግሥት በጐሳ ፤ በቋንቋ ፤ በኢኮኖሚ ፤ በድርጅትና በባህል ብዙ አገሮችንና ሕዝቦችን ያቀፈ በሀውርያዊ የአፄ መንግሥት ፤ ሕብረተሰብና ሥርዓት እንደነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ያመለክታል ።

[18] *Ibid.*, Sabaean *Inscriptions*, pp. 132-33.

[19] Kobischchanov, *Axum*, p. 54.

ሦስተኛ ፤ በአራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ “ የአክሱም ፤ የሀሚር ፤ የረይዳን ፤ የኢትዮጵያ ፤ የሀበሻ ፤ የሳባ የሰልሄን ፤ የፅያሞ ፤ የቤጃ፤ የካሱ ንጉሠ ነገሥት ” የሚለው የአፄ ኢዛና መንግሥታዊ ስመ ማዕረግ በዘመኑ የአክሱማውያን መንግሥት የሦስቱ አጉራባች የአረቢያ የኢትዮጵያና የአባይ ሸለቆ የበላይ ሥርዓት እንደነበር ያሳያል ።

አራተኛ ፤ በስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ “ የአክሱም ፤ የካሱ ፤ የረይዳን ፤ የሳባ ፤ የሰልሄን ፤ የትአሞ ፤ የየመን ፤ የትሃማት ፤ የራባም ፤ የቤጃ ፤ የኖባ ፤ የአራባት ንጉሥ ” የሚለው የአፄ ካሌብ መንግሥታዊ ስመ ማዕረግ በዘመኑ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ አንድ ታላቅ የተባበረ የቀይ ባህር ፤ የአረቢያ ፤ የአፍሪካ ቀንድና የአባይ ሸለቆ ዓለም አቀፍ ኃይል እንደነበር በግልጽ ያሳያል ።

አምስተኛ ፤ በ540ዎቹ “ የሳባ ፤ የድሁረይዳን ፤ የሃድራማዊት ፤ የየመን ፤ የአረቦች ደጋና የትሃማት ንጉሥ ” የሚለው በአረቢያ የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት እንደራሴ.የአብርሃ ንጉሣዊ ስመ ማዕረግ ይህንኑ ቲሲስ የበለጠ ያጠናክራል ።

ስድስተኛ ፤ በተጨማሪም በ525 የግሪኩ ነጋዴ ኮስማስ የአክሱማውያንን ቤተ መንግሥት በጎበኘው ጊዜ በአፍሪካ ቀንድ በሰሜን ምዕራብ በተከዜና በአባይ ወንዞች መካከል የአገውም አገር በአክሱማውያን የፖለቲካ ተፅዕኖ ስር ነበር ። [20]

ባጭሩ የአክሱማውያንን የግዛት ክልል በሚመለከት ፤ የዘመኑ ዜና መዋዕሎች ከኮስማስ ማስረጃ ጋር እንደሚያሳዩን ፤ በዘመነ ክርስትና ከአራተኛው እስከ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ግዛተ አፄው በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ በነበረበት ወቅት ፤ በአፍሪካ ቀንድ በሰሜን-ምሥራቅ በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ ሰላጤ፤ በደቡብ-ምሥራቅ በታችኛው አዋሽ ሸለቆ ፤ በሰሜን በግብጽ ፤ በምዕራብ በሜሮዌና በአባይ ወንዝ የሚከለለው ቀበሌ በአፍሪካ አህጉር የመንግሥቱ መደበኛው የግዛት ክልል ነበር ። በወቅቱ ከመንግሥቱ ሰሜናዊ የጠረፍ ክልል ውጭ ግብጽ በሮማውያን ይዞታ ስር ነበር ።

## የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ሁኔታ

እስከ ዛሬ የተገኙ ጥንታዊ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች ፤ ሾጣጣ ሀውልቶች ፤ የገንዘብ ቅርሶች ፤ የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ከግሪኮ - ሮማውያን ጸሐፊዎች ስለ አካባቢው የተጻፉ መጻሕፍት ከጥንታዊ ከተሞች ጋር

[20] Cosmas, *Christian Topography*, p. 52.



በአንድነት እንደሚያሳዩት ፤ የአክሱማውያን መንግሥት በገበሬ ፤ በዕደ ጥበብ ሙያተኛ ፤ በነጋዴና በባርያ ጉልበት የተገነባ በገጠርና በከተማ የተከፈለ የኢኮኖሚ ስርዓት ነበረው ። [21]



ከ2000 ዓመታት በፊት የአክሱማውያን ሾጣጣው ሀውልት ከትግራይ


በዚህ ጉዳይ ለምሳሌ በ250 አካባቢ በድንጋይ ላይ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈው በኤርትራ በአካለ ጉዛይ አውራጃ ሠፍራ ከተባለው ከአንድ ጥንታዊ ቦታ ከቅርብ ጊዜ በፊት በፕሮፌሰር አብርሃም ድሬዊስ የተገኙ አራት መንግሥታዊ የግብር ሕጐች በዘመነ አክሱም የአገሩ አርሶ አደሮች ከምርታቸው በገበታ ፤ በገምቦና በቁና እየሰበሰቡ ከእንስሳትም በቁጥር እየመረጡ ለነገሥታትና ለካህናት ይገበሩ የነበረውን ፊውዳላዊ የዱቄት ፤ የዳቦ፤የዘይት፤ የጠላ፤የማር፤ የጠጅ፤ የላም ፤ የበግ ፤ የቅቤ፤ የሥጋ ፤ የቆዳ ፤ የልብስ፤የእንጨትና የብር ግብር ይዘረዝራሉ ። [22]

የአክሱማውያን ነገሥታትና ካህናት ከአምራቹ የሠርቶ አደር መደብ እንደዚህ በዓይነትና በጉልበት በሚሰበስቡት ሀብት ለሙታን የመታሰቢያ ተስካር ፤ እንዲሁም ለሠራተኞች የምግብ ድርጐና ቀለብ ይሰጡ እንደነበር ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የአገልግሎትና የግብር ሕጐች ጨምረው ያረጋግጣሉ ።

በተጨማሪም ከአገር በግብር ፤ በዘረፋና በጦር ምርኮ በሚሰበሰበው ሀብትና ንብረት ከፍጆት ተግባርና አገልግሎት ሲተርፋቸው አክሱማ

[21] G.W.B.Huntingford ,tr. and ed. *The Land Charters of Northern Ethiopia* 1965) P. 8; UNESCO, *African History*, II, 123-189,362-380.

[22] Drews, *Inscriptions*, pp. 30-64.



ከ2000 ዓመታት በፊት የአክሱማውያን
ሸጣጣው ሀውልት ከትግራይ

22

ውያን የገዥ መደቦች ለራሳቸውና ለአግልክቶቻቸው ክብር የሀውልትና የመቅደስ መታሰቢያ ይሰሩበት እንደነበር ዛሬ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ጥንታዊ ሾጣጣ ሀውልቶች ፤ መቅደሶችና የቤተ መንግሥት ፍራሾች ታሪካዊ ማስረጃዎች ናቸው ።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ በትግራይ በአጋሜ አውራጃ አንዛ ከተባለው ከአንድ ጥንታዊ ሥፍራ በድንጋይ ላይ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው አንድ ታሪካዊ ጽሑፍ በዘት የሚባል የአገቦ አገር ንጉሥ አንድ የመታሰቢያ ሀውልት ሲያሰራ የአገሩ ሰዎች በሕብረት ወጥተው ሀውልቱን ወደሚቆምበት ቦታ ተሸክመው ከመውሰዳቸውም በላይ ለሀውልቱ ተከላ በዓል ለተዘጋጀው ድግስ 20600 ዳቦዎችንና 520 የጠላ ገምቦዎችን ጨምረው መስጠታቸውን ይገልጻል ። [23]

ከመጠራ ጥንታዊ ከተማ የተገኘው አንድ ሌላ ጽሑፍ ደግሞ አንድ አገዘ የሚባል የአካባቢው ሹም ለአባቶቹ ክብር የመታሰቢያ ሀውልት ሲያቆም አውአ ፤ አለፎና ሰለበ ተብለው የሚጠሩ የአካባቢው ሕዝቦች በሕብረት ወጥተው ሀውልቱን ወደሚተከልበት ቦታ ወሰዱት ይላል ። [24]

እንዲሁም በአራተኛው ምዕተ ዓመት አፄ ኢዛና ስድስት የቤጃ አመጸኛ ገባር ነገሥታትን ከነሰዎቻቸው በቅጣት እርምጃ ከአገራቸው አንስቶ በመሀል አገር ወደ ሌላ ቦታ ባጋዛቸው ጊዜ ከሥጋና ከመጠጥ ቀለብ ጋር ለብዙ ወራት በየቀኑ 22,000 ህብስት ማለትም የዳቦ ድርጎ (ቀለብ) ይሰጣቸው እንደነበር ከአክሱም ከተማ የተገኘው አንድ የአፄው ዜና መዋዕል ይገልጻል ። [25]

በአጭር አነጋገር እነዚህ ከሠፍራ፤ ከአንዛ ፤ ከመጠራና ከአክሱም ጥንታዊ ከተሞች የተገኙ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በዘመነ አክሱም በኢትዮጵያ ፤ ከአርሶ አደር ፤ ከባርያና ከዕደ ጥበብ ሙያተኛ ጉልበትና ጥበብ ጋር እርሻና የእንስሳት ርባታ የሕብረተሰቡ ዋና የሥራ ፤ የምርት ፤ የአገልግሎትና የባህል መሠረቶችና መሣሪያዎች እንደነበሩ ፤ የዘመኑ ታላላቅ የመቅደስ ፤ የሀውልትና የቤተ መንግሥት ሕንፃዎችም በአገሩ የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ጥበብና በሕዝብ ጉልበት በሕብረት የተሰሩ ሥራዎች እንደ ሆኑ ይጠቁማሉ ። [26]

[23] *Ibid.*, P. 67.

[24] *Ibid.*, pp. 67.-68.

[25] Littmann, *DAT*, Inscription No. 6, p. 10.

[26] Kobishchanov, *Axum*, pp. 147-150.



ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በሌላ በኩል ደግሞ የአክሱማውያን የእርሻ መሣሪያና ምርት ማለትም የዘመኑ የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ እንደነበር የሚያመለክቱ ብዙ ሁኔታዎችንና ምልክቶችን ማመልከት ይቻላል ። በዚህ ጉዳይ ለምሳሌ ፤

አንደኛ አክሱማውያን ከማረሻ ፤ ከመጥረቢያ ፤ ከፋስ ፤ ከማጭድና ከውሃ ግድብ የበለጡ የምርት መሣሪያዎችና የሥራ ዘዴዎች እንደነበሩአቸው የሚያሳዩ መረጃዎች እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኙም ። የእነዚህ የተጠቀሱት የምርት መሣሪያዎች ዓይነት የአክሱማውያን አገርና መንግሥት የዳበረ የእርሻ ፤ የኢኮኖሚና ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት የነበረው ሕብረተሰብ እንደሆነ አያመለክቱም ።

ሁለተኛ በአክሱም ከተማ ከድንጋይ የተሰሩ ታላላቅ መቅደሶች ሾጣጣ ሀውልቶች ፤ የቤተ መንግሥቱ ሕንፃዎች ፤ ፊደልና ጽሕፈት ፤ ከሸክላ የተሠሩ ልዩ ልዩ ዓይነት የጌጣጌጥና የቤት ዕቃዎች ከወርቅ ከነሐስ ከመዳብ ከብር ከተሰሩ ገንዘቦች ጋር በጥንታዊት ኢትዮጵያ በአንፃራዊ አባባል የዕደ ጥበብን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የሚያመለክቱ መረጃዎች ቢሆኑም ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአገሪቱ የእርሻ የኢንዱስትሪና የመገናኛ መሣሪያዎችና ሥራዎች በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ እንደነበሩ የሚያመለክቱ መረጃዎች የሉም ።

በዚህ ረገድ በዘመኑ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ በሚላኩ በንግድ ዕቃዎች ዝርዝር በሙያ ጥበብ የተሰሩ የእርሻና የኢንዱስትሪ ውጤቶች እስከ ዛሬ ለዓይነትም አልታዩም ። የዘመኑ የጽሑፍ መረጃዎች ጨምረው እንደሚያመለክቱት ፤ አክሱማውያን ነጋዴዎችና ወታደሮች ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በሰው እጅ በተሠሩ መንገዶችና ድልድዮች ላይ ሳይሆን በሲራራ ንግድ መንገድ በየኬላው ከወንበዴዎች በቡድን እየተከላከሉ በእግር ጉዞ ጫካዎችን ሜዳዎችን ፤ ሸለቆዎችንና ወንዞችን በማቋረጥ ነበር ።

ይህ አክሱማውያን በእርሻ ፤ በዕደ ጥበብ ፤ በኢንዱስትሪና በመገናኛ መስኮችና ሥራዎች የነበራቸው ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ በተጨባጭ የሚያሳየን አንድ መሠረታዊ ነገር በጥንታዊት ኢትዮጵያ የሳይንስና የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃ በጣም ኋላ ቀር እንደነበር ነው ።

## የተፈጥሮ ሀብት ሚና

በሌላ በኩል አክሱማውያን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ፤ በዕደ ጥበብ ባእርሻ ፤ በኢንዱስትሪና በመገናኛ መስኮችና ሥራዎች ለነበራቸው ዝቅ

ተኛ የዕድገት ደረጃ የአገሪቱ ታላቅ የተፈጥሮ ሀብትና በዘመኑ በቀይ ባህር ወደቦችና በሮች የነበረው ታላቅ ዓለም አቀፍ ንግድ መካካኞዎች በመሆን አገልግሎአል ።

በተፈጥሮው የኢትዮጵያ ምድር በበረሃ ፤ በቆላ ፤ በወይና ደጋና በደጋ የአየር ንብረት ፤ ማዕድናት ፤ እንስሳት ፤ አራዊት ፤ አእዋፍ ፤ ነፍሳትና አዝርዕት የታደለ አካባቢ መሆኑ ተደጋግሞ በትክክል የተነገረለት ሐቅ ነው ። ይህ የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦም ተጽዕኖም ሲያደርግ ኖሮአል ።

በዚህ ረገድ ከጥንታዊ ግብጻውያን ዘመን ጀምሮ በየጊዜው በዓለም ላይ የተነሱ የግብጽ ፤ የግሪክ ፤ የሮማውያን ፤ የአረብና የአውሮፓ አገር ጎብኝዎች ፤ ነጋዴዎችና ጸሐፊዎች ለምሳሌ የጥንታውያንን የአገርና የሕዝብ ገጽታዎች ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በስዕል ቀርጾ ያቆየው የግብጽ መርከበኛው ፤ <u>የኤርትራ ፔሪፕለስ ደራሲ</u> ፤ በ520ዎቹ ጸሐፊው ኮስማስ ፤ በ530ዎቹ መልእክተኛው ኖኖሱስ ፤ በ1330ዎቹ የታሪክ ደራሲ አልማሪ ፤ በ1430ዎቹ ሌላ የታሪክ ደራሲ ማክሪዚ ፤ በ1520ዎቹ መልክተኛው አልቫሬዝ ፤ በ1530ዎቹ የአህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ጸሐፊው አረብ ፋቂህ ፤ በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት የፖርቱጋል ጸሐፊዎች ፤ በአስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት አገር ጎብኚው ብሩስ ሁሉም በየዘመናቸው ይህንን የአገሪቱን ታላቅ የአየር ንብረት ፤ የአፈር ፤ የውሃ ፤ የሜካ ፤ የላም ፤ የአህያ ፤ የፈረስ ፤ የበቅሎ ፤ የፍየል ፤ የበግ ፤ የዶሮ ፤ የዝሆን ፤ የአንበሳ ፤ የግመል ፤ የኢጋዘን ፤ የአውራሪስ ፤ የጉሽ ፤ የወርቅ ፤ የዕጣን ፤ የገብስ ፤ የስንዴ ፤ የጤፍ ፤ የፍራፍሬ - ሀብት ብዛትና ስፋት በልዩ ልዩ ደረጃዎችና መንገዶች በመዘርዘርና በማድነቅ መዝግቦአል ። ለምሳሌ ፤

ከእነዚህ ፀሐፊዎች አንዱ ኖኖሱስ በ533 ከአገሩ ከባይዛንታውያን አፄ ተልኮ ወደ አክሱማውያን ቤተ መንግሥት በመጣ ጊዜ በአዱሊስና በአክሱም ከተሞች መካከል በአድዋ አካባቢ በመንገድ ዳር በ5000[27] የሚቆጠሩ ዝሆኖችን መንጋ በአንድ ቦታ ማየቱን መዝግቦአል ።

ምንም ለከፍተኛ የኢንዱስትሪ ምርት ጥሬ ዕቃ ሆኖ በአገልግሎት ላይ ባይውል ይህ ታላቅ የኢትዮጵያ አካባቢያዊ የተፈጥሮ ሀብት ለአክሱማውያንና ከእነርሱም በኋላ ለተነሱ ተወላጅና ወራሽ ኢትዮጵያውያን የፍጆት ኢኮኖሚ ዋና መሠረት በመሆን ሲያገለግል ኖሮአል ።

[27] Sergew H. Selassie, *History*, p. 139.



በተመሳሳይ ማህበራዊ የዕድገት ጉዳናና ደረጃ እንደ አለፉ የዓለም ጥንታዊ መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ሁሉ የአክሱማውያን የአፄ መንግሥትም ከፍተኛ አምራች መንግሥትና ስርዓት ሳይሆን የከፍተኛ ግብር ንግድ ፤ ፍጆትና አገልግሎት ሕብረተሰብ ነበር ።

በዚህ ረገድ የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት በአራተኛው ምዕተ ዓመት በአፄ ኢዛና ዘመነ መንግሥት በሥፍራ ከመስፋፋት አኳያ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ደርሶ በነበረበት ወቅት በሰሜን ኢትዮጵያ ፤ በአረቢያና በአባይ ሸለቆ የአጓዛት ፤ የገበዝ ፤ የፀረኔ ፤ የሐማሴን ፤ የሀበሻ ፤ የሳባ ፤ የአራብቱ ፤ የረይዳን ፤ የሀምያር ፤ የቤጃ ፤ የባርያ ፤ የሚሮዌ ፤ የዕያሞና የኖባ አገሮችና ሕዝቦች በአክሱም መዲና ለማዕከላዊው የአፄ መንግሥት ከግብርና ከንግድ ለሚመጣው ሀብት ዋና ምንጮች ነበሩ ።

እነዚህ አገሮችና ሕዝቦች በአመጽ ወይም በሆነው ሁሉ ምክንያት ዓመታዊና ወቅታዊ የግብር አገልግሎት ሲከለክሉ ብሎም በአካባቢያቸው የሲራራ ነጋዴዎችና መንገደኞች ሲዘረፉ አክሱማውያን ነገሥታትና ወታደሮች በቅጣት እርምጃ የዘረፋ ዘመቻ ያካሄዱባቸው እንደነበር በየዘመናቸው አፄ ኢዛናና አፄ ካሌብ በእነዚህ በተጠቀሱ አገሮችና ሕዝቦች ላይ ያካሄዱባቸው ጦርነቶች ጥሩ ታሪካዊ ማስረጃዎችና ምሳሌዎች ናቸው ።

በእነዚህ ጦርነቶች ወቅት ለምሳሌ ከጸረኔ ዘመቻ በውጊያ ሂደት ከሞቱትና ከሸሹት ሌላ 205 ሰዎችን ከ32,727 እንስሳት ጋር ፤ ከኖባ ዘመቻ ደግሞ 629 ሰዎችን ከ61,610 እንስሳት ጋር አፄ ኢዛና በምርኮ እንደወሰዳቸው ዜና መዋዕሎቹ ይገልጻሉ ። በተጨማሪም ለአመጸኛ ገባር የቤጃ ነገሥታት በቅጣት እርምጃ በተጋዙበት መሀል አገር ለመተዳደሪያቸው አፄ ኢዛና 25,140 ላሞችን እንደሰጣቸው ይታወሳል ።

ይህ ታላቅ የዘረፋና የግብር ሀብት ራሱ በአንድ በኩል የግብርና የዘረፋ ስርዓት ለአክሱማውያን መንግሥት አንድ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንደነበር በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ ለዘረፋም ሆነ ለግብር የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑን በተጨባጭ የሚያመለክት አንድ ታሪካዊ ማስረጃ ነው ።

## <u>የንግድ ሚና</u>

የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት የግዛትና የሀብት መጠን በተመለከተ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ፤ በቀይ ባህር ፤ በአረቢያና

በአባይ ሸለቆ የበላይ ዓለም አቀፍ ኃይል ሆኖ የተነሳው በፊት በአካባቢው የነበሩ ሁለት ጥንታዊ የሳባና የሚሮዌ መንግሥታት በተለያዩ በራሳቸው ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ከወደቁ በኋላ መሆኑን በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ ተመልክቷል ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት የኢትዮጵያ የአክሱማውያን መንግሥት እንደ ዚህ አንድ የዓለም ኃይልና ሥርዓት ሆኖ እንዲያድግ ተጨባጭ ኢኮኖ ሚያዊ አስተዋጽኦ ከአደረጉ አያሌ ነገሮች አንዱ ከሳባና ከሚሮዌ መንግ ሥታት ውድቀት በኋላ በቁጥጥሩ ስር የዋለው የአካባቢው ዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓት ነበር ። በዚህ ጊዜና አኳያ ፤

አንደኛ ፤ በኢትዮጵያና በአረቢያ ከወርቅ ፤ ከብር ፤ ከነሐስና ከመ ዳብ ተቀርጸው በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉባቸው የአክሱማውያን ገንዘቦች በሀውርታዊ የአፍሪካ ቀንድ ፣ የቀይ ባህር ፤ የአረቢያና የአባይ ሸለቆ አገሮችን በአንድ ማዕከላዊ የአፄ መንግስትና ሥርዓት የሚያይዙ ተግባራዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሣሪያዎች በመሆን ማገልገል ጀመሩ።

ሁለተኛ ፤ የአፍሪካ ቀንድ ጥንታዊ የአዱሊስ ፤ በባቤልማንደብ ስርጥ ዳርቻ (በዛሬው ጂቡቲ የራስሲያን ወደብ በሚገኝበት ቦታ የነበረው) የድሬ ፤ የዛሬው የዜላ ወደብ በሚገኝበት ቦታ የነበረው የአዋልት እና የዛሬ በርበራ በሚገኝበት ቦታ የነበረው የማለኦ ጥንታዊና ታላላቅ ዓለም አቀፍ የንግድ ወደቦች ከአካባቢው ታዋቂ የቅመማቅመም ፤ የዕ ጣን ፤ የከርቤና የሙጫ ምርትና ንግድ ጋር በአክሱማውያን የአፄ መን ግሥት ቁጥጥር ስር ዋሉ ። [28]

በጥንታዊ የአፍሪካ ቀንድ ንግድ ነገር ፤ በቅድም ተከተል በ332 እና በ30 ዓመተ ዓለም በአካባቢው የግብጽ በግሪኮችና በሮማውያን እጅ መውደቅ የቀይ ባህርና የአፍሪካ ቀንድ አገሮችንና ሕዝቦችን በር ለግ ሪኮ - ሮማውያን ንግድ ፤ ባህልና ጸሐፊዎች እንደከፈታቸው አይዘነጋም ።

በዚህ ረገድ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት የአክሱማውያን መንግሥት በአካባቢው የበላይ ዓለም አቀፍ ኃይልና ሥር ዓት እስኪሆን ድረስ ያለውን የቀይ ባህርና የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ለማ ወቅ የሚረዱ የጽሑፍ መረጃዎች ከግብጽ በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክን ያቶች አካባቢውን ከጐበኙ የግሪክና የሮማውያን ጸሐፊዎች በተለ ይም ፤—

1. በ130 ዓመተ ዓለም ገደማ ከአጋትሃርቻይድ ( Agatharchide )
2. በ100 ዓመተ ዓለም ገደማ ከአርቴማዶር ( Artemidore )

[28] *Ibid.*, pp. 36-41; Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 49, 79, 86.



3. በዓመተ ዓለም መጀመሪያ ምዕተ ዓለም ከድኦድርና ከስትራቦን (Diodore and Strabon)
4. በ80 ዓመተ ምህረት ገደማ ከአዛውንቱ ፕላኔ ( Pline the Elder )
5. በ150 ከክሉድዮስ ቶለማይ ( Claudius Ptolemy)
6. በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ከኤርትራ ፔሪፕለስ ደራሲ
7. በ520 ዎቹ ከኮስማስ ( Cosmas ) የተገኙ ቁልፍ ታሪካዊ ጽሑፎች ናቸው ። [29]

እነዚህ ግሪኮ - ሮማውያን ጸሐፊዎች ከምድረ ግብጽ በታች በአባይ ሸለቆና በአፍሪካ ቀንድ የተለያዩ ነባር ጐሳዎችንና ማህበረሰቦችን መሠ ረታዊ የጐሳ ፤ የስም ፤ የቋንቋ ፤ የመልክና የዘር ገጽታዎችን ለይተው ሳይጠቅሱ በማህበረሰቦቹ ባህላዊ ሥራና ልምድ መሠረት ብቻ ሥራ ሥር ፤ እንጨት ፤ ሳር ፤ ኤሊ ፤ አንበጣ ፤ ሰጐን ፤ አሳ ፤ ዝሆን የሰው ስጋ የሚበሉ ወገኖች ማለትም በቅደም ተከተል በጸሐፊዎች ስያሜና ትርጉም ፤ The Rhizophages, the Helophages, the Agriphages, the Chetenophages, the Acridophages, the Struthophages, the Ihthyophages, the Elephantophages, and the Kreophages :-

እያሉ በሽፍን በመግለጻቸው የማህበረሰቦቹ ጊዜያዊና ጐሳዊ የአ ፏፏርና የአበላል ልምድ በማህበራዊ የዕድገት ሂደት ከተለወጠ በኋላ በታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ እነዚህ ጥንታዊ የአፍሪካ ሕዝቦች እነማን እንደ ነበሩ ወይም በኋላ ምን እንደሆኑ በትክክል ለማወቅ የማይቻል ነገር ሆኖ አል ።

ነገር ግን ግሪኮ- ሮማውያን ጸሐፊዎች በአፍሪካ ቀንድ ከእነዚህ በባህላዊ ግብራቸው ብቻ ከተገለጹ ዘላንና አዳኝ ማህበረሰቦች በስተቀር በማህበራዊ ዕድገት ወደከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሦስት ሌላ ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን ማለትም ፤

1. በደቡብ ምሥራቅ በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በወቅቱ “ ከቅመ ማቅመም ጫፍ” ወይም ከዛሬው ጉአርዳፋይ ጫፍ እስከ የዛንዚባር ደሴት በሚደርሰው ምድር የባንቱን ጥንታዊ “የአዘኒያ” ሕዝብንና መንግሥትን ፤

2. በምሥራቅ በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ ሰላጤ ዳርቻዎች በግ ምት ከአዱሊስ እስከ “ ቅመማቅመም ጫፍ ” በሚደርሰው የጠረፍ ቀበሌ ደግሞ ነባር ትሮጅሎዳውያንና በርበራውያን ተብለው በሁለት ተለዋጭ ስሞች የሚታወቁ ሕዝቦችን ፤

[29] *Ibid.*, *Histoire Sommaire*; H. Labrousse, “ Enquete et Decouvertes D, D'Obock A Doumeira,” *AE.*, vol. II (1978), pp. 75-77; *J.* Desanges,“ Le Littora; Africain Du Babil Mandeb D' Apres Les Sources Grecques et Latines.”, *AE*, Vol. II (1978), pp. 83-101.

3. በሰሜንና በምዕራብ አክሱማውያንና ኢትዮጵያውያን ተብለው በሁለት ተለዋጭ ስሞች የሚጠሩ ሕዝቦችን ለይተው በወል ስሞቻቸው ገልጸዋል ። [30]

በግሪኮ - ሮማውያን መረጃዎች መሠረት ከዘመኑ የአፍሪካ ቀንድ ነባር ሕዝቦች የትሮጅሎዶ- በርበራውያን በአካባቢው ከጥንታዊ ፑንታውያን በዘመኑ ደግሞ ከአክሱማውያን ጋር በዘር ፣ በሃይማኖትና በባህል የቀረበ ግንኙነት የነበራቸው ይመስላል ። በዚህ አኳያ ትሮጅሎዶ- በርበራውያን እንደ ጥንታዊ ፑንታውያን በቅመማቅመም ፣ በዕጣንና በከርቤ ምርትና ንግድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ሰዎች ነበሩ ። [31] በተጨማሪም የትሮጅሎዶ- በርበራውያን ሃይማኖትና አማልክት ከጥንታዊ የፑንትና የግብጽ ሃይማኖቶችና አማልክት ጋር ተመሳሳይ ነበሩ። [32]

በኋላ የአክሱማውያንና የትሮጅሎዶ - በርበራውያን ግንኙነት በተመለከተ ሁለቱም ወገኖች በዘር በኢኮኖሚና በባህል የተቀራረቡ መሆናቸውን ፣ ከአገራቸው ደጋማ አካባቢ ሄደው ብዙ አክሱማውያን ሠራተኞችና ሰፋሪዎች በትሮጅሎዶ - በርበራውያን ቆላማ ምድር በቅመማቅመም በዕጣንና በከርቤ ምርትና ንግድ ተሰማርተው ከነዋሪውም ሕዝብ ጋር እየተጋቡ ይኖሩ እንደነበር ግሪኮ - ሮማውያን ጸሐፊዎች ጨምረው መዝግበዋል ። [33]

<u>በኤርትራ ፔሪፕለስ</u> ደራሲ እንደ ተገለጸው ደግሞ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ገደማ የአክሱማውያን ንጉሥ ዞስካሌስ ከአገሩ ሰሜናዊ ደጋ አንስቶ በሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ እስከ "ቅመማቅመም ጫፍ" ድረስ የትሮጅሎዶ - በርበራውያንን አገር ጨምሮ በደቡብ ምስራቅ ከአዘኒያ ሉአላዊ ንዑስ የጠረፍ አገርና መንግሥት በስተቀር መላውን የአፍሪካ ቀንድ ደጋና ቆላ ከአዱሊስ ፣ ከድሬ ፣ ከአዋልትና ከማለእ የጠረፍ ወደቦችና ንግድ ጋር አጣምሮ በአንድነት ይገዛ ነበር ። [34]

በአጭር አነጋገር በዘመኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የነበረው የአፍሪካ ቀንድ የቅመማቅመም ፣ የዕጣን ፣ የከርቤ ንግድ በተለይም ከዘመነ ዞስካሌስ ጀምሮ በአዱሊስ ፣ በድሬ ፣ በአዋልትና በማለእ ታላላቅ የጠረፍ በሮች ለአክሱማውያን የአጼ መንግሥት አንድ ጠንካራ የገቢ ምንጭ ነበር ።

---

[30] *Ibid., Histoire Sommaire*, pp. 70-83.
[31] *Ibid.*, pp. 72-73.
[32] *Ibid.*, p. 74.
[33] *Ibid.*, pp. 72-73.
[34] *Ibid.*, p. 79.



ሦስተኛ ፣ የአክሱማውያን የአጼ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ በቀይ ባህር ፣ በአረቢያና በአባይ ሸለቆ ሉአላዊ ሥልጣኑን አስፋፍቶ ከመሠረተ በኋላ የአገሪቱ ታላላቅ የአዱሊስ ፣ የድሬ ፣ የአዋልትና የማለእ ዓለም አቀፍ የንግድና የባህል ወደቦች በመሀል አገር ከመጠራ ፣ በዛሬው ኮሀቴ ከነበረው ከኮሎና ከአክሱም ከተሞች ጋር ለግብጽ ለሶሪያ ፣ ለግሪክ ፣ ለሚሮዌ ፣ ለአረቢያና ለሕንድ ነጋዴዎችና ዜጎች የሥራና የመኖሪያ ሥፍራዎች ነበሩ ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑ የንግድና የባህል ዕቃዎች ከእነዚህ አገሮች ከወርቅ የተሠሩ ከ100 በላይ የሕንድ ገንዘቦች ጨምሮ አሁን በዘመናችን ከአያሌ አክሱማውያን ከተሞች ተገኝቷል ። [35]

በአክሱማውያን የአጼ መንግሥት ግዛቶችና የመሀል አገር ከተሞች ዓለም አቀፍ የንግድ ቋንቋ በዘመኑ ዓለም ከፍተኛ የሥልጣኔና የትምህርት መማሪያ የነበረው የግሪክ ቋንቋ እንደሆነ በወቅቱ በዚህ ቋንቋ የተጻፉ የአክሱማውያን ዜና መዋዕሎችና የገንዘብ ላይ ጽሑፎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው ። በአክሱማውያንና በውጭ አገሮች መካከል ይካሄድ በነበረው የንግድ ዕቃዎች ዝርዝር እንደሚታየው ደግሞ በዘመኑ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች ከውጭ ወደ አገሪቱ የሚገቡ የንግድ ዕቃዎች ግን የከፍተኛ የዕደ ጥበብ ውጤቶች ነበሩ ።

በዚህ ነገር ከአክሱማውያን አገር ወደ ውጭ አገሮች በሚላኩ በንግድ ዕቃዎች መካከል ለምሳሌ ዕብነ በረድ ፣ የዝሆን ጥርስ ፣ የአውራሪስ ቀንድና ቆዳ ፣ የጉማሬ ቆዳ ፣ ወርቅ ፣ ዝንጀሮ ፣ የኤሊ ቆዳና ባሮች መደበኛ ሸቀጣሸቀጦች ሲሆኑ ፣ ከሚሮዌ ፣ ከአረቢያ ፣ ከሕንድ ፣ ከግብጽና ከሶሪያ የወይን ፣ የስንዴ ፣ የሩዝ ፣ የዘይት ፣ የሸንኮራ አገዳ ፣ የብርጭቆ፣ የሸክላ ፣ የብረታ ብረትና የጨርቃ ጨርቅ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ እንደነበር የተለያዩ የግሪኮ - ሮማውያን ጸሐፊዎች በየዘመኑ መዝግበዋል ። [36]

ከዚህ ተጨባጭ ታሪካዊ መረጃ የምንረዳው አንድ መሠረታዊ ነገር የአክሱማውያን ሕዝብና መንግሥት በምርት ቴክኖሎጂ ረገድ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ እንደ ነበር ነው ።

## <u>የድርጅት ሁኔታ</u>

የአንድ ሕብረተሰብ የፖለቲካ የድርጅትና የባህል ሥርዓቶችና ተግባራት የሕብረተሰቡ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዓይነተኛ ውጤቶች ናቸው ።

---

[35] UNESCA, *African History*, II pp. 387-390.
[36] Kobishchanov, *Axum*, Tables 2,3,pp. 172, 175.

በመሆኑም የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት የፖለቲካ ፣ የድርጅትና የባህል ሥርዓቶችና ተግባራት ከዚህ በላይ ባጭሩ ከተገለፀው የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በቅርብ የተያያዙ ገጽታዎች ናቸው ። ለአክሱማውያን የአፄ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ፣ በቀይ ባህር ፣ በአረቢያና በአባይ ሸለቆ በአንድ የጋራ ኢኮኖሚ ሥርዓት ቋንቋና ባህል ያልተያያዙ እያሌ አገሮችንና ሕዝቦችን በአንድነት ለማስተዳደር ከሁሉ በፊት በነገሥታት ስር ጠንካራ የጦር ድርጅት አስፈላጊ ሆነ ። ሌላ መሠረታዊ የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት የሥልጣን መሣሪያ ሃይማኖታዊ ርዕዮተ ዓለም ነበር ። ሁለቱም የአክሱማውያን መንግሥት የጦርና የሃይማኖት ድርጅቶች ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የደረሱት በአራተኛው ምዕተ ዓመት በአፄ ኢዛና ዘመነ መንግሥት ነው ።

በዚህ አኳያ አፄ ኢዛና "ሰዎቼ" እያለ የሚጠራቸው መሀራ፣ሀራ፣ደመወፈልሀ ፣ ጽራእ ፣ ሀሌን ፣ ምጤን ፣ ዳኬን ፣ ለኬንና ሰብራት የተባሉ ወታደራዊ ድርጅቶች ደግሞም "አባቶቼ" የሚላቸው አርስ ፣ መህርም ፣ አስተር ፣ ብሔር ፣ ምድርና ክርስቶስ ተብለው የሚታወቁ የውጭና የአገር ውስጥ አዋማዊና መለኮታዊ አማልክት የአፄው ዜና መዋዕሎች ማዕከላዊ አካላት ናቸው ። [37]

ከእነዚህ ከአፄ ኢዛና አማልክት መካከል አርስ የግሪክ የጦር አምላክ ፣ መህርም የሴማውያን የጦር አምላክ ፣ ክርስቶስ ደግሞ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚል በሮማውያን የአፄ መንግሥት ስር ባሮች የነበሩ የአይሁዶች የሰላምና የፍቅር አምላክ ነበር ። ነገር ግን ራሱን በልዩ ልዩ ጊዜያት " ወልደአርስ"፣" ወልደ መህርም "፣ ማለትም " የአርስ ልጅ"፣ የመህርም ልጅ " እያለ የሚጠራው ዘዴኛው የጦርና የፖለቲካ ሰው አፄ ኢዛና እነዚህን አማልክት በሙሉ የራሱ የጦርነትና የቅጣት አማልክት አደረጋቸው ።

በዚህ ነገር በአክሱማውያን ነገሥታት እምነት ጦረኛው አርስ-መህምር (1) የአክሱማውያን ፈጣሪ አባት ፣ (2) በጠላቶቹ የማይሸነፍ ከሃሊ አምላክ (3) የነገሥታት አባትና አምላክ ፣ (4) የአማልክት ሁሉ አምላክ ነበር ። [38]

ባጭሩ አክሱማውያን ነገሥታት እንደዚህ የፖለቲካ ኃይላቸውና ስልጣናቸው ከምስጢራዊና ከከሃሊ አማልክት የተሰጠ ብሎም በሰዎች

[37] Littmann, DAE, *Inscriptions* Nos. 4,6-11, pp.4-35.

[38] Kobishchanov, *Axum*, p. 396.



ኃይል ፣ እንደበትና ሕግ የማይደፈር የማይሸነፍ የማይገሰፅና የማይዘለፍ ልዩ መለኮታዊ ኃይልና ስልጣን ነው በማለት ስለ አሳመኑት የአገሪቱ ሕዝብ ለነገሥታትና ለካህናት ስልጣን እንደ ባርያ ቀጥ ሰጥ ብሎ ይታዘዝ ይገዛ ነበር ።

ከዚህ በላይ በልዩ ልዩ መንገዶችና ጊዜያት የተጠቀሱት የዘመኑ የዜና መዋዕል ፣ የገንዘብ የሀውልትና የመቅደስ መረጃዎች በግልጽ እንደሚያሳዩት ፣ በአክሱማውያን ሕብረተሰብ በድርጅትና በተግባር የተሳሰሩ ሦስት ማዕከላዊ ነገሮች ነገሥታት ፣ አማልክትና ሠራዊት ማለትም መንግሥት ሃይማኖትና ጦር ናቸው ። ይህ የመንግሥት ፣ የሃይማኖትና የጦር ድርጅታዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር በኢትዮጵያ ታሪክ ከዘመነ አክሱም እስከ ታላቁ የ1966 አብዮት ድረስ መሠረታዊ ለውጥ ሳይታይበት የኖረ ጥንታዊ ክስተት ነው ።

በዚህ ረገድ ከዘመነ አክሱም በኋላ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን " ሰለሞናውያን " ተብለው የተነሱ የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገሥታት በአብዮቱ እስኪወገዱ ድረስ ራሳቸውን " ሥዩመ እግዚአብሔር " ማለትም በምድር የእግዚአብሔር ሹሞችና እንደራሴዎች ነን በሚል አዋግዊ የጥንት ፈሊጥ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ፍጹም መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን በሕብረተሰቡ ላይ በጦር ኃይልና በሃይማኖታዊ ርዕዮተ ዓለም በማጠናከር ይህን ጥንታዊ የአክሱም ነገሥታትን የሥልጣንና የርዕዮተ ዓለም ትምህርት በቃልም በተግባርም ሲከተሉ እስከ አብዮቱ ጸንተው ኖሩ ።

## ቋንቋና ጽሕፈት

የአክሱማውያን የግዕዝ ቋንቋ ፣ ፊደልና ጽሕፈት በዓመተ ዓለም ቢያንስ ከአምስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በዘመነ ክርስትና በአራተኛው ምዕተ ዓመት እስከ አፄ ኢዛና ዘመነ መንግሥት ድረስ በ900 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ያሳዩት ባህላዊ ዕድገት ብሎም የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ዝቅተኛ እንደ ነበር ከግዕዝ ቋንቋ የድምፅና የንግግር ሥርዓት ዕድገት ሁኔታ እንደሚከተለው በአጭር መገምገም ይቻላል ።

የግዕዝ ቋንቋ ፣ ፊደልና ጽሕፈት በመነሻ ደረጃ የተከሰተው በዓመተ ዓለም በዘመነ ደአማት መሆኑ በታሪካዊ መረጃ በትክክል የተረጋገጠ ነገር ቢሆንም ፣ እስከ ዛሬ በታወቀው ታሪካዊ መረጃ መሠረት የግዕዝ ቋንቋና ፊደል በዘመናዊ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የተገኘው በዘመነ ክርስትና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት በሰሜን ኢትዮጵያ በዛሬው ትግራይ "ገዳር የአክሱም ንጉሥ"[39] በሚለው አጭር ዜና መዋዕል ነው ።

[39] Caquot et Drewes, " Les Monuments Recueillis," p. 33.

በንጉሥ ገዳር ጽሑፍ የተገኘው የግዕዝ ፊደልና ጽሕፈት ራሱ ገና በድምጽና በንባብ እንዚር ማለትም በድምጽና በንባብ ምልክት ተለይቶ ያልተጻፈ ልሙጥ ግንደ ፊደል ብቻ ነበር ። በሌላ በኩል ከንጉሥ ገዳር እስከ አፄ ኢዛና ድረስ ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ በግዕዝ ቋንቋ ፊደልና ጽሕፈት ብሎም በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ታላቅ የዕድገት እምርታ እንደተገኘ ታውቋል ።


በዚህ አጭር የባህላዊ ፈጠራና ዕድገት ዘመን አንደኛ ከሀያ አራት እስከ ሀያ ስድስት የሚደርሱ የግዕዝ ግንደ ፊደላት ማለትም የድምጽና የንባብ እንዚሮች ወይም የመለያ ምልክቶች የሌላቸው ፊደላት በዘመናዊ ቅርጻቸው ባህላዊ የጽሕፈት መሣሪያዎች እንደሆኑ ተረጋግጧል ።[40] ከሀያ ስድስቱ ግንደ ፊደላት በቅደም ተከተል ከ“ ሀ” እስከ “ተ” ያሉት አስራ አንዱ ፊደላት ልክ የዛሬ ሥፍራቸውን ይዘው ነበር ።[41]

ሁለተኛ ፤ በአፄ ኢዛና ዘመነ መንግሥት አክሱማውያን ምሁራንና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች በታላቅ የፈጠራ ሙያና ተግባር በግዕዝ ልሙጥ ግንደ ፊደላት ላይ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የድምፅ ፤ የንባብና የንግግር ባህላዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የሆኑትን “ካዕብ” ፤ “ሳልስ” “ራብዕ” ፤ “ሐምስ ” ፤ “ ሳድስ ” እና” ሳብዕ” የተባሉ የድምጽና የንባብ እናባቢ እንዚሮችን( ምልክቶችን)ቅጥያዎች በማድረግ የፊደሉን ጠቅላላ ምልክቶች ከሀያ ስድስቱ ግንደ ፊደላት እስከ አንድ መቶ ሰማንያ አራት አሳደጉ ። በተጨማሪም አክሱማውያን በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ ከግዕዝ ፊደል ጋር የግሪክ ቁጥር መጠቀም እንደጀመሩ ከዚህ በሚከተለው በዘመኑ የፊደልና የአሀዝ ገበታ ላይ ይታያል ።

[40] Littmann, *DAE*, IV, Iaf. vi.
[41] Schneider, “ Evolution of the Ethiopian Writing.”



ሠንጠረዥ 1 ፤
በአራተኛው ምዕተ ዓመት የአክሱማውያን የፊደልና የቁጥር ገበታ



የተገኘበት ፤ Littmann, *DAE, IV Taf. VI.*

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ የቀረቡት 24 የግዕዝ ግንደ ፊደላት ከነአናባቢ እንዚርቻቸውና ከግሪክ ቁጥር ጋር የተወሰዱት ፕሮፌሰር ሊትማን <u>የአክሱም ዘመቻ</u> በተባለው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጽሑፎች ቁጥር 9 ፤ 10 እና 11 በሚል ስያሜ ተርጉሞ ካሳተማቸውና በቅደም ተከተል ስለ አጓዛት ፤ ስለፀረኔና ስለኖባ ጦርነቶች ከተጻፉ ከአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች ነው ።

ከፕሮፌሰር ሊትማን ጥናት እንደሚታየው በዚህ የግዕዝ የፊደል ገበታ ተራ ቁጥር በቅደም ተከተል ከ“ ጠ” እና “ፈ” ቀጥለው የሚመጡ የ“ ጰ” እና “ፐ” ግንደ ፊደላት በአራተኛው ምዕተ ዓመት እንደነበሩ የሚያሳይ የጽሑፍ መረጃ እስከ ዛሬ አልተገኘም ። የሆነው ሆኖ ከ“ጰ” እና ከ“ፐ” ጋር የኢትዮጵያ የግዕዝ ግንደ ፊደላት ብዛት 26 ከነእንዚርቻቸው ጋር የፊደሉ ምልክቶች ጠቅላላ ቁጥር ደግሞ $26\times7=182$ ይሆናል ።

በዚህ በግዕዝ መደበኛ ምልክቶች ብዛት ከ“ቀ” ፤ “ኀ” ፤ “ከ”፤ እና “ገ” ግንደ ፊደላት “ቋ”፤ “ኋ” ፤ “ኳ” ፤እና“ጓ” እየተባሉ በልዩ ልዩ እንዚርች የሚፈጠሩ 20 የፊደል ምልክቶች አልተጨመሩም ።ከእነዚህ ጋር የግዕዝ ፊደል ጠቅላላ ምልክቶች ብዛት 202 ይደርሳል ማለት ነው ።

በሌላ በኩል በግዕዙ ጥንታዊ የድንጋይ ላይና የብራና ጽሑፎች ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ያልተገኙ ብሎም ከቅርብ ዘመናት ወዲህ በአማርኛ ቋንቋና ጽሑፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኙ የኢትዮጵያ “ሸ” ፤ “ቸ”፤ “ኘ” ፤ “ኸ” ፤ “ዠ” ፤ “ጀ” ፤እና “ጨ” የተባሉ ሰባት ግንደ ፊደላት አሉ ።

በመሆኑም የግዕዝና የአማርኛ ግንደ ፊደላት ከነአናባቢ እንዚርቻቸው ጋር ሲደመሩ የኢትዮጵያ ጠቅላላ ግንደ ፊደላት ብዛት $26+7=33$ የፊደሉና የእንዚርች ጠቅላላ ድምር ደግሞ $33\times7=231$ ይሆናል ማለት ነው ።

በተጨማሪም ከእነዚህ ከግዕዝና ከአማርኛ ግንደ ፊደላት ማለትም ከ“መ” ፤ “ረ” “ለ” ፤ “ሸ” ፤ “በ” ፤ “ተ ” ፤ “ቸ ” ፤ “ነ ”፤ “ኘ” ፤ “ሰ” ፤ “ዠ” ከላይና ከታች ልዩ ልዩ የካዕብ እንዚርች እየተጨመረባቸው ለምሳሌ “ሯ” ፤“ቧ” ፤“ቧ” እየተባሉ የሚፈጠሩ አያሌ የግዕዝና የአማርኛ የፊደል ልዩ ልዩ ምልክቶች በአንድነት ሲቆጠሩ የኢትዮጵያ ፊደል ጠቅላላ ምልክቶች ብዛት ወደ 300 ይደርሳል ማለት ነው ።

በተጨማሪም በሀያኛው ምዕተ ዓመት የላቲኑ ፊደል “ቨ” ኢትዮጵያዊ የድምጽ ፤ የንባብና የንግግር እንዚርች ተጨምሮለት ከኢትዮጵያ



ግንደ ፊደላት አንዱ በመሆኑ የአገራችን የፊደል ጠቅላላ ምልክቶች ብዛት ከ“ቨ” ተጨማሪ እንዚሮች ጋር ወደ 307 ይደርሳል ማለት ነው ።

በአክሱማውያን መንግሥት የግዕዝ ፊደል የድምፅ ፤ የንባብና የንግግር ፈጠራ በዘመኑ በተለይ በትምህርትና በባህል መስኮች ያስከተለውን ከፍተኛ የዕድገት ለውጥ ለማወቅ ከአናባቢ እንዚሮች ፈጠራ በፊትና በኋላ የተጻፉትን የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች በንጽጽር ማየት ይጠቅማል ።

በዚህ ረገድ ስለ ቤጃ ጦርነት የሚያወራው የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕል የተጻፈው የፊደሉ የድምፅና የንባብ እንዚሮች ከመፈጠራቸው በፊት በልሙጥ ግንደ ፊደላት ሲሆን ፤ ስለ አጓዛትና ስለኖባ ጦርነቶች የሚናገሩ ዜና መዋዕሎች የተጻፉት ግን ከእንዚር ፈጠራ በኋላ ነው ።

በዘመኑ የፊደሉ የነጥብ ሥርዓት ገና ስላልተፈጠረ በሁለቱም በልሙጥና በእንዚራዊ ፊደላት በተጻፉ ጽሑፎች ቃላትና አረፍተ ነገሮች አንዱ ከሌላ የሚለዩበት በመካከላቸው በሚጻፍ የእዝባር ምልክት ነው። ስለዚህም በልሙጥ ፊደላት በተጻፈው ጽሑፍ የቃላትና የአረፍተ ነገሮች ድምጽና ንባብ ለአንባቢው ቀላልና ግልጽ አይደለም ።

በአንፃሩ ግን በእንዚራዊ ፊደላት በተጻፉ ጽሑፎች የቃላትና የአረፍተ ነገሮች ድምፅና ንባብ በካዕብ ፤ በሳልስ ፤ በራብዕ ፤ በሐምስ ፤ በሳድስና ፤ በሳብዕ ምልክቶች ተለይተው ለአንባቢው በቀላሉ እንደሚታዩ ከሚከተሉት ሦስት ምሳሌዎች ግልጽ ነው ።

### ሀ. <u>የፊደሉ የድምፅና የንባብ እንዚር ሕግ ከመፈጠሩ በፊት የተጻፈው የቤጃ ጦርነት ታሪክ መግቢያ</u>

“1. ዐዘነ / ነገሠ/ አክሰመ/ ወዘሐመረ / ወከሰ

2. ወሰበአ/ ወሐበሠተ/ ወረየደነ/ ወሰለሐ/ ወደየ

3. መ/ወበገ/ ለፀረ/ አጸረረ/ ሐዘበ/ በገ/ ፈነወነ / ” [42]

---

[42] Littmann, *DAE*, IV, *Inscription* No. 7,p.10.

ለ. የፊደሉ የድምፅና የንባብ ሥርዓት ከተፈጠረ በኋላ የተጻፈው የእንዛት ጦርነት ታሪክ መግቢያ

"1. ዔዛና / ወልደ/አለ/ዐሚዳ/በእሰየ / ሐሴን / ንጉሠ/ አክ
"2. ሱም/ወዘ/ሕሚር/ወዘ/ ረይዳን/ወዘ/ሰበእ/ወዘ/ሰልሔን/ወ
"3. ዘ/ጽያሞ/ ወዘ/ ብጋ/ወዘ/ካሱ/ንገሠ/ነገሥት/"[43]

ሐ. የፊደሉ የድምፅና የንባብ እንዚር ስርዓት ከተፈጠረ በኋላ የበለጠ በዳበረው ፊደል የተጻፈው የኖባ ጦርነት ታሪክ መግቢያ

1. በኃይለ / እግዚአ/ ሰማይ/ ወምድር/ መዋኢ/ ለዘ/ ከነ/ ዔ
2. ዛና/ወልደ/አለ/ዐሚዳ/ ብእሰየ/ ሐሴን / ንጉሠ / አክሱም / ወዘ/ሕሚ
3. ር/ወዘ/ረይዳን/ወዘ/ሰበእ/ወዘ/ሰልሔን/ወዘ/ጽያሞ/ሕሚ
4. ካሱ/ንጉሠ/ነገሥት/ወልደ/አለ/ዐሚዳ/ዘአይት/መዋኢ/ ለፀር . .[44]

ከዚህ በላይ ለናሙና ከተጠቀሱ የአፄ ኢዛና ዜና መዋዕሎች በተለይ የኖባ ጦርነት ታሪክ የተጻፈበት ጽሑፍ በአራተኛው ምዕተ ዓመት የአክሱማውያን የአፄ መንግሥት በግዛት ፤ በድርጅት ፤ በአስተዳደር ፤ በፀጥታ ፤ በጦር ፤ በዓለም አቀፍ ጉዳይ ፤ በኢኮኖሚ ፤ በቋንቋ ፤ በባህል፤ በስነ ጽሑፍና በሃይማኖት የደረሰበትን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ በአጭር የሚገልጽ አንድ ልዩ ባህላዊ መነጽር ነው ።

ጽሑፉ የተጻፈበት የግዕዝ ቋንቋ በዓለም የቋንቋና የስነ ጽሑፍ ታሪክ የራሱ የሆነ አዲስ እንዝራዊ የድምጽና የንባብ ሥርዓት ያለው ፣ ሰፊና ውስብስብ የሆኑ ብዙ ሃይማኖታዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊ ፣ ድርጅታዊ አስተዳደራዊ ፣ ጉሳዊ ፣ ባህላዊ ፣ ዲፕሎማሲያዊ ታሪካዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ጅኦግራፊያዊ ሁኔታዎችና ነገሮች በስፋትና በጥልቀት የተገለጹበት መንግሥታዊ የትምህርትና የፕሮፓጋንዳ ልሳን አጼ ሆኖ ቀርቦአል ከዚህም የተነሳ የግዕዝ ቋንቋና ጽሕፈት የአክሱማውያን ሥልጣኔ ባህላዊ መሣሪያና መግለጫ ነው ለማለት ይቻላል ።

## የጂኦፖለቲካ ሚና

ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ጥያቄ ከአካባቢው ጂኦፖለቲካ ጋር ማለት ከአፍሪካ ቀንድ ፣ ከቀይ ባህር ፣ ከአባይ

[43] *Ibid., Inscription*, No. 9, p. 24.
[44] *Ibid., Inscription*, No. 11,pp. 32.



ሸለቆ ፣ ከአረቢያና ከመካከለኛው ምስራቅ አንጻር ከአገሪቱ ከተፈጥሮ አቀማመጥና ከየዘመኑ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ ጉዳይ እንደሆነ ተደጋግሞ የተገለጸ ነው ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ የአካባቢው ጥንታዊ የሚርዊና የሳባ መንግሥታት ሥርዓታዊ ውድቀት በመጨረሻ ለአክሱማውያን የአጼ መንግሥት ዕድገትና መስፋፋት ያደረገው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አይዘነጋም ።

በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ፤ በዘመኑ የአክሱማውያን የአጼ መንግሥት የአካባቢው ብቸኛው የበላይ ኃይልና ሥርዓት ሆኖ ከዘመኑ ታዋቂ የዓለም መንግሥታትና ሕዝቦች ጋር ለምሳሌ ከሕንድ ፣ ከፋርስ ፣ ከግብጽ ፣ ከሶሪያ ፣ ከግሪኮችና ከሮማውያን ጋር እንደ ወቅቱ ተጨባጭ ዓለም አቀፍ ሕግና አሠራር በንግድ ፣ በቋንቋ ፣ በባህል ፣ በሃይማኖት ፣ በዲፕሎማሲያዊና በወታደራዊ መስኮችና መንገዶች ሉአላዊ ግንኙነት እንደነበረው ተመልክቷል ።

ለዚህ ጥቅል አባባል የግሪክ ቋንቋና አግልክት በአክሱማውያን ቤተ መንግሥትና ከተሞች መገኘት ፣ በግሪክ ነጋዴዎችና ስደተኞች አማካይነት የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ፣ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ፣ በሃይማኖታዊ ፣ በዲፕሎማሲያዊና በወታደራዊ ጉዳዮች በየጊዜው በአክሱማውያንና በሮማውያን መንግሥታት መካከል የነበረው ሉአላዊ መስተጋብር ፣ በአክሱማውያን የወደብና የመሀል አገር ከተሞች ነዋሪ የነበሩ የተለያዩ የውጭ አገር ነጋዴዎችና ዜጎች ፣ በሃይማኖትና በአካባቢው ሰላም ጉዳይ በ520ዎቹ በአክሱማውያንና በሮማውያን መንግሥታት ትብብር በአረቢያ የተካሄደው ዓለም አቀፍ ጦርነት አንዳንድ ታሪካዊ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች ናቸው ።

ነገር ግን በመጨረሻ ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የአካባቢው አረቢያ ፣ የቀይ ባህር ጠረፎችና መካከለኛው ምስራቅ ከግብጽ ጋር በአዲሱ ዓለም አቀፍ የአረቦች እስላማዊ እንቅስቃሴ ሲያዙ የኢትዮጵያ የአክሱማውያን መንግሥት ለዘመናት በንግድና በባህል ከውጭ ዓለም ጋር የነበረው ጥንታዊ ግንኙነት ቀስ በቀስ እየተቋረጠ ሄደ ።

ከዚህ በኋላ ይህ አዲስ የአረቦች እስላማዊ ሁለአቀፍ የፖለቲካ ፣ የሃይማኖት ፣ የኢኮኖሚና የባህል ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ በቀጥተኛ ወረራ ሳይሆን በኢርቱዕ መንገድ የአገሪቱን የዓለም አቀፍ ንግድ የመግቢያና የመውጫ በር በመዝጋት በአክሱማውያን ሥልጣኔ ላይ የገለልተኝነትና የውድቀት ተጽዕኖ ማሳደሩ በታሪክ የታወቀ ነገር ነው ።

በሌላ አነጋገር የአገሪቱ የቀይ ባህርና የአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ እንደ ዘመኑ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የዕድገትም

አስተዋጽኦ የውድቀትም ተጽዕና ሲያደርግ ኖሮአል ። ለወደፊትም ሲያደርግ እንደሚኖር የታሪክ ልምድ እንዲሁም የጂኦፖለቲካ ሕግ ያስተምረናል ።

በዚህ አኳያ ከውጭ አዲሱ የአረቦች ዓለም አቀፍ ኃይልና እንቅስቃሴ ተጽዕና በአክሱማውያን ሥልጣኔ ላይ የገለልተኝነትና የውድቀት ሁኔታ ከአስከተለበት በኋላ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥትና አዲሱ መንግሥታዊ የክርስትና ሃይማኖት የዕድገትና የመስፋፋት አቅጣጫ በአክሱማውያን ነገሥታት እግር ተከታትለው በተነሱ በአገውና “በሰለሞናውያን” ሥርወ መንግሥታትና ነገሥታት አመራር በሰሜን ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ በደቡብ ወደ መሀል አገር በኢኮኖሚና በባህል መስክ ደግሞ ከንግድ ወደ ፊውዳላዊ እርሻና እንስሳት ርባታ እንደሚዞር በሚቀጥለው ክፍል ይታያል ።

## የአገው መንግሥት ከ1100 እስከ 1270

በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ሰባት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ሦስቱ የሮማውያን ፣ የፋርሳውያንና የአክሱማውያን የአጼ መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ ፣ በአረቢያ ፣ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ዓለም አቀፍ ክልል እርስ በርሳቸው በረጅም የኃይል ሚዛን ትግል ውስጥ እንደነበሩ ይታወሳል ።[1] በመጨረሻ ግን ከ570 እስከ 700 ገደማ ድረስ በአረቢያ፣ በመካከለኛው ምስራቅ ፣ በግብጽና በሰሜን አፍሪካ የሦስቱም የጭቆና ግዛትና ዘመን አንድ በአንድ በዓለም አቀፉ የአረቦች አመጽ ተደመሰሰ።

በተጠቀሱ የአጼዎች ሥልጣንና ሥርዓት ላይ የአረቦች የትጥቅና የርዕዮተ ዓለም ትግል የጀመረው በ520ዎቹ በአረቢያ በአክሱማውያን የባህር ማዶ ግዛት ላይ ነበር ። በ520ዎቹ መባቻ በአረቢያ ህምያሪያዊው አመጸኛ ጽሁኑዋስ ወገኖቹን በግድ በጁዳይዝም ሃይማኖት አደራጅቶ በአክሱማውያን ክርስቲያን ሰፋሪዎችና ወታደሮች ላይ የአመጽ ጦርነት በመክፈት በሕይወትና ንብረት ላይ ታላቅ ጉዳት አስከተለ ። በመሆኑም በ523 እና በ525 የአክሱማውያን አጼ ካሌብ በሮማውያን የፖለቲካ ድጋፍ የጽሁኑዋስን አመጽ ለማጥፋት በመርከብ ጦር ሁለት ተከታታይ ዘመቻዎችን በራሱ መሪነትና አዝማችነት አካሄደ ።[2]

የ523-525 ህምያሪያውን የትጥቅ አመጽ በክርስቲያኑም ዓለም ትብብር እንደዚህ ከተደመሰሰ በኋላ እስከ 575 ድረስ ለአምሳ ዓመታት የአክሱማውያን የአጼ መንግሥት እንደራሴው ንጉሥ አብርሃና ወራሾቹ ልጆቹ

[1] Kobishchanov, *Axum*, p. 37.
[2] Sergew H.Selassie, *History*, pp. 126-135.



የአረብ ገባሮቹን በብርቱ የጦርና የሃይማኖት ኃይል ገዙ ። ነገር ግን በመጨረሻ በ575 የህምያሪያ የመን አመጸኞች በፋርሳውያን ወታደራዊ እርዳታ በአረቢያ የአክሱማውያን ሰፋሪዎችንና ወታደሮችን በሽንፈት ከአገራቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስወጡ ። በመሆኑም ከ575 እስከ 610ዎቹ ድረስ ማለትም እስከ ነቢዩ መሐመድ አመጽ ድረስ አረቢያ በፋርሳውያን እጅ ገባ ።[3]

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ፣ በ632 ነቢዩ መሐመድ ከሞተበት ጊዜ አንስተው የአረብና የቱርክ ተከታዮቹ በአጭር የታሪክ ዘመን በየመን በአማያድ ፣ በሶሪያና በኢራክ በአባሲድ ፣ በግብጽ በፋጢማና በማምሉክ በመካከለኛው ምስራቅ ደግሞ በኦቶማን ካሊፎችና ሱልጣናት መሪነትና አዝማችነት በአረቢያ ፣ በመካከለኛ ምስራቅ ፣ በግብጽ ፣ በሰሜን አፍሪካና በሜዲትራኒያን ባህር አካባቢ ሁለቱን ጥንታዊ የፋርሳውያንና የሮማውያን የአጼ መንግሥታት ደምስሰው በምትካቸው አዲሱን ዓለም አቀፍ የአረብ - ቱርክ እስላማዊ ዘመንና ሥርዓት መሠረቱ ።

ከነቢዩ መሐመድ ሞት በኋላ በአረቢያ የአማያድ ካሊፋዎችን ሥልጣንና የአረቦችን ዓለም አቀፍ የአጼ መንግሥትና ሥርዓት መሥራች እማር ካሊፋ የኢትዮጵያን ታሪካዊ የአዱሊስ ወደብ ከተማ ለመያዝ በ640 [4] የላከው የባህር ኃይል በአክሱማውያን ከተደመሰሰበት በኋላ አረቦች ቀይ ባህርን ተሻግረው በአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያ ምድርና መንግሥት ላይ እንደገና ሌላ የወረራ ሙከራ ለማድረግ ሳይችሉ ቀሩ ። ቢሆንም ከ700 ዎቹ ጀምሮ የዳህላክ ደሴት በቀጥታ በአረብ ሰፋሪዎች ተያዘ ።

የቀይ ባህር ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የግብጽ በአረቦች እጅ መውደቅ በአንድ በኩል በዓለም የንግድ ሥርዓትና በአካባቢው ጂኦፖለቲካ አገልግሎት ላይ ለተመሰረተው የአክሱማውያን ሥልጣኔ ውድቀት በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ሉአላዊና በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ በሰሜን ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ወደ ደቡብና መሀል ለማደግና ለመስፋፋት ዓለምና አገር አቀፍ ሁኔታዎችን ፈጠረ ።

በዚህ አኳያ የቀይ ባህር ጂኦፖለቲካ ከመካከለኛው ምስራቅና ከግብጽ ጋር በአረቦች እጅ ከወደቀ በኋላ በሰሜን ምዕራብ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ መካከል ደግሞ የቤጃ ፣ የሜሮዌና የኖባ ሕዝቦችና አገሮች ከጥንታዊ የአክሱማውያን የፖለቲካና የኤኮኖሚ ተጽዕና ነጻ ወጡ ። እንዚህ የቤጃ ኃይለኛ ዘላን ጐሳዎች በአክሱማውያን የአጼ መንግሥት በቀላል የማይገመት የጠረፍ ጥቃት ፈጸሙ ።

[3] *Ibid.*,pp. 155-158.
[4] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 46.

በመጨረሻም በ1000 [5] ዓመተ ምሕረት አካባቢ እስከ ዛሬ በትክክል ባልታወቀ ወቅትና ሁኔታ በኢትዮጵያ ሰሜኑ ደጋ በላስታ አዲሱ የአገው ማለትም “ዘአገው” ስርወ መንግሥት ተፈጥሮ ከአክሱማውያን የገዥ መደብ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ሥልጣን ወስዶ እስከ 1270 ድረስ ለሦስት ምዕተ ዓመታት ጊዜ ያዘ ።

በሥልጣናቸው ዘመን የአገው ነገሥታት በአክሱማውያን አጼዎች እግር ተተክተው ለኢትዮጵያ በሀውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ ዕድገትና መስፋፋት ጠንካራ መሠረት አበጁ ። በዚህ ረገድና ታሪካዊ የሽግግር ዘመን የአገው ነገሥታት ፤

አንደኛ ፤ በጐሳ ፤ በቋንቋና በባህል በተለያዩ በኢትዮጵያ ኩሻዊ፤ ሴማዊ ፤ አሞአዊና ናይሎቲካዊ ማህበረሰቦች መካከል ለዘላቂ ብሔራዊ አንድነትና ውህደት ታሪካዊ የሥርዓት አንድነት አጠናከሩ ። የሮማውያንና የፋርሳውያን የአጼ መንግሥታት በአረቦችና በቱርኮች እጅ ተንኮታኩተው እንደ ወደቁ የአክሱማውያን መንግሥታዊ ሥርዓት እንዳይጠፋ አደረጉ ።

ሁለተኛ ፤ የአገሪቱን የአዋማዝም ፤ የጁዳይዝም ፤ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶችን በሚከተሉ በጐሳና በቋንቋ በተለያዩ ብዙ ማህበረሰቦች መካከል የሕግና የኃይል ተጽዕኖ ሳይደረግ በአንድ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ሥልጣንና ሥርዓት ስር ለአንድ የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብረተሰብ ዕድገት ሰፊ ፖለቲካዊ መንገድና መሠረት አበጁ ። በአገሪቱ ረጅም ታሪክ የአገው ስርወ መንግሥት በተለይ የሰላም ዘመን ነበር ።

ሦስተኛ ፤ በድህረ አክሱም በአገሪቱ የውጭ ግንኙነትም ጉዳይ በዘመኑ በአካባቢው አዲሱን የእስላም ሃይማኖትና ሥርዓት ከሚከተሉ ኃይለኛ የየመንና የግብጽ አጐራባች መንግሥታት ጋር በተለይም በንግድና በሃይማኖት መስኮችና ጉዳዮች እንደ ወቅቱ ተጨባጭ ዓለም አቀፍ ሁኔታና አሠራር የተሻለ መግባባት ለመፍጠር ብርቱ ብሔራዊ ጥረት አድርጐአል ።

አራተኛ ፤ በዘመኑ ከ1095 እስከ 1365 በመካከለኛው ምስራቅና በግብጽ እስትራቴጂያዊ አገሮች በአውሮፓ ክርስቲያንና በአካባቢው እስላም መንግሥታትና ሕዝቦች መካከል ከተካሄደው ሁል አቀፍ “የመ

[5] *Ibid.*, p. 55.




ስቀል ጦርነት” አገሪቱን ገለልተኛ በማድረግ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ሊደርስበት ከሚችለው ጉዳት በጥበብ አድናዋል ። በመሆኑም በዘመኑ በቅዱሱ ኢየሩሳሌም ከተማ ለአገሪቱ ቤተ ክርስቲያን ከእስላም ባለሥልጣኖች የአምልኮ ቦታ ለማግኘትም ችሎአል ። ይህም ለአገው ነገሥታት ዲፕሎማሲያዊ ጥበብና ችሎታ አንድ ታሪካዊ ምሳሌ ነው ።

አምስተኛ ፤ የአገው ብልህ ነገሥታት በላስታ ከቋጥኝ ድንጋይ አስፈልፍለው ያሰሩት የላሊበላ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች እንደ አክሱም ሾጣጣ የድንጋይ ሀውልቶች የአገሪቱ ብቻ ሳይሆኑ አንድ ታላቅ የዓለም ባህላዊ ቅርስ ናቸው ።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ በሀውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ ከጥንቱ የግዕዝ ፊደልና ጽሕፈት ጋር ዛሬ ብሔራዊ የመገናኛ መሣሪያ ሊሆን የበቃው የአማርኛ ቋንቋ “ልሳነ አጼ” ተብሎ በአገው ስርወ መንግሥት ዘመን በቤተ መንግሥት አካባቢ እንደ ተከሰተ ይነገርለታል ።

ከዚህ በላይ በአጭርና በጥቅል በተዘረዘሩና በሌላ ብዙ ተመሳሳይ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ጥንታዊ ፤ ሉአላዊና በሀውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ ግምባታና ዕድገት ታሪክ የአገው ስርወ መንግሥት በጥንቱና በመካከለኛው ዘመናት መካከል ወሳኝ የሆነ የሽግግር ወቅት ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአገሪቱ በ1270 በተነሳው አዲሱ “ሰለሞናዊ” ስርወ መንግሥት መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ተጽዕኖ የስርወ መንግሥቱ የአነሳስና የአወዳደቅ ዝርዝር ሁኔታ እስከ ዛሬ ድረስ በተረት ጉም ተሸፍኖ ቀርቷል ።

ምናልባትም በሰላም ዘመንና ሥርዓት ስርወ መንግሥታቸው እንደዚህ በምስጢር “በሰለሞናዊ” መሳፍንትና ቄሶች አመጽ በድንገት የተደመሰሰው የአገው ነገሥታት በመንግሥታቸው የውስጥና የውጭ ፖሊሲና ተግባር ከወታደራዊ ጉዳይ የበለጠ ትኃትና ትኩረት ለሃይማኖታዊ ነገሮች በመስጠታቸው ሊሆን ይችላል ። ከእነርሱ በፊትና በኋላ የተነሱ የአገሪቱ የአክሱማውያንና “ ሰለሞናዊ ” አጼ ነገሥታት ለረጅም ዘመን በሥልጣን ኮርቻ ላይ የቆዩት በቀጥታ በአጼው የሚመራ ጠንካራ የወታደር ኃይል ይዘው እንደነበር ይታወቃልና ።



ጥንታዊ የላሊበላ የቋጥኝ ድንጋይ ቤተ ክርስቲያን

## የደቡብ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ዕድገት እስከ 1270

### የታሪክ መረጃ

የቅድመ ታሪክና የዘመነ ታሪክ መለያ ምልክትና ሚዛን የሰነድ መረጃ ነው ተብሎአል ። በዚህ ረገድ ከጥንታዊ ግብጻውያን ፡ ከግሪኮች ፤ ከሮማውያን ፤ ከአረቦችና ከግዕዝ በተገኙ ሰነዳዊ መረጃዎች መሠረት በአፍሪካ ቀንድ በሰሜኑ ክፍል የኢትዮጵያን ጥንታዊ የፑንታውያንን የደአማታውያንን ፤ የአክሱማውያንንና የአገውን ታሪክ በሥፍራና በጊዜ ለማገናዘብ ከዚህ በላይ ጥረት ተደርጐአል ።

ጥንታዊ የግሪክና የሮማውያን ጸሐፊዎች በአፍሪካ ቀንድ ምስራቃዊ ጠረፍ ከአክሱማውያን በታች አያሌ ነባር ሕዝቦችን “ ትሮጅሎዲውያን ፤ ” በርበራውያን ፤ እንጨት ፤ ሳር ፤ ኤሊ ፤ አንበጣ ፤ ሰጐን ፤ አሳና ዝሆን የሚበሉ ሕዝቦች በማለት ገላጭ ባልሆኑ በልዩ ልዩ የወልና የባ



ህል ስሞች በሽፍን ይጠሩ እንደነበር ይታመናል ።[1] በተጨማሪም በጥንታዊ የግሪክ ፤ የሮማውያንና የአረብ ሰነዳዊ መረጃዎች መሠረት በግምት ከ100 ዓመተ ዓለም እስከ 1400 ዓመተ ምህረት ድረስ በአፍሪካ ቀንድ ምስራቃዊ ጠረፍ በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ከዛሬው የጉአርዳፉይ ጫፍ እስከ ዛንዚባር ደሴት ድረስ በሚገኘው የጠረፍ ቀበሌ አዛኒያ የሚባል የባንቱ አገርና መንግሥት እንደነበር ተመልክቷል ።[2]

ባጭሩ በዘመነ ክርስትና ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በቀይ ባህር ከዳህላክ ደሴትና ከጠረፍ ወደቦች እስላማዊ የአረብ ነጋዴዎችና ሰባኪዎች በአፍሪካ ቀንድ እስኪገኙ[3] ድረስ ከላይ ከተጠቀሱ ከትሮጅሎድ ከበርበራና ከአዛኒያ የጠረፍ አገሮችና ሕዝቦች ውጭ ጥንታዊ የግሪክ ፤ የሮማውያንና የአረብ ጸሐፊዎች ስለ ምስራቅ ደቡብና መሀል ኢትዮጵያ ነባር አገሮችና ሕዝቦች ያወቁትና የጻፉት ነገር እስከ ዛሬ ገና አልተገኘም።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ፤ ከላይ እንደተገለጸው ፤ በሐረርጌ ከለጋኦዳ ዋሻ ፤ በሲዳሞ ከሻቤ ዋሻ ውስጥ በድንጋይ ላይ ተስለው የተገኙ ጥንታዊ የእንስሳትና የሰዎች ስዕሎች እንዲሁም በደቡብ ሸዋ ፤ በአርሲና በሐረርጌ ደጋ ብዙ ሥፍራዎች የሚገኙ የትክል ድንጋይ ሀውልቶች በጥንታዊ ግብጻውያን ፤ ግሪኮች ፤ ሮማውያንና አረቦች ሆነ በአክሱማውያን በቀጥታ ባል ተደረሰው በደቡብ ኢትዮጵያ ቢያንስ ገና ከዛሬ 4000 ዓመታት ገደማ ጀምሮ በእንስሳት እርባታ ፤ በእርሻና በዕደ ጥበብ ተግባራት የተሰማሩና የሰለጠኑ ብዙ ጥንታዊ ሕዝቦች ይኖሩበት እንደ ነበር በግልጽ ያመለክታል ።[4]

### የደቡብ ነባር ሕዝቦች

በደቡብ ኢትዮጵያ የተጠቀሱ የዋሻ ድንጋይ ላይ ስዕሎችንና የመቃብር ላይ ሀውልቶችን የሠሩ ጥንታዊ ሕዝቦችን ማንነትና ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ እስከ ዛሬ ድረስ በደቡብ ምስራቅ በተለይም በሐረርጌ


---

1 Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 78-79, 116-136; J.D.Fage, *An Atlas of Africa History*, (1982), map. 8,p.36.

2 *Ibid.*, Histoire Sommaire, pp. 82-83.

3 G.W.B.Huntingford, "Arabic Inscriptions in Southern Ethiopia", *Antiquity* (vol. 29 (1955), pp. 230-33.

4 F. Anfray, " Les Steles du sudshoa et Sidamo " *AE*, No. 12 (1982); R. Joussoume, *Legalithisme EN Ethiopie: Monuments Funeraires Proto-Historiques du Harar* 1979) pp. 101-103.



ጥንታዊ የላሊበላ የቋጥኝ ድንጋይ ቤተ ክርስቲያን

የአካባቢው ነዋሪዎች በትውፊታዊ ግንዛቤያቸው የጥንቱ " የሀርላ ሕዝቦች" በሚል ጥቅል ስያሜ እንደሚጠሩአቸው ታውቋል ።[5]

ከታሪክ አንጻር ደግሞ ከአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በአካባቢው በዛሬው የሱማሌ የኦሮሞና የአፋር ማህበረሰቦች እስኪወረስ ድረስ በምስራቅ ኢትዮጵያ ዛሙባራህ ፤ ባርዛራህ ፤ ያቀላህ ፤ ጃዛር ፤ አራብ ታከላና አልቃ በተባሉ በራሱ እያሌ ጉሳዎችና ማህበረሰቦች የተከፈለ በእንስሳት እርባታ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራና በባላባታዊ ሥርዓት የሚኖር አንድ ጥንታዊ " ሀርላ" የተባለ አገርና ሕዝብ እንደ ነበር ከዘመኑ ሰነዳዊ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ይችላል ።[6]

በመሆኑም በእነዚህ በተጠቀሱ - የአርኪኦሎጂ ፤ የትውፊትና የታሪክ መረጃዎችና ማስረጃዎች መሠረት ከደቡብ ኢትዮጵያ እያሌ ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ በዘር ፤ በቋንቋና በሃይማኖት በደቡብ ምስራቅ ከዛሬ የአደሬ ሕዝብ ጋር የቀረበ ግንኙነት የነበረው የሀርላ ሕዝብ እንደነበር ይታመናል ። በተጨማሪም በደቡብ ኢትዮጵያ ፤

1. በግምት በምስራቅ ከዋቤ ወንዝ በምዕራብ እስከ የጊቤ ወንዝ ድረስ በሚገኘው ምድር በአስራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ገዳይቾ ፤ ጉዳላ ፤ ዲሆ ፤ ሀይባ ፤ ገንዘ ፤ ስጋ ፤ ገባ ፤ ቀቤና ፤ ጉጋለና አለባ በተባሉ አሥር የጉሳ ማህበረሰቦች ተከፍሎ የነበረው የሀዲያ - ሲዳማ ሕዝብ ፤[7]

2. በደቡብ ምዕራብ ከአባያ ሀይቅ እስከ ጉጀብ ወንዝ በሚገኘው በኦሞ ሸለቆ ክልል የተለያዩ የጋሞ - ወላይታ ሕዝቦች ፤[8]

3. በመሀል - ምዕራብ በአዋሽ ፤ በሙገር ፤ በጊቤ ፤ በአባይ ፤ በዲዴሳና በጉጀብ ወንዞች አካባቢ በታሪክ ዳሞት ፤ ሂናሮ ( እናርያ ) ፤ ቦሻ ከፋ ፤ ሸከቾ ( ሞቻ) ፤ ቢዛሞ ፤ ሺናሻና አንፊሎ ተብለው በልዩ ልዩ የጉ

[5] U. Braukamper, "Islamic Princpalities in South-East Ethiopia between the13th and the 16th Centuties," Part I and II, Ethiopianist Notes Vol 1 No. 1 (1977). p.p. 20-21.

[6] G.W.B. Huntingford, tr. and ed., *The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia* (1965), p. 74; Arab - Faqih, *Histoire de la Conquete de L'Abyssinie*, tr. and ed. by R. Basset (1897), pp. 111,118, 124, 130, 150, 170, 171.

[7] Huntingford, *Glorious Victories*, pp. 19-23; Omari, *Masalik* pp. 14-18; J Perruchon, tr. and ed., *Les Chraniques de Zara Yaeqob et de Maeda Maryam* (1893); pp 16-18; U. Braukamper, *Geschichte Der Hadiya Sud-Athiopiens* (1980), maps. 6-18.

[8] C.F. Beckingham and G.W.B. Huntingford, trs and eds., *Some Records of Ethiopia* 1593-1646( 1954), pp.LXV-LXVII.



ሳና የማህበረሰብ ስሞች ለሚታወቁ እያሌ ነባርና ተዛማጅ አገሮችና ሰዎች የጋራ መነሻ የሆነው የጉንጋ ሕዝብ ፤[9]

ከላይ ከተጠቀሰው የሀርላ ሕዝብ ጋር የደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝቦች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙት የሰነድ መረጃዎች ውስጣዊ ጥንቅር እንደሚያሳየው በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በኤደን ባህረ ሰላጤና በጊቤ ወንዝ መካከል የነበሩ ጥንታዊ ማህበረሰቦች ከሀርላና ከሀዲያ ሕዝቦች ጋር በሰፍራ በዘርና በታሪክ የቀረበ ግንኙነት እንደነበራቸው ተገምቷል ።[10]

## የመንግሥት ምሥረታና ዕድገት

እነዚህን የተለያዩ ጥንታዊ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችን በተለይም ተዛማጅ የሀርላና የሀዲያ ማህበረሰቦችን በግምት ከስምንተኛው ምእተ ዓመት ወዲህ በንግድ ፤ በተደራጀ መለኮታዊ ሃይማኖት ( Monothesitic Religion ) በባህልና በመንግሥት ምስረታ ተግባራት ለመጀመሪያው ጊዜ ከውጪ ዓለም ጋር ያገናኘው ታላቅ የታሪክ ኃይል በቀይ ባህር ከዳህላክ ደሴትና በኤደን ባህረ ሰላጤ ከዜላ ወደብ በእስላም ነጋዴዎችና ሰባኪዎች አማካይነት ወደ መሀል አገር ዘልቆ የገባው የእስላም ሃይማኖትና ትምህርት ነው ።

በዚህ ወቅትና ሁኔታ ከዳህላክ ደሴትና ከዜላ ወደብ የገቡ የእስላም ነጋዴዎችና ሰባኪዎች በሲራራ ንግድ መስመሮች በመሀል አገር ከአዋሽ ሸለቆና ከጩርጩር ተራራዎች ባሻገር እስከ ታላላቅ ሀይቆችና የጊቤ ወንዝ ዘልቀው በመላው የሀርላ - ሀዲያ ምድር የንግድ ፤ የሃይማኖትና የመንግሥት ምስረታ ትምህርትና ተግባራት በስፋት አስፋፉ ።[11]

ከዘጠነኛው ምዕተ ዓመት እስከ አስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ የተጠቀሱ የንግድ መስመሮች በሚያልፉባቸው አገሮች በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቁ የደቡብ ኢትዮጵያ እስላማዊ የሸዋ (ከ890 ገደማ ጀምሮ) ፤ የይፋት ፤ የአዳል ፤ የሞራ ፤ የሁባት ፤ የጀዳያ ፤

[9] Huntingford, *Glorious Victories, P.45*; O. G. S. Crawford, ed, *Ethiopian Itineraries Ca.* 1400-1524 (1958), pp. 78-84; Tekle Selassie, *Susenyos* 1615-1632 ( Unpublished Chronicle); W. Lange, *History of the Southern conga: South Western Ethiopia* (1982),

[10] Braukamper, " Islamic Principalities", I, pp. 19-22.

[11] Crawford, *Ethiopian Itineraries*, p. 80.

ሠንጠረዥ 2

በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት የደቡብ ኢትዮጵያ መንግሥታት የመሬት ፤ የጦርና የድርጅት ገጽታዎች

| አገር | የአገር ስፋት በስኩዌር ኪሎ ሜትር | | | የጦር ድርጅት በወታደርና በፈረስ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁመት በኪሎ ሜትር | ጐን በኪሎ ሜትር | ስፋት በስኩዌር ኪሎ ሜትር | የእግር ጦር | የፈረስ ጦር | ድምር |
| 1. ይፋት | 288 | 384 | 111.000 | 20000 | 15000 | 35000 |
| 2. ደዋር | 96 | 38 | 3600 | 2000 | 15000 | 35000 |
| 3. አራባቢኒ | 77 | 77 | 5900 | 10000 | 10000 | 20000 |
| 4. ሀዲያ | 160 | 172 | 27500 | 80000 | 40000 | 120000 |
| 5. ሻርካ | 58 | 96 | 5500 | 5000 | 3000 | 8000 |
| 6. ባሌ | 384 | 120 | 46000 | ብዙ ሺህ | 18000 | ከ18000 በላይ |
| 7. ደራ | 57 | 57 | 3300 | 2000 | 2000 | 4000 |
| ድምር | 1,120 | 944 | 203,000 | ከ137000 በላይ | 103000 | ከ240000 በላይ |

ምንጭ Omari, *Masolik* pp. 5-16; Huntingford, *Glorious Victories*, pp. 20-23.



የደዋር ፤ የአራባቢኒ ፤ የሀዲያ ፤ የፈጠጋር ፤ የሻርካ ፤ የባሊና የደራ ንዑስ ማህበረሰቦችና መሳፍንታዊ መንግሥታት እንደ እንጉዳይ ተከሰቱ ።[12]

ከእነዚህ የኢትዮጵያ እስላማዊ ማህበረሰቦች የይፋት - አዳል ሱልጣኔት ከበስተ ምስራቅ በግምት ከዛሬው ምስራቃዊ ሸዋና ከሐረርጌ ደጋ ክልል አንስቶ በጠረፍ እስከ ኤደን ባህረ ሰላጤና ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ የሚገኘውን ሰፊ መሬት ይዞ በሃይማኖት ፤ በትምህርትና በባህል በአካባቢው የተቀናጁ ሱልጣኔቶች ማዕከልና መንፈሳዊ መሪ አገር እንደ ነበር ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የዘመኑ ሰነዳዊ መረጃዎች ያሳያሉ ።

በ14ኛው ምዕተ ዓመት በይፋት ሱልጣኔት ከታወቁ የእንስሳት ዓይነትና ምርቶች ላም ፤ በግ ፤ ፍየል ፤ ዶሮ ፤ ፈረስ ፤ በቅሎ ፤ ቅቤ ፤ ማር ፤ የዱር አራዊት ዓይነትና ምርቶች አንበሳ ፤ ነብር ፤ ጅብ ፤ ጉሽ ፤ የሜዳ ፍየል ፤ የሜዳ አህያ ፤ ሰጐን ፤ ኢጋዘን ፤ አውራሪስ ፤ የእህል ሰብል ዓይነትና ምርቶች ፤ በቆሎ ፤ ዘንጋዳ ፤ ጤፍ ፤ አደንጓሬ ፤ የአትክልት ዓይነትና ምርቶች ጉመን ፤ ሸንኮራ ፤ አገዳ ፤ ሜት ፤ ኮክ ፤ ሎሚ ፤ ወይን ፤ ሙዝ ፤ ብርቱካን እንጆሪ ፤ አበሱዳ (ጥቁር አዝሙድ)፤ በለስ ፤ በደረጀን ፤ በጤሀ ፤ ኪያር ከሸንኮራ አገዳ የሚሠራ ከረሜላ ( በዛሬው መተሃራ አካባቢ) ዋና ዋናዎቹ ነበሩ ። [13]

ከጥንት እስከ አስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ በመሀል - ምዕራብ ኢትዮጵያ በግምት በምስራቅ ከዛሬው ምዕራባዊ ሸዋ አንስቶ በምዕራብ እስከ ከፋና ወለጋ ድረስ የጉንጋ ሕዝብ ምድር በነበረው በአዋሽ በሙገር ፤ በአባይ ፤ በጊቤ ፤ በዲዴሳና በጉጀብ ታላላቅ ወንዞች ክልል ዳሞት በራሱ ዘውዳዊ ሥርዓት የሚገዛ አንድ ታላቅ የደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርና መንግሥት እንደነበር ይታወሳል ።[14] በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ አካባቢ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እየተስፋፋ በመምጣት ይህ ታላቅ አዋማዊው የዳሞት መንግሥት የይፋት ሱልጣኔትንም ያስገብር እንደነበር በዘመኑ ተመዝግቦአል ።[15]

ባጭሩ የአካባቢውን የጥንት ታሪካዊ ዕድገት በተመለከተ ፤ በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት "በሰለሞናዊ" ነገሥታት አመራር ከሰሜኑ ደጋ በመላው ደቡብ ኢትዮጵያ የመስፋፋት

---

12 Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 60-63; Huningford, *Glorious Victories* pp. 14-15, 18-23. Omari; *Masalik*, *Maqrizi*, *Moslem kings*; *Arab-Faqih*, *Conqueet-Perruchon*, *Chroniques*; *Br* Braukamper, *Hadiya*.

13 Omari, *Mamalik*, pp. 9-14,

14 Crawford, *Ethiopan Itineraries*, 80.

15 *Ibid.*, *Taddasse Tamrat*, *Church and State in Ethiopia* 1270-1527 (1972), pp. 122-23., UNESCO, *African History*. III, p. 580.

ፖሊሲውን በጀመረበት ጊዜ በመላው መሀል አፍሪካ ቀንድ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በዴዴሳ ሸለቆ መካከል በሚገኘው ቀበሌ ሦስት በመንግሥት ደረጃ ተደራጅተው የነበሩ ነባር ሕዝቦችና አገሮች ፤

1. በምስራቅ በሀርላ ምድር የይፋት ሱልጣኔት ፤

2. በመሀል ደቡብ የሀዲያ ሱልጣኔት


3. በመሀል ምዕራብ በጉንጋ ምድር የዳሞት አዋማዊ መንግሥት በዘመኑ ለዓይነት የሚቀርቡ ሦስት ታላላቅ በሰነድ የታወቁ የደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥታት ነበሩ ።

በወቅቱ ሦስቱም የይፋት ሱልጣኔት ፤ የሀዲያ ሱልጣኔትና የዳሞት መንግሥት በየአካባቢያቸው በዕድገትና በመስፋፋት ሂደት ላይ እንደ ነበሩ የዘመኑ የኢትዮጵያና የአረብ ሰነዶች ጨምረው ያሳያሉ ። በመጨረሻ በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት ሁሉም በአንድነት ከሰሜኑ ደጋ ወደታች እየተስፋፋ የመጣው የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ውስጣዊ አካላትና አባላት ሲሆኑ በጥናቱ በሚከተለው ክፍል ይታያል ።



በ3000 ዓመታት የተገመተ የእንስሳት ስዕል በጥንታዊው የሻቤ ዋሻ በሲዳሞ






የአፄው መንግሥት ዕድገት ከ1270 እስከ 1524

ፖሊሲውን በጀመረበት ጊዜ በመላው መሀል አፍሪካ ቀንድ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በዴዴሳ ሸለቆ መካከል በሚገኘው ቀበሌ ሦስት በመንግሥት ደረጃ ተደራጅተው የነበሩ ነባር ሕዝቦችና አገሮች ፤

1. በምስራቅ በሀርላ ምድር የይፋት ሱልጣኔት ፤

2. በመሀል ደቡብ የሀዲያ ሱልጣኔት


3. በመሀል ምዕራብ በጐንጋ ምድር የዳሞት አዋማዊ መንግሥት በዘመኑ ለዓይነት የሚቀርቡ ሦስት ታላላቅ በሰነድ የታወቁ የደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥታት ነበሩ ።

በወቅቱ ሦስቱም የይፋት ሱልጣኔት ፤ የሀዲያ ሱልጣኔትና የዳሞት መንግሥት በየአካባቢያቸው በዕድገትና በመስፋፋት ሂደት ላይ እንደ ነበሩ የዘመኑ የኢትዮጵያና የአረብ ሰነዶች ጨምረው ያሳያሉ ። በመጨረሻ በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት ሁሉም በአንድነት ከሰሜኑ ዶጋ ወደታች እየተስፋፋ የመጣው የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ውስጣዊ አካላትና አባላት ሲሆኑ በጥናቱ በሚከተለው ክፍል ይታያል ።



በ3000 ዓመታት የተገመተ የእንስሳት ስዕል በጥንታዊው የሻቤ ዋሻ በሲዳሞ






የአፄው መንግሥት ዕድገት ከ1270 እስከ 1524

## 2. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአጼው መንግሥት ዕድገት ከ1270 እስከ 1524 የታሪክ መረጃ

በኢትዮጵያ ረጅም በሀውርታዊ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ከ1270 እስከ 1524 ድረስ ያለው ዘመን በአፍሪካ ቀንድ የአዋማዝም የጁዳይዝም ፣ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ አራት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች በአንድ የኢትዮጵያ ማዕከላዊው አጼ መንግሥት ሥር ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት የተደራጁበት ታሪካዊ ዘመን ነው ። የዘመኑንም ታሪክ የሚገልጹ ቁልፍ የሰነድ ምንጮች የሚከተሉ ናቸው ።

1. ከዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በደቡብ ኢትዮጵያ የእስላማዊ መንግሥታትን ምሥረታና ዕድገት የሚገልጹና በአካባቢው በአረብኛ ቋንቋ በመቃብር ድንጋይ ላይ የተጻፉ ጥንታዊ ጽሑፎች ፣[1]
2. በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአፍሪካ ቀንድ የአዋማዝም ፣ የጁዳይዝም የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ብዙ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ ሕዝቦች በማዕከላዊው የአጼ መንግሥት ሥር በአንድነት መደራጀታቸውን የሚገልጽ የአጼ ዓምደጽዮን ዜና መዋዕል ፣[2]
3. በደቡብ ኢትዮጵያ የእስላማዊ አገሮችንና መንግሥታትን ታሪክ የሚገልጹ በቅደም ተከተል በ1330ዎቹና በ1430ዎቹ (በአንድ ምዕተ ዓመት ውስጥ) በሁለት ታዋቂ የአረብ የታሪክ ባለሙያዎች ኦማሪና ማክሪዝ የተጻፉ ሁለት መጻሕፍት ፣[3]
4. በ1434—1468 የአጼ መንግሥስትን የድርጅትና የአስተዳደር ጉዳይ በሚመለከት የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ፣[4]
5. በኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ዋዜማ በ1520—1527 የኢትዮጵያን የአጼ መንግሥትና ሕብረተሰብ ጥንቅርና አስተዳደር የሚገልጽ የፖርቱጋሉ አልቫሬዝ ገላጭ መጽሐፍ ፣[5]

---

[1] Hunt ngford, " Arabic Inscriptilon in Southern Ethiopia," p. 230.
[2] *Ibid.*, *Glorious Victories.*
[3] Omari, ***Masalik***; Maqrizi, ***Moslem Kings.***
[4] perruchon, *Les Chroniques.*
[5] F. Alvarez, *The Prester John of Indies*, 2vols., trs and eds by C. F. Beckingham and G.W.B. Huntingford ( 1969).



6. በ1524—1543 የኢማም አህመድ ግራኝን ጦርነት መነሻና ሂደት የሚገልጽ የአረብ ፋቂህ መጽሐፍ ፣[6]

በአንድነት የዘመኑ ታሪክ ቁልፍ የመረጃ ምንጮች ናቸው ።

### መንግሥትና ሃይማኖት

ሁለቱ የዓለም ታላላቅ መለኮታዊ ( Monotheaitic) የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ ምድር መገኘት የአገሪቱን የመንግሥት ምሥረታ ሂደትና እድገት በኃይል አሰፋ ። ከሁለቱ በ330ዎቹ ወደ አክሱማውያን አገርና ቤተ መንግሥት የገባው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ የክርስትና ሃይማኖት ፣ ለአስራ ስድስት ምዕተ ዓመታት በኋላ በ1974 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ሃይማኖትን ከመንግሥት ጉዳይ እስኪለየው ድረስ ፣ የአጼ ነገሥታት አንድ ታላቅ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም መገሪያ ሆነ ። በተለይም ከ1270 እስከ 1974 ድረስ “ በሰለሞናውያን ” ስርወ መንግሥት ዘመን ከመላው የአጼ መንግሥት መሬት አንድ ሲሶው የቤተ ክርስቲያኑ ድርጅታዊ ይዞታ እንደሆነ ይታመን ነበር ።

በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ገደማ ከአረቢያ ቀይ ባህርን ተሻግር በነጋዴዎችና በሃይማኖት ሰባኪዎች አማካይነት በሲራራ ንግድ በሮችና መስመሮች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የገባው የእስልምና ሃይማኖት ደግሞ በበኩሉ ከ890 እስከ 1330 ድረስ በአምስት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ በግምት ከኤደን ባህረሰላጤ እስከ ጊቤ ለተከሰቱ የሸዋ ፣ የይፋት ፣ የደዋሮ ፣ የሀዲያ ፣ የአራባቢኒ ፣ የሻርካ ፣ የባሊ ፣ የደራ ፣ የፈጠጋር ፣ የአዳል ፣ የሞራ ፣ የገርጋያ ፣ የሁባትና የጅዳያ እስላማዊ ሕዝቦችና አዳጊ መንግሥታት ታላቅ ድርጅታዊ የፖለቲካ ፣ የትምህርትና የርዕዮተ ዓለም መሠረትና መገሪያ ሆነ ።[7]

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ሚና ሲገመገም የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታይ የገዥ መደቦች በግዛትና በሥልጣን ትግል በየፊናቸው ሃይማኖታቸውን እንደ መገሪያ እየተጠቀሙ በመካከላቸው ለረጅም ዘመን ባካሄዱ ጦርነቶች በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ላይ በሕይወትና ንብረት ታላቅ ጥፋት እንዳስከተሉ የዘመኑ ታሪክ ያስተምረናል ። ከ1270 እስከ 1577 ከሁለቱም ወገኖች የጦርነቱ ተዋንያን የሚከተሉት ክርስቲያን “ ሰለሞናዊ ” ነገሥታትና እስላም የዋልስማ ሡልጣኖች ነበሩ ።

---

[6] Arab-Faqih, *Histoire de la Conquete de L' Abyssinie*, tr and ed. by R. Basset (1897).
[7] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 46-47.

ሠንጠረዥ 3

**በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ የሥልጣን ባላንባ አጼዎችና ሱልጣኖች**

**1270-1597**

| "ሰለሞናዊ" አጼዎች | | | የይፋት-አዳል ዋለስማ ሱልጣኖች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ. | አጼ | ዘመነ መንግሥት | ተ.ቁ. | ሱልጣን | ዘመነ መንግሥት |
| 1 | ይኩኖ አምላክ | 1270-1285 | 1 | ኡማር ዋለስማ | 1285-? |
| 2 | ቀዳማዊ ሰለሞን | 1285-1294 | 2 | ባዘ | -?-? |
| 3 | ባሀር አስገደ | -?-? | 3 | ቀዳማዊ ሀቀዲን | 1390-132? |
| 4 | ሰንፋ አስገድ | -?1297 | 4 | ቀዳማዊ ሱብረዲን | 132?-1332 |
| 5 | ሕዝበ አራድ | -?--? | 5 | ቀዳማዊ ጀማልዲን | -1332 |
| 6 | ከድማ አስገድ | -?-? | 6 | ናስረዲን | -1332 |
| 7 | ዝሀን አስገድ | -?1299 | 7 | ዓሊ | ?-? |
| 8 | ወደም አራድ | 1299-1314 | 8 | አህመድ | ?-? |
| 9 | ቀዳማዊ ዓመደ ጽዮን | 1314-1344 | 9 | ዳግማዊ ሀቀዲን | 1376-1387 |
| 10 | ንዋየ ክርስቶስ | 1344-1372 | 10 | ሰአዲን | 1387-1415 |
| 11 | ንዋየ ማርያም | 1372-1382 | 11 | ዳግማዊ ሱብረዲን | 1415-1422 |
| 12 | ቀዳማዊ ዳዊት | 1382-1413 | 12 | ማንሱር | 1422-1525 |
| 13 | ቀዳማዊ ቴዎድሮስ | 1413-1414 | 13 | ዳግማዊ ጀማልዲን | 1425-1433 |
| 14 | ይስሐቅ | 1414-1429 | 14 | በድላይ | 1433-1445 |

| "ሰለሞናዊ" አጼዎች | | | የይፋት—አዳል ዋለስማ ሱልጣኖች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ. ቁ. | አጼ | ዘመነ መንግሥት | ተ. ቀ. | ሱልጣን | ዘመነ መንግሥት |
| 15 | እንድርያስ | 1429-1430 | 15 | ሙሐመድ በድላይ | 1445-1471 |
| 16 | ተክለ ማርያም | 1430-1433 | 16 | ሻምሱዲን ሙሐመድ | 1472-1487 |
| 17 | ሰርዋኢየሱስ | -1433 | 17 | ሙሐመድ አዝሀረዲን | 1488-1518 |
| 18 | ዓምደ ኢየሱስ | 1433-1434 | 18 | አቡባከር መሐመድ | 1518-1527 |
| 19 | ዘርዓ ያዕቆብ | 1434-1468 | 19 | ኡማርዲን | 1527-1553 |
| 20 | በእደ ማርያም | 1468-1478 | 20 | ዐሊ ኡማርዲን | 1553-1555 |
| 21 | እስክንድር | 1478-1494 | 21 | በራካት ኡማርዲን | 1555-1560 |
| 22 | ዳግማዊ ዓምደጽዮን | -1494 | 22 | ታልሃ | 1560-1571 |
| 23 | ናአድ | 1494-1508 | 23 | ናስር | -1571 |
| 24 | ልብነ ድንግል | 1508-1540 | 24 | ሙሐመድ አራተኛው | 1571-1577 |
| 25 | ገላውዴዎስ | 1540-1559 | | | |
| 26 | ሚናስ | 1559-1563 | | | |
| 27 | ሠርፀ ድንግል | 1563-1597 | | | |

ምንጭ

R. Pankhurst, *Ethiopian Royal Chronicles* (1967);
Huntingford, *Glorious Victories*; Maqrizi, *Moslem Kings*; *Trimingham, Islam*, p. 70.